# ይህች አለም ምን ትሆናለች?

## የእግዚአብሔር የማዳን እቅድ

ኤቫንጌልዩም ሚሲዮን
ባድ ዛልስ ኡፍን

የኢቫንጌልየም ሚሽን
ፖ.ሣ.ቁ. 19747
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ትርጉም:- ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ በወ/ዊ ሽመልስ ረጋ

የማተምና የማባዛት መብት
ኢቫንጌልየም ሚሽን ዮአኪም ላንግሐመር
1998 እ.አ.አ.

መጽሐፉ የተተረጎመባቸው ቋንቋዎች:-

| ቋንቋዎች | ብዛት |
|---|---|
| ራሽያ | 700000 |
| ሮማንያ | 110000 |
| ኮርሽንቲያ | 70000 |
| ግሪክ | 25000 |
| ሃንጋሪ | 40000 |
| ስሎቫኪያ | 20000 |
| ቡልጋሪያ | 15000 |
| እንግሊዝኛ | 10000 |
| አልባንሽ | |
| ጀርመን | 15000 |
| አማርኛ(ኢትዮጵያ) | 5000 |

# ማውጫ


መቅድም ......... 5
መግቢያ ......... 6
ይህች አለም ምን ትሆናለች ......... 7
የእግዚአብሔር የማዳኒ ምክር ......... 9
የእግዚአብሔር የማዳን እቅድ በመጽሐፍ ቅድስ ......... 11
አልፋና ኦሜጋ /የመጀመሪያና መጨረሻ የሌለው/......... 20
የጕልጕታው መስቀል ......... 23
የአምላክ ሶስትነት /ስላሴ/......... 25
1. እግዚአብሔር አብ ......... 27
2. እግዚአብሔር ወልድ ......... 27
3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ......... 30
የአለም ሕዝብ የእስራኤል ሕዝብ እና
የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ......... 35
1. የአለም ሕዝቦች ......... 36
2. የእግዚአብሔር የመዳን ታሪክ ከእስራኤል ጋር ......... 44
3. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ......... 63
እስራኤል - በእግዚአብሔር በአለም ሰአት ላይ ......... 77
1. የእስራኤል ሕዝብ መበተን ......... 78
2. የእስራኤል ተበትና በነበረችበት ዘመን ......... 87
3. የእስራኤል ሕዝብ መመለስ ......... 99
4. የእስራኤል በመጨረሻዎቹ ቀናት ......... 113
የአሕዛብ ዘመን ......... 114
1. የዓለም አራቱ ኃያላን መንግስታት መነሳት ......... 125
2. ፀረ ክርስቶስና መንግሥቱ ......... 121
የጐግ ማጐግ ......... 170
የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ......... 181
1. የጌታ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ መመለሱ ......... 183
2. የኢየሱስ ክርስቶስ ለአህዛብ መመለስ ......... 186
3. የኢየሱስ ክርስቶስ ለእስራኤል ህዝብ መመለስ ......... 194

የመሲሁ የሰላም መንግስት (የሺህ ዓመት መንግሥት) ........................................ 198
የመጨረሻው ፍርድ ........................................................................212
አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ..............................................................219
መግለጫ ክፍል 1 ሁለቱ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረጎች..................................222
መግለጫ ክፍል 2 ከመጽሐፍ ቅዱስ የጊዜ አቆጣጠር ጋር ያለ ችግር ........................235
መግለጫ ክፍል 3 በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ የቤተ መቅደስ መስፋፋት......240
መግለጫ ክፍል 4 በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ውስጥ ሰባቱ ዘመናት........................250
ምሥጋና.................................................................................258



# መቅድም

የሚቀጥሉት መግለጫዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የድነትን ታሪክ ካርታ የሚያብራሩ ናቸው። የበለጠ እይታ ለማግኘት ይቻል ዘንድ የሚያብራሩ ይሆናሉ። ካርታው የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ በጂኦግራፊ አቀማመጥ በተቻለ አቅም ለማብራራት የሚያስችል ነው።

ያለፉትና በአሁን ጊዜ ያሉት ሁኔታዎች መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ እንደተነበየው የድነት ታሪክ በቅርብ ጊዜ የሚፈጸም መሆኑን ያረጋግጡልናል። የድነትን ታሪክ በማገናዘብ የእግዚአብሔርን ቃልና ዋናዎቹን የድነትን ትይይዝ በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን። በማዳን ዕቅድ ስብከት ብዙ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳለው የማዳን ዕውቀት በመምጣታቸው እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ይህ ካርታ የትንቢትን ቃል፣ የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ ከእስራኤል ጋር ያለውን፣ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ዘመንና የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአት ላጠኑ አማኞች ክፍተኛ ድጋፍ ሆኗል፣

የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የታቀደው ለእኛ ለሰው ልጆች ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መላዕክት እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ ስለ እኛ የፈጸመውን ታላቅ ደህንነት ይመለከቱ ዘንድ እንደሚናፍቁ ይናገራል (1ጴጥ.1:12)። በእርሱ ምህረትን ያገኙት ኃጢአተኞች ብቻ ከመዝሙር ደራሲው ጋር ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ይጠራል ይህን የማጽናናት ቃል ለሁሉም «አውጁ» በማለት ከእርሱ ጋር ሊደሰቱ ይችላሉ። ***«ኢየሱስ ሐጢአተኛን ይቀበላል ስለዚህ ይህን አጽናኝ ቃል ለሁሉም ተናገር»***

የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ አንድን ነገር በጣም ግልጽ ያደርጋል። ይኸውም እግዚአብሔር በአድልዎ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ እድርጎ ሳይመለከት ሁሉንም እኩል መውደዱን ነው። ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ ወደ እርሱ እንዳለን እንመጣለን። ጌታ ኢየሱስም ሕይወታችንን ይቀይራል (ይለውጣል)። በእርሱ ስናምን በክበረ ደሙ ከኃጢአት ያነጻንና የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ያደርገናል። ምክንያቱም «ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ሁሉ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው» (ዮሐ.1:12) ተብሏልና። ጥልቅ የሆነው ትልቁ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ፍቺ ይህ ነው ለማንኛውም የደህንነትን ታሪክ ካርታ ይህን መጽሐፍ ድጋፍ አድርገው ለሚያጠኑት የእግዚአብሔርን የዘላለም ደህንነት እንዲይዙና ጌታ በግላቸው :-

«ይህን ለአንተ አደረግሁ፣ አንተ ደግሞ ለእኔ ምን ታደርጋለህ?»ብሎ የሚገልፅላቸውን እንዲገነዘቡ መልካም ምኞቴ ነው።

ዮአኪም ላንግ ሐመር በ1998 እ.ኤ.እ

# መግቢያ

የደህንነትን ስዕላዊ መግለጫ ከማጥናትዎ በፊት ሀሳብዎን ወደሚከተሉት ነጥቦች ለመሳብ እንፈልጋለን::

1. ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ፍቺን የሚሰጥ አይደለም:: ነገር ግን በዚህ አስደናቂ በሆነው የመዋጀት ዕቅድ ውስጥ ያሉትን ዋናዎቹን የደህንነትን ክፍሎች እይታ የሚሰጥ ነው::
2. ማገናዘቢያው በመጽሐፉ መጨረሻ የሚገኘው የደህንነት ካርታ መግለጫ ነው:: በተቻለ አቅም የታሪኮቹን ቅደም ተከተል ዘመናቸውን ሳናዛባ ለማቅረብ ጥረት አድርገናል:: አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ካርታውን ቀንጨብ በማድረግ አቅርበናል::
3. በተቻለ አቅም መጽሐፉ በውስጡ ድግግሞሽ እንዳይኖር ታቅዶ የተዘጋጀ ነው:: ስለሆነም የደህንነትን ካርታ መግለጫዎችን በየደረጃቸው (ቅደም ተከተላቸው) እንዲያጠኗቸው እናሳስባለን::
4. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት መግለጫዎች ፍጹምና እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን በምናምነው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ዓላማ በማድረግ የተለያዩ ሀሳቦችንና ትርጉሞችን ከማቅረብና ከመነጋገር ተቆጥበናል::
5. የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአማርኛው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ እና ክጥንቱ የግሪክ መፅሐፍ ቅዱስ ነው::
6. በካርታ መግለጫ ላይ ያለው አስተያየታችን የተጠናቀቀ አይደለም:: ምክንያቱም በዚህ ትምህርት ልንረዳቸው ያልቻልናቸው ነገሮች እንዳናጠናቅቀው አድርገዋል:: መጽሐፉ እግዚአብሔር ስለ ደህንነት ያለውን ሃሳብ ግንዛቤ ለሌላቸውና ወይም ጥቂት እውቀት ላላቸው ስለዚህ ትምህርት የሚያሳውቅ ነው:: እንደዚሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ለሚያነቡና ለሚያጠኑ ተጨማሪ በረከት ይሆናል ተብሎ ታቅዶ የተዘጋጀ ነው::





## በማዳን ዕቅድ መግለጫ ካርታ ላይ ዋናው ጥያቄ
## ይህች ዓለም ምን ትሆናለች?

የሰው ልጅ በመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃን አማካኝነት በዓለም ላይ ስለሚካሄዱት ድርጊቶችና በመጨረሻው የፀጋ ዘመን ውስጥ ስለመኖሩ በቀላሉ መረዳት ይችላል:: ይህች ዓለም ምን ትሆናለች? ብለው የሚጠይቁት ብዙዎች ናቸው:: ይህን ጥያቄ አማኞች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ሰዎች በተለያየ መንገድ የሚያስበ[illegible]ና የሚያሰላስሉት ነው::

ዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨለመች ስለመሔዷ የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ በደንብ ያረጋግጥልናል:: በዚህ በያዝነው በሃያኛው ክፍለ ዘመን ብቻ የሰው ልጅ 65,000,000 ሚሊዮን ያህል ህይወት ያለፈበትን ሁለት አለቃቂ የዓለም ጦርነቶችን አሳልፏል:: የሚገርመውና የሚያሳዝነው ጦርነቱ በዚህ ብቻ አለማብቃቱ /አለመቆሙ/ ነው:: ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ 140 የሚሆኑ ወታደራዊ ግጭቶች፣ ጦርነቶች፣ ጭቅጭቆች ሲደረጉ 30 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል:: ይህን ለሚያይ ሰው በዚህ መቶኛ ክፍለ ዘመን በብዛት የሚካሄደው የነፍስ ግድያ ማብቂያ የሚኖረው አይመስልም::

በዚህ ላይ ተጨማሪ የምናደርገው በኃጢአት የተሞላ ሰው ሌላውን ሰው ለመጉዳትና ለማጥፋት የቻለው በቴክኖሎጂ ግኝቶች አማካኝነት ነው:: በፍጥነት እያደገ ያለው የኒውክለር የጦር መሳሪያ ቴክኖሎጂ ስንመለከት ዓለም ከግምት በላይ በሆነ አደገኛ ሁኔታ ላይ መድረሷን እንገነዘባለን:: በዚህ ላይ በተጨማሪ የዜና አገልግሎቶች:- ቴሌቪዥን፣ ሲኒማ፣ቪድዮ፣ጋዜጦች የመሳሰሉት በሚሰጡት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች በየጊዜው ሀፍረተ ቢስ ጨቋኞች፣ አደገኞችና የገበያ አቀራረባቸው የሰውን ጠባይና ሞራል በማበላሸት ከፍተኛ ውድቀት ላይ አድርሰውታል:: እንዲሁ ደግሞ የአካባቢው መበከል የተፈጥሮን ሁኔታ በፍጥነት እያቃወሰውና እያጠፋው ነው:: ቴክኖሎጂ በየጊዜው በተፈጥሮ ላይ እያደረሰ ያለው ተፅዕኖ፣ የሚያስፋፋው ወረርሽኝና የበሽታ ዓይነት እጅግ አሳሳቢ ነው:: ከላይ የተጠቀሱት ትዕይንቶች ሁሉ የዓለምን የወደፊት እድል ፈንታ የት ያደርሱት ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መልኩ የሚነሳ አንገብጋቢ ጥያቄ አድርገው ከፊታችን ደንቅረውታል::

እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህ ዘመን ችግሮች የሚያስደነግጡና የሚያስፈሩ ናቸው:: ይህም ሆኖ በፖለቲካ፣ በአገር አንድነትና በሳይንስ መስኮች ለዚህ ጥያቄ ምንም ዓይነት መልስና መፍትሔ አለመገኘቱና ለጉዳዩ ተጠሪ የሆኑት አዋቂዎችም አደገኝነቱን ያለመገንዘባቸው ነገር ተስፋ አስቆራጭ ሆኖአል::

### *ይህ ለምን ይሆን?*

ይህ በዓለም ላይ ያለው የመዘበራረቅ ሁኔታ በየጊዜው እየጨመረ የሄደው የሰው ልጅ ወደ እውነተኛ የህይወት ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ባለመመለሱ ነው:: ለዚህ «ይህች ዓለም ምን ትሆናለች?» ለሚለው ጥያቄ አስተማማኝ መልስ ከፈለግን በሙሉ መንፈስ ወደ ፈጠራት ፈጣሪ መቅረብ ብቻ ነው:: ይህም ሲሆን በዚህ ጥያቄ ላይ ያለንን ጉጉት ለማርካት ብቻ ሳይሆን የበለጠ ለመፍትሔው መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር ይኖርብናል::

ይህች ዓለም ከየት እንደመጣችና ወዴት እንደምትሄድ በትክክል ሊነግረን የሚደፍረው አንዱ ምንጭ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው:: ከመጽሐፍ ቅዱስ የምንማረውና የምንረዳው:-

1. እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ ነው::
2. እግዚአብሔር የዓለም አዳኝ ነው::
3. እግዚአብሔር የዓለምን ፍጻሜ የሚያመጣ መሆኑን ነው::

ዓለምን የፈጠረውና በክርስቶስ ኢየሱስ ያዳነን እግዚአብሔር ዓለምን ወደ ፍጻሜ ያመጣታል::





**በደህንነት ታሪክ ማዕከላዊና ዋና ሀሳብ የሆነው የደህንነት ካርታ መግለጫ**

## የእግዚአብሔር የማዳን ምክር

## ሐ.ሥ.20:27

***«የእግዚአብሔርንም ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና ምንም አላስቀረሁባችሁም» (ሐሥ. 20:27)***

**ከላይ የተጠቀሰውን ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረው የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በተሰናበተበት ጊዜ ነበር:: ጳውሎስ በኤፌሶን የሦስት ዓመታት ቆይታው የእግዚአብሔርን ምክር አስታውቋቸው ነበር:: የግሪኩ መሠረታዊ ትርጉም የእግዚአብሔርን ሙሉ ምክር ብሎ ይተረጉመዋል:: ይህ «ምክር» የሚለው ቃል ከ10 ጊዜ በላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጽፎ እናገኘዋለን:: ይህ «ምክር» የሚለው ቃል አስፈላጊ ወደ ሆነው የህይወት ለውጥ በሚደረግ ውሳኔ የምንጠቀምበት ቃል ነው:: ይህ ቃል በየቀኑ ለሚያጋጥሙን ምድራዊ ነገሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት የምንጠቀምበት ነው:: የእግዚአብሔር ምክር የሚያተኩረው ወደ ግል ደህንነታችን ነው:: የተጠሩት ደህንነትን ኃጢአተኞች የኃጢአት ይቅርታንና የዘለዓለም ህይወትን እንዲያገኙ ነው::**

***«ለአንዳንዶች ጌታ የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፣ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሃ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንደይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል»*** **(2ኛጴጥ.3:9)::**

***«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና»*** **(ዮሐ.3:16)::**

**የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ አስደናቂና ዘለዓለማዊ ዕቅድ ነው:: ይህም ምድር ከመመስረቷ በፊት ከነበረው ጊዜ ጀምሮ አሁን ያለችውን ምድርና የመዳኛ ጊዜ በተጨማሪም ወደፊት እግዚአብሔር የሚፈጥራቸውን አዲስ ሰማይንና አዲሲቷን ምድር ያጠቃልላል:: የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ *«በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው ሃሳቡንም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው» (ኤፌ.1:10)* የሚለውን ሃሳብ የሚያመለክት ነው:: ይህም «በሰማይና በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ ተጠቃልለው በአንድ በክርስቶስ ስልጣን ስር የሚሆኑበት ጊዜ ነው» እርሱ ሁሉንም በመስቀሉ ላይ ከእግዚአብሔር የነበረው**

መነጣጠልንና ሰውንና እግዚአብሔርን የነጣጠለ የኃጢአትን ጥልቀት ለዘለዓለም ያሸነፈ ነው።

ስለዚህ ደህንነት ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም። ምክንያቱም እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚአብሔር ለሰዎች የለጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ማንም ሌላ የለም። ማቴ1:21፤ ሐሥ.4:12 ይመልከቱ።

ዋነኛው ጉዳይ እግዚአብሔር ለእኛ የዘላለም ደህንነት የመስጠቱ ነገር ነው። ይህ ደህንነት የተመሠረተው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንደሚለው ሙሉ በሙሉ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ብቻ ነው። በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2:4 እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ያለውን ፈቃዱን ለዓለም ምስክርነቱን ይሰጣል። ቃሉም «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድሃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው» ይላል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲያውቁ ነው። ይህ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ሥጋዊ ሰው ራሱን የማዳን ኃይል የሌለው በመሆኑ ነው። በኃጢአቱ ምክንያት ሰው ደህንነት የሚያስፈልገው ሆኗል።

የሰው ልጅ ደህነትን መፈለጉ በኃጢአት ከመውደቁ ውጤት የተነሳ ነው። የመጀመሪያው ሰው አዳም ኃጢአት በመስራቱ የሰውን ልጅ ሁሉ በኃጢአት ውስጥ ጣለው (ሮሜ 5:12)። ኃጢዓትም በሰው ልጅ ላይ ሞትን አመጣበት (ሮሜ.6:23)። መሞታችን ከአዳም መምጣታችንን ያረጋግጥልናል (ይመሰክርልናል) (ዘፍ.2:16-17)። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰው ለዘላለም ስለ ጠፋ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው ደህንነት የሚያስፈልገው ሆኗል። ስለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚለው:-

1. ማንኛውም ሰው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት!
2. ማንኛውም ሰው ንስሃ መግባት ይኖርበታል!
3. ማንኛውም ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ተቀብሎ ደህንነትን ማግኘት ይኖርበታል!

ይህንንም ዕቅድ እግዚአብሔር ከዓለም መፈጠር በፊት ለእኛ ወስኖ ነበር። *«ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን። በፍቅሩም እግዚአብሔር በጎ ፈቃዱ ሆኖ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት በነፃ የሰጠን የክብር ፀጋ እንዲመሰገን ነው» (ኤፌ 1:4-5)።*
ይህ ደህንነት በተፈጸመው የክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ ላይ የተመሰረተና እኛም በእምነት የተቀበልነው ነው።





# የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

*«በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው» (ዮሐ.17:17)*

መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ቃል ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቃላት በደንብ ያረጋግጥልናል። ከዚያም በላይ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ምንጭ ናቸው። እግዚአብሔር ሰውን በራሱ እምሳያ በፈጠረ ጊዜ ለሰው ልጆች ራሱን ገልጧል (ዘፍ.1:27)።

«ይህች ዓለም ምን ትሆናለች?» ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። በአምላካዊ ሥልጣን ይህች ዓለም ከየት እንደመጣችና ወዴት እንደምትሄድ ይነግረናል። በዚህም ከዓለም ፍጥረት በፊት ምን እንደነበር፣ የአሁኑ ዓለም ምን እንደሆነና በሚመጣው ዘለዓለማዊ ዓለም ምን እንደሚሆን ይነግረናል።

መጽሐፍ ቅዱስ 40 በሚደርሱ እስራኤላውያን ሰዎች በ1600 ዓመታት ውስጥ የተጻፈ ነው። እነዚህ ሰዎች በተለያዩ የጊዜ ክፍሎችና ዘመናት ከተለያዩ የኑሮ ሁኔታዎች የመጡ ነበሩ። ይህም ሆኖ የ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት አንድነት በጣም የሚያስደንቅ ነው። በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ምሪት (መረዳት) ብቻ ላይ የተመሰረተ ነወ (2ጴጥ.1:20-21፤ 2ጢሞ.3:16-17)።

መጽሐፍ ቅዱስ የደህንነት ታሪክ መጽሐፍ ነው። በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር የደህንነት ንድፉንና ዕቅዱን ለሰው ልጅ ሁሉ ይገልጽበታል። ጠቅለል ባለ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት የመዋጀትን ዕቅድ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ያሳያሉ። ቀጥታ እነዚህ ክፍሎች በመዋጀት ዕቅድ ካርታ ላይ ከመለኮታዊ ስላሴ፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ መስመር በታች ይገኛሉ። በስተጨመረሻ ከመፅሐፉ ጋር ተያይዞ ያለውን የደህንነት ካርታ ይመልከቱ።

## 1. ብሉይ ኪዳን - የደህንነት ዝግጅት

የመጀመሪያዎቹ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እግዚአብሔር እንዴት በረጅም ጊዜ ውስጥ ይህንን የደህንነት ሥራ እንዳዘጋጀ ያረጋግጣሉ። የደህንነት ዝግጅት ሥራ ከዘፍ.3:15 ጀምሮ ከአዳም፣ ከኖህና ከሴም እስከ አብርሃም መስመሩን ይዞ ከዘር ዘር ተላልፏል። በዘፍ. ምዕ. 5፣10 እና 11 የምናነባቸው የዝርያ ዝርዝሮች የተጻፉበት ዋናው ምክንያት የማዳኑን ሥራ ወደ አብርሃም የሚመራውን መስመር ለመጠቆም ነው።

ትክክለኛው የማዳን ሥራ ዝግጅት ከአብርሃም ይጀመራል:: ከዚህ ከትልቁ የእምነት አባት አንድ ልዩ የሆነ ዘር እንዲመጣ አደረገ:: የደህንነት ህዝብ (ዘር) እስራኤል በሲና ተራራ ላይ በተደረገው ህግና ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ ሆነ ዘፀ. ከምዕራፍ 12 እስከ 24 ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር ክብር በቅድስና እንዲኖሩ ነበር:: ይህም ማለት በእስራኤል ውስጥ ማንኛውም ዓይነት የጣዖት አምልኮ እንዳይኖር ነበር:: ምክንያቱም ምንም ቢሆን የእግዚአብሔር ልጅ የጣዖት አምልኮ በሞላበት አገርና ህዝብ መካከል ከቶ ሊመጣ ስለማይችል ነው:: የጣዖት አምልኮ ሁልጊዜ ለሰይጣን የሚደረግ መስዋዕት ነው:: አረማውያን መስዋዕት የሚያቀርቡት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋንንት ነው (1ቆሮ.10:20):: ለዚህ ነው ለደህንነት ሥራ ዝግጅት የእስራኤል ህዝብ ከሌላው አህዛብ ተለይቶ በቅድስና እንዲኖር የተደረገው:: መሲሁን ለመቀበል እግዚአብሔር እስራኤልን ለኢየሱስ ስራ መረጠ:: ይኸውም «ደህንነት ከአይሁድ ስለሆነ» ነው (ዮሐ.4:22):: በዚህ ላይ አስመግባባት መፈጠር የለበትም:: የእስራኤል ነገድ (ህዝብ) ራሳቸው አዳኙን አይደሉም:: ሆኖም ግን ደህንነት ከእነርሱ መካከል የሚወጣ ነበር (ኤር. 30:21):: ይህም ጌታና አዳኝ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደህንነት እንደሚመጣ ያመለክታል ማለት ነው::

ስለሆነም ብሉይ ኪዳን ደህንነት (መዋጀት) ይመጣል ብሎ የሚያውጅ መጽሐፍ መሆኑን እንረዳለን::

## 2. አራቱ ወንጌሎች - የደህንነት መሠራት

በአራቱም ወንጌሎች በማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር ወርዶ የደህንነትን ሥራ ለእኛ ለሰው ልጆች እንደፈጸመ ተመዝግቧል:: ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ በጎልጎታ መስቀል ላይ

**«ተፈጸመ» ብሎ ጮኸ» (ዮሐ.19:30)**

በ1ኛው ቆሮንጦስ መጽሐፍ እንደተፃፈው ይህ ትልቁ የመዋጃ እውነትና የመዳናችን መሠረት ነው::

*«ከተመሠረተው በቀር ሌላ ማንም መሰረት ሊመሰርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»* (1ቆር.3:11)::

ስለሆነም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በስብዕናውና አስደናቂ በሆነው የማዳን ሥራው የማይነቃነቀው የደህንነታችን መሠረት ነው:: ይህም ማለት ኃጢዓተኞች ለመዳን ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያሟላ እርሱ ነው ማለት ነው:: በዚህ መሠረት (ዓለት) ላይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ይገነባል (ማቴ.16:18):: ስለሆነም





**የዚህ የማዳን መሠረት በአራት ምሰሶዎች ማለትም:-**

**1. ከኃጢዓት ነፃ በሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በመሆን፣**

**2. በተተኪነት በተከፈለው በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕታዊ ስቃይ፣**

**3. በክብር የተመላው የኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በመነሳትና፣**

**4. በአሸናፊነት በተሞላው የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ፣ ላይ ያረፈ ነው::**

እነኚህ አራቱ የደህንነት ምሰሶዎች የማይነጣጠሉ ናቸው:: የሚመሰረቱትም ሙሉ በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብዕናና ሥራ ላይ ብቻ ነው:: አራቱ ወንጌሎችም መሠረቱንና በክርስቶስ የሆነውን የመዳን እውነት ይገልጻሉ:: ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሠረት (ዓለት) ነው::እርሱ ብቻ ዘላለማዊ መሠረት ነው::

## 3. የሐዋሪያት ሥራ - የደህንነት መስራጨት

የሐዋሪያት ሥራ ወንጌል እንዴት ወደ ዓለም እንደተሰራጨ ይነግረናል:: 28ቱም ምዕራፎች ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመው ደህንነት እንዴት በወንጌል ስብከት እስከ ዓለም መጨረሻ እንደደረሰ በሰፊው ይገልጻሉ (ያስታውቃሉ):: ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ እንደዚህ አላቸው:-

*«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በዚያን ጊዜ በኢየሩሣሌም፣ በይሁዳ አገር ሁሉ በሰማሪያ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ»* (ሐሥ.1:8)::

ደቀመዛሙርቱና ሐዋርያቱ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የኢየሱስንና በእርሱ የተደረገውን የጎልጎታ የማዳን ሥራ መስክረዋል::

*«እኛ ግን ክርስቶስ ስለ እኛ መሰቀሉን እንመስክራለን»* (1ቆሮ.1:23)::

ይህ የተሰቀለውና የተነሳው ክርስቶስ ኢየሱስ የመሠረተው የድል ወንጌል ሞልዕክት በኢየሩሣሌም፣ በይሁዳና በሰማሪያ ባሉት ህዝብ ልብ ውስጥ ዘልቆ ገባ:: 100 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይህ ወንጌል የሮምን መንግስት ዘልቆ ገባ:: ሰሜን አፍሪክ፣ ትንሹ እስያ፣ ፐርሺያ፣ ሶሪያ፣ ሱዳንና ግብጽ ለመቶ ዓመታት የክርስቲያን አገሮች ሆኑ:: በዚያን ጊዜ መላው ዓለም በወንጌል ተሞልቶ ነበር ይህም ሊታመን የማይቻል ነበር:: እዚህ ላይ ነው የጎልጎታ ድል ትርጉም ግልጽ የሆነውና የተገለጸው:: ጠላት ሰይጣን ለአንዴና ለዘላለም የተሸነፈ ሆነ:: ለዘለዓለምም የተሸነፈ ጠላት ሆኖ ይቀራል::

ከ2000 ዓመታት ጀምሮ በክርስቶስ የተገኘው ደህንነት በመላው ዓለም እየተሰበከ ነው። ይህን እንዲሠሩ እግዚአብሔር መላዕክትን ከሰማይ ወደ ምድር አልላከም። የተፈጸመውን የደህንነት ሥራ ለሰዎች ለማዳረስ እግዚአብሔር ይህን ደህንነት በህይወታቸው በእምነት ለተለማመዱት ሰዎች አደራ ሰጠ። ለእነርሱም እንዲፈጽሙት ግልጽ የሆነውን

*«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ»* የሚለውን ተልዕኮ ሰጣቸው *(ማር.16:15)*። *«እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን» (2ቆሮ.5:20)*

*«ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ» (1ቆሮ.11:26)*።

ጌታ ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ወንጌልን የማሰራጨት ተልዕኮ የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ይሆናል። ስለሆነም የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ወንጌልን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ የማሰራጨት መለኮታዊ ተልዕኮን በጥልቀት የሚያሳይ ነው።

## 4. የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች - የደህንነት ትርጉምና መግለጫ

21ዱ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና በእርሱ የተፈጸመውን የመዋጀት ሥራና ጥልቅ የሆነውንና በክርስቶስ ያለውን የደህንነት ይዘት ይገልጻሉ። አራቱ ወንጌላት ስለ ክርስቶስ መስቀል ሲናገሩ መልዕክቶቹ ደግሞ ይህ ለምን እንደሆነ ያስረዳሉ።

*«እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቆጥርባቸውም ነበር» (2ቆሮ.5:19)*።

የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች የኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና በእርሱ የተደረገውን ለዘለዓለም ጥልቅ የሆነውን የመዋጀት ሥራን ያሳዩናል። ከዚህም በላይ እኛ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ያለንን ህብረት ያመለክቱናል። እያንዳንዳችን የአካሉ ብልትቶችና በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ደግሞ አካሉ መሆናችንን ያሳዩናል (ኤፌ. 1:23 እና ኤፌ.5:30)። ምስጢሩ፣ ጥሪውና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል መሆኗን ሐዋሪያው ጳውሎስ በጻፋቸው መልዕክቶች ልዩ በሆነ መንገድ ተገልጧል።

በተጨማሪም እነዚህ መልእክቶች በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ደህንነታችንን በእምነት «በፍርሀትና በአክብሮት ተግታችሁ ሥሩ» (ፊል.2:12) እንደዚሁም በውስጣችን ያለውን ኃጢአት ድል እንድናደርግ «እንዲሁም እናንተ ደግሞ





ለኃጢዓት እንደ ሞታችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ» (ሮሜ.6:11) «ክርስቶስ በእናንተ እስኪሳል ድረስ...» (ገላ.4:19፤ ኤፌ.4:15-16) በማለት ደህንነታችንን በጥንቃቄ እንድንፈጽም ያስተምሩናል።

ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን ደህንነት በእምነት ካልተቀበለ በስተቀር በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የደህንነት ትርጉም (ምንነት) መረዳት አይችልም። አማኝ ብቻ ነው ወደዚህ የደህንነት ሙላት የሚገባው ስለዚህ ምክንያት ነው ሀያ አንዱ መልዕክቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት አማኞች በቅድምያ የተጻፉት። አዳኙ ጌታ «መጽሐፍትን መርምሩ» (ዮሐ.5:39) በማለት አማኞችን አዝዟል።

የቤሪያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህን ትዕዛዝ «መጽሐፍትን በመመርመር» በትክክል መንገድ ታዘዙት (ሐሥ.17:11)። ዛሬም ቢሆን እኛ ፍጹም የሆነውን መለኮታዊ የማዳን ሥራ ለመረዳትና ለመገንዘብ ያላቋረጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ልናደርግ ይገባናል።

## 5. ራዕይ የደህንነት /የመዋጀት/ መፈጸም

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ ነው (ራዕ.1:1)። ይህ መጽሐፍ ደግሞ የዮሐንስ ራዕይ በመባል ይጠራል ራዕዩ የተሰጠው አንድ ጊዜ በኢየሱስ ደረት ላይ ጠጋ ብሎ ወደነበረው ወደ ሐዋሪያው ዮሐንስ ነው (ዮሐ.13:23፣ 21:20) በአዲስ ኪዳን ብቸኛ የትንቢት መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ዋና መልዕክት እንዴት እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነትን እንደፈጸመና እንደሚፈጽም ማሳየት ነው። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣው መሲህ፣ የዓለም ፈራጅና የሁሉ ፈጻሚው (ሙላት) መሆኑ ራሱ ገልጿል።

*«አብ በማንም ላይ አይፈርድም ነገር ግን የፍርድን ሥልጣን ሁሉ ለወልድ ሰጥቶታል» (ዮሐ.5:22)*። ይህም ማለት አሁን ንስሐ ለሚገቡት ኃጢአተኞች አዳኝ መድሃኒት የሆነው ያው ጌታ አምላክ-የለሽ በሆኑት ላይ ለመፍረድ ይገለጣል ማለት ነው። በህይወታቸው ሳሉ በኢየሱስ የሚገኘውን ደህንነት ያጣጣሉ ሁሉ ለዘለዓለም ይጠፋሉ። የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ኢየሱስን «በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ የሚንበረከኩለት» ብቸኛ ገዢ አድርጎ ያቀርበዋል (ፊል.2:10)።

ከብዙዎች አስቃቂ ከሆኑት እግዚአብሔር-የለሽ ህዝቦች ላይ ከሚወርደው ፍርድ ሌላ ራዕይ ደህንነት እንዴት አድርጎ ከአዲስ ሰማይና

ከአዲስ ምድር ጋር እንደሚጋጠም ያሳያል (ራዕ.21:1)። ከዚያ በኋላ ነው የእግዚአብሔር የደህንነት እቅድ ተሟልቶ ለፍጻሜ የሚደርሰው።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ

እስካሁን በተሰጠው መግለጫ እንዳየነው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ በሆነና ሊታይ በሚችል መልኩ የደህንነትን ይዘት የዘረዘረ መጽሐፍ ነው። ይኸውም፡

***ከዘፍ. 1 - እስከ 11***

የዓስም ታሪክ መግለጫ፣ ፍጥረት፣ የሰው ውድቀት፣ የጥፋት ውሃ፣ የባቢሎን ግንብ ግንባታ

***ከዘፍ.12 እስከ - ሐዋ.12***

የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ታሪክ ከእሥራኤል ጋር ከአብርሃም ጀምሮ በክርስቶስ መጨረሱ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነትን በጎልጎታ መስቀል ላይ መፈጸሙ

***ከሐዋ. 13 እስከ - ዮሐ.ራዕይ 3***

እስከ ዓሰም ዳርቻ ድረስ (መጨረሻ ድረስ) የማዳን ሥራ መሰራጨት፣ የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከአይሁዶችና ከአረማውያን በተውጣጡ መሰብሰብ

***ከራዕ. 4 እስከ 22***

በምድር ላይ የሚወርደው የፍርድ ጊዜ የማዳን ሥራ መፈጸም፣ የኢየሱስ እንደገና መምጣት፣ የመጨረሻ ቀን ፍርድ፣ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር





## መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ የሆነውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ይገልጻል

ከላይ እንደተመለከትነው ሁሉ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ በአምስት ንውሳን ክፍሎች ይከፈላሉ ይኸውም፡-

1. የደህንነት ዝግጅት፣
2. የደህንነት ሥራ እርግጠኝነት፣
3. የደህንነት መስፋፋት፣
4. የደህንነት ትርጉም፣
5. የደህንነት መፈጸም።

እጅግ ጥልቅ የሆነውን የመስኮታዊ ደህንነት ሥራ በዚህች ምድር ላይ ማንም ሙሉ በሙሉ ሊለካውና ሊረዳው አይችልም። ጥልቅ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የእግዚአብሔርን የደህንነት ሥራ የሰው ልጆች በሁለት ጉዳዮች ሊገነዘቡ ይችላሉ።

1. የእግዚአብሐር ማዳን «ስእኛ»
2. የእግዚአብሐር ማዳን «በእኛ ውስጥ»

«የእግዚአብሔር ማዳን ስእኛ» በ12 ቲዮሎጂያዊ (ሥነ-መስኮታዊ) አከፋፈሎች ሊጻፍ (ሊገለጽ) ይችላል።

በዚህ ላይ የምናየው የደህንነት መፈፀም በሰዎች ማመንና አለማመን ላይ የተመረኮዘ ያስመሆኑን ነው።

አብዛኛውን የሰው ዘር እግዚአብሔርን ባለማመንና በእግዚአብሔር ላይ ጠላትነታቸውን በመግለጽ ይሄዳሉ። ይህም ሲሆን ስሰው ልጆች የሆነው ደህንነት የማይለወጥ ሆኖ ይኖራል። ነገር ግን ልክ አንድ ሰው በእምነት ወደ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ ይህ እውን የሆነው ደህንነት በእውነት ይገልጻል። ይህም ማለት ኃጢአተኝነቱን አምኖ ንስሐ የገባው ሰው በእግዚአብሔርና በኢየሱስ በማመኑ የእግዚአብሔርን ሙሉ ደህንነት ይቀበላል ማለት ነው። ይህ ልዩ የሆነ አስደናቂ ልምምድ «የእግዚአብሐር ደህንነት በእኛ ውስጥ» የሚለው በ12 (ስነመስኮታዊ) ሀሳቦች ሊከፋፈል ይችላል። ህያ አራቱ ዋና ሀሳቦች በሚቀጥለው ቻርት ላይ ባጭሩ ተጠቃልለው ይገኛሉ።

ለማንኛውም ሰው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ለማዳን የወጣውን የሥዕላዊ መግለጫ የማዳን ዕቅድ ለመመርመር የሚፈልግ ሁሉ እነዚህ ባጭር የተገለጹት ሃሳቦች እርዳታ ይሰጣሉ።

## የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ

## በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

### የእግዚአብሔር ማዳን «ለእኛ»

1. የእግዚአብሔር የማዳን ምክርና ዕቅድ
(ሐሥ.20:27)
2. የእግዚአብሔር የማዳን ፍላጎት በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ
(ዕብ.10:5-7፤ ኤፌ.1:5)
3. ከዓለም ፍጥረት በፊት ለደህንነት መመረጥ
(ኤፌ.1:4-5)
4. በኃጢአትና በሰው ውድቀት ምክንያት የደህንነት አስፈላጊነት
(ሮሜ.3:23፣ 5:12)
5. የማዳን ተስፋ በኢየሱስና በእርሱ ሥራ
(ዘፍ.3:15)
6. የደህንነት ታሪክ ከእሥራኤል ህዝብ ጋር
(በዘፍ.12:1) ጀምሮ
7. በእስራኤል ታሪክ ለደህንነት ዝግጅት
(ዮሐ.4:22)
8. የደህንነት አገር የእሥራኤል ምድር
(ዘፍ.12:1)
9. የደህንነት ህዝብ የተመረጠው የእሥራኤል ነገድ
(ዘፍ.12:2)
10 የደህንነት ጊዜ – የዘመኑ ፍጻሜ በደረስ ጊዜ
(ገላ.4:4)
11. በአራቱ ወንጌሎች የተፈጸመው የደህነት ሥራና እውነት
(ዮሐ.19:30)
12. የደህንነት መሠረት የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ
(1ቆሮ.3:11)





## የተፈጸመው የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ

## በልጁ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ

### የእግዚአብሔር ማዳን «በእኛ ውስጥ»

1. የደህንነት ለዓለም ህዝብ ሁሉ መሠራጨት
(የሐሥ. 1: 1 -28)
2. መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ በማንበብ የሚገኘው
የደህንነት ፍቺ መገለጥ (ዮሐ.5:39)
3. የደህንነት ይዘት፣ ኢየሱስና የእርሱ ሥራ
(ዮሐ.14:6፤ ሐሥ. 4:12)
4. ደህንነትን በእምነት ስለመቀበል
(ሮሜ.3:21-31)
5. በክርስቶስ ላመነው አማኝ የመዳን እርግጠኛነት
(ሮሜ.4:1-25)
6. በመንፈስ ቅዱስ ምሥክርነት ደህንነት እርግጠኛ ሆኗል።
(ሮሜ. 8:16፣ 38፣ 39)
7. የደህንነት ደስታ በተዋጁትና በዳኑት ዘንድ
(ሮሜ.14:17፤ ፊል. 4:4)
8. አማኝ የሚያድግበት የደህንነት እውቀት
(2ኛ ጴጥ.3:18)
9. የቅድስና ህይወት ለመኖር የደህንነት ተጋድሎ
(ሮሜ.6:1-7፣25)
10. ደህንነትን በተቀበሉና በዳኑ የደህንነት አዋጅ መደረግ
(2ቆሮ.5:20)
11. በእውነት ለዳኑት የመዳናቸው ያለመናወጥ
ደህንነት (ሮሜ.3:1-39)
12. በእውነት ለዳኑት የደህንነት መፈጸም
(ፊል.1:6)

ዘፀት.3:14

*ዘፍ. 1 እና 2 ያለ ኃጢአት*

*በመጀመሪያ*

*እግዚአብሔር*

*ሰማይንና*

*ምድርን*

*ፈጠረ::*

*ዘፍ. 1:2*

## ሁለቱ የእግዚአብሔር የማዳን ታሪክ አዕማዶች

# አልፋና ኦሜጋ

### Ā እና Ω

በእግዚአብሔር የማዳን ሥዕላዊ መግለጫ ላይ «Ā» እና «Ω» ፊደሎች ከቀኝና ከግራ ተጽፈው ይገኛሉ:: አልፋና ኦሜጋ ሁለቱ የግሪክ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደላት ናቸው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልፋና ኦሜጋ ከሚለው ገለጻ በስተኋላ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ትርጉም አለው:: በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሙሴ በሚነድ ቁጥቋጦ ውስጥ:-

*«ያለና የምኖር እኔ ነኝ »* (ዘፀ.3:14)

በአዲስ ኪዳን ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በነበረበት ጊዜ ጌታ:-

*«ያለውና የነበረው የሚመጣው ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ኦሜጋ የመጀመሪያውና የመጨረሻው እኔ ነኝ»* (ራዕ.1:8)

እነዚህን ሁለት ጥቅሶች ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው:: ዘለዓለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን መገለጽ ይናገራሉ:: ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር ነው (መዝ. 90:2) ያም ማለት እርሱ ብቻ ዘለዓለማዊ ነው ማለት ነው:: እርሱ ከዓለም ፍጥረት በፊት ዘለዓለማዊ ነው:: እንዲሁም:-





## መጀመሪያና መጨረሻ

እግዚአብሔር የደህንነት ሥራውን በአስደናቂ ቃል ይጀምራል::

*«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»* (ዘፍ.1:1)::

የመጀመሪያው ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ስለ ዓለም መፈጠር ይናገራሉ:: በዕብራውያን መልዕክት እግዚአብሔር ዓለምን ከማይታየው እንደፈጠረ ተጽፏል:: «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ የምንረዳው በእምነት ነው ስለዚህ የሚታየው ነገር ሁሉ ከማይታየው እንደተሰራ እናውቃለን» (ዕብ.11:3)::

ይህም ማለት ከዓለም ፍጥረት በፊት እግዚአብሔር ብቻ (አብ፣ ወልድ፣መንፈስ ቅዱስ) ነበሩ:: ፍጥረት ሁሉ በሚቻለው ቃሉ ከማይታየው ወደ መሆን መጣ ከዘለዓለም ወደ ጅማሬ መጣ እርሱ ሲተናገረው ተፈጠረ በትዕዛዙም ሁሉ ነገር ተመሥርቶ ታየ:: መዝ.33:9

የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ በአዲሱ ሰማይና በአዲስ ምድር የሚፈጸመው ስለዚህ ነው::

«አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ» ራዕ.21:1

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች የአዲስ ሰማይና የአዲስ ምድርን መፈጠር ይገልጻሉ::

### ኃጢዓት የሌለባት አለም

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹና የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች በአንድ ነገር የተለዩ ናቸው:: በዘፍ.1 እና 2፤ በራዕ. 21 እና 22 ከኃጢአት ነፃ ስለሆኑት ዓለም ይገልጻሉ:: እግዚአብሔር ዓለምን

ራዕ. 1:8

*ራዕ.21 እና 22 ያለ ኃጢአት*

አዲስ

ሰማይና

አዲስ

ምድር

አየሁ

*ራዕ.21*

*እና*

*22*

ውብና ድንቅ አድርጎ ነበር የፈጠረው:: የፈጠረው ሁሉ መልካም ነበረ (ዘፍ.1:31):: የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም በሆነ ሕብረት የኖሩና ኃጢዓት የሌለባቸው ነበሩ ኃጢዓት በሌለበት ዓለም የኖሩና በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል ምንም ኃጢዓት ያልታየ ነበር:: ይህ ኃጢዓት የሌለበት ዓለም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የራዕይ ዮሐንስ ምዕራፎች ተገልጿል::

እግዚአብሔር የደህንነትን ሥራ ሲጨርስ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን ይፈጥራል:: በዚያም በአዲሱ ዓለም ኃጢዓትም ሆነ ሞት አይታይም:: ይህ ሞትና ኃጢዓት የሌለበትን ዓለም የመጨረሻዎቹ ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ያሳዩናል::

**የጅማሬውና የፍጻሜው አንድ መሆን**

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹና የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች እርስ በርስ ሲነፃፀሩ ዘለዓለማዊና ጸንተው እንደሚኖሩ ምሰሶዎች ይመስላሉ:: የዘመናትና የሰው ልጆች ታሪክ በእነዚህ ሁለት ግዙፍ ምሰሶዎች መካከል ይገኛሉ:: ማንኛውም ሰው ኃጢዓት፣ ጥፋት፣ ስቃይና ሞት ወዳለበት ዓለም ይወለዳል::

ክፋትንና ኃጢዓትን ወደ ዓለም ያመጣው ሰይጣን ነው (ዘፍ.3) «በኃጢዓት ምክንያት ደግሞ ሞት መጣ»:: ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአትን ስለ ሠራ ነው (ሮሜ. 5:12)::

የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰውን ዘር ለመዋጀትና ለማዳን ሁሉን ነገር እንዳደረገ ያሳየናል:: እግዚአብሔር የደህንነትን ዕቅድ ያዘጋጀው በብሉይ ኪዳን ጊዜ ነበር:: በደህንነት ታሪክ እግዚአብሔር ልጁን በመስጠቱና በመላኩ የዕቅዱን ግብ የመታ ሆነ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደህንነት ሥራውን በቀራንዮ መስቀል ላይ ፈፅሞ እኛን ከኃጢዓት፣ ከሞትና ከዘለዓለም ጥፋት አዳነን:: ሰው ደህንነት የሚያገኘው በጌታ ኢየሱስ ሲያምንና እምነቱን ሲገልጽ ወይም ሲያውጅ ነው::





# የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ መካከለኛ /እምብርት/

# የጎልጎታው መስቀል


*«ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»* (1ቆሮ.3:11)::

በትልቁ የእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ ዕምብርት ሆኖ የቆመው የጎልጎታው መስቀል ነው:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የእግዚአብሔር ልጅ ለጠፋው የሰው ዘር ኃጢዓት የሞተው እዚያ ነው:: የጎልጎታው መስቀል የእግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ ያተኮረበት ነጥብ ነው:: የመዋጀት ብርሃን ከዘላለም እስከ ዘላለም ከዚህ ያንጸባርቃል::

ጌታ ኢየሱስ በስብዕናው በዚህች ምድር ላይ በኖረበት ጊዜ ነው የጎልጎታው መስቀል በምድር ላይ የተተከለው:: እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የዓለምን ኃጢዓት እንዲሸከም የእግዚአብሔር በግ አድርጎ ያዘጋጀው::

*«ዓለም ሳይፈጠር እንኳን አስቀድሞ የታወቀ ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ ከእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ከሙታን ባስነሳው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ»* (1ጴጥ.1:20)::

ስለሆነም ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ነበር:: በመጨረሻ የመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፍ በዮሐንስ ራዕይ ጌታ ኢየሱስ የተገለፀው «በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም» የተገባው የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ነው:: (ራዕ.5:13)



የእግዚአብሔር ልጅ የእግዚአብሔር በግ በመሆን ለዘላለም ይኖራል (ራዕ.5:13):: ይህ እውነት በመጀመሪያ ግልጽ የሆነው አዳኙ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ ነው:: ስለዚህ የተሰቀለው የክርስቶስ መልዕክት ሁልጊዜ ትኩረት የሚደረግበት አብይ ነገር ነው::

በመጀመሪያው የሐዋሪያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች *«እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን»* ብሎ ይፅፋዋል (1ቆሮ.1:23)::

## የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ

ብሉይ ኪዳን በአጠቃላይ በሚሰቀለው ክርስቶስ ላይ ሲያተኩር:: አዲስ ኪዳን ደግሞ በመስቀል ላይ በሞተው የዓለም አዳኝ በሆነው ላይ ወደኋላ በማየት ያተኩራል:: ስለሆነም የተሰቀለውን ክርስቶስን የማይሰብክ እርሱ ሐሰተኛ ሰባኪ፣ ሐሰተኛና ውሸታም ነብይ ነው::

በዓለም ውስጥ ብዙ ሰዎች ስለ «እግዚአብሔርና» ስለ «ኢየሱስ» ያወራሉ:: በቤተ ክርስቲያንም መድረኮች ብዙ ይሰበካል ቢሆንም የሚሰበከው ፍጹም የተሟላ አይደለም:: ምክንያቱም ብዙ ጊዜ አስፈላጊው ነገር ስለሚተው ነው:: እውነተኛ ደህንነት የሚገኘው በእርሱ ብቻ ነው (ሐሥ.4:12):: ስለዚህ ነው ጠቅላላ ዘለዓለማዊ ሃሳብ በተሰቀለው በክርስቶስ ላይ የሚያተኩረው:: በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ እምብርት የተሰቀለው ክርስቶስ ብቻ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ ይቆማል /ይኖራል/::

### «ተፈጸመ!»

በዮሐ.19:30 የሚገኘው ይህ ቃል በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ሥራ ውስጥ መካከለኛ (እምብርት) ነው በጎልጎታ የደህንነት ሥራ ተፈጽሟል:: ይህም ማለት ማንም ሰው አንዳች የማይጨምርበት የመስኮት ሥራ ነው:: የእኛም የአማኞች የራሳችን ሥራ የተጣለ ነው:: እንደ እግዚአብሔር ልጆች ክርስቶስን ልንከተለውና በእምነት ልናድግ ይገባናል:: ዓለምን ልንክድና በቅድስና ልንኖር ይገባናል:: ይህንንም ልናደርግ የምንችለው በጎልጎታ የማዳን ሥራ መሠረት ብቻ ነው:: ይህ ሥራ በእኛ ሳይሆን በጌታችንና በአዳኛችን የተፈጸመ ነው::

ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለናል ተሰቅለንም እንኖራለን (ሮሜ6:6):: ማንም ሰው ራሱን መዋጀት አይችልም:: በክርስቶስ ኢየሱስ ጎን የተሰቀለው የነፍስ ገዳይ ሰው ታሪክ እንኳን ይህንን ግልጽ በሆነ መንገድ ያስተምረናል:: ይህ ሰው ንስሐ ገባ የጌታችንን ስም ጠራ ጌታም «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ብሎ ተናገረው (ሉቃ. 23:43)::





ይህ ሰው እጆቹና እግሮቹ በመስቀል ላይ በሚስማር ስለተቸነከሩ ምንም ማድረግ አይችልም ነበር:: እጆቹን ማጠፍም ሆነ መጠመቅ አይችልም ነበር አዳኙ በገነት እንደሚሆን ተስፋ ሰጠው:: እኛም በዚህ ጊዜ ደህንነትን ልንቀበልና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ልንሞት እንችላለን:: ደህንነትን ስናገኝና አዳኙን በልባችንና በህይወታችን በእምነት ስንቀበል አዲስ ህይወት በእኛ ይጀምራል:: ስለዚህ በኋላ ራሳችንን ለጥምቀት እንሰጥና አማኞች በመሆን እንካፈላለን:: ሕብስቱና ወይኑ የጎልጎታን ሥራ የሚያስታውሱን ማዕድ ናቸው (1ቆሮ.11:24-25)::

## ከክርስቶስ በፊት – ከክርስቶስ በኋላ

ጎልጎታ በዓለምና በማዳን ታሪክ እምብርት ላይ ይገኛል:: ከዚህም የተነሳ ነው ታሪካዊ ድርጊቶችን ለማመልከት ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በማለት የምንጠቀመው:: የእግዚአብሔር ጠላቶች እንኳን ይህን የጊዜን አቆጣጠር ለመጠቀም የተገደዱ ሆነዋል:: ይህም ታላቅ የሆነውን የማዳን ሥራ ከዓለም ላይ ለማጥፋት እንደማይቻል ግልጽ ያደርገዋል:: በአምስቱ የዓለም አህጉሮች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በተሰቀለው በክርስቶስ ኢየሱስ እያመኑ ይከተሉታል:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በጎልጎታ መስቀል ላይ የተፈጸመው የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ የማያጠራጥር የታሪክ መሠረትና ነጥብ ነው::

### ሦስቱ መለኮታዊ መስመሮች የሚመስሉት

## የአምላክ ሦስትነት /ሥላሴ/

እግዚአብሔር መካከለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ነው:: ነገር ግን እኛ ሰዎች በዙሪያችን የሚዞረውን ተፈጥሮ በመመልከት ራሳችንን መዓከላዊ በማድረግ የፍጥረተ-አለም መካከለኛ የሆነውን እግዚአብሔርን እንዘነጋለን:: በእውነትም እግዚአብሔር ለፍጥረተ-ዓለም መዓከላዊ ነው::

*«ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና» (ሮሜ.11:36)::*

እግዚአብሔር የማይታይ ነው ስለዚህም በአይንና በህሊና እርሱን መሳል (መቅረጽ) አይቻልም:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር ቃል ተከልክሎአልና:: ስለዚህ ጉዳይ ሙሴ በጌታ መንፈስ ተመርቶ «በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው፣ በታችም በውሃ ካለው ነገር ማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ጣኦት አድርገህ አትስራ» (ዘፀ.20:4):: በማለት ስለፃፈ እግዚአብሔርን በምንም ነገር መስለን ልንገልጠው አልተፈቀደልንም::

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር አብ (አባትነት)**

*«እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ።»* (ዮሐ.20:17) በማለት ይናገራል።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ወልድም**

*«እነሆ ድምጽ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው»* በማለት ይገልፃል (*ማቴ.3:17*)።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይናገራል**

*«አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ፣ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል»* (ዮሐ.14:26)።

በዚህም አንዱ እምላክ ራሱን በሦስትነት መግለጹን እንገነዘባለን። *ሥነ-መለኮታውያን /የመጽሐፍ ቅዱስ እጥኚዎች/* የእምላክን ሦስትነት ለመግለጽ በሥነ-መለኮታዊ ቋንቋ ስላሴ የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። ይህንን በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ለመግለጽ ሞክረናል። በሁለቱ ታላላቅ ርዕሶች ሥር እነዚህን ሦስት መስመሮች እናገኛለን። ከእነዚህ ሦስት መስመሮች ብርቱካንማ የሆነው የመጀመሪያው መስመር እግዚአብሔር አብን ያመለክታል፣ ቡናማ የሆነው የመካከለኛው መስመር ደግሞ እግዚአብሔር ወልድን ሲያመለክት ከስር ያለው አረንጓዴው ደግሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያመለክታል።

እነዚህ ሦስቱ የመለኮት መግለጫ መሰመሮች በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስ በመላው ዓለምና በሰዎች ታሪክ የበላዩን ሥፍራ እንደያዙ ግልጽና ጉልህ ያደርጉታል።

**አብ** ዮሐንስ 10.29 ኤፌ 3,14.15; 4,6

**ወልድ** 1ኛ ጴጥ 1,18-21 ዕብራ 1,2.3 ዮሐ 1,1-18

**መንፈስ ቅዱስ** ዮሐ 16,7-15 ሮሜ 8,2.9,14-16





**1. ብርቱካንማው መሥመር፣ /እግዚአብሔር አብ/**

*«ስለዚህ ምክንያት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ» (ኤፌ.3:14፣15)*።

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ካርታዊ መግለጫ ላይ እግዚአብሔር አብን የሚያመለክተው በብርቱካንማ ቀለም ተለይሞ ያለማቋረጥ በቀጥታ ከግራ ወደ ቀኝ ይሄዳል። በዚህ መሥመር እግዚአብሔር አብ ሁልጊዜ በሰማይ ያለና የሚኖር መሆኑን ለመግለጽ እንፈልጋለን። «ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም» እርሱ አምላክ ነው (*መዝ.(90):2*) ። በዮሐንስ ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ ስለዚህ እውነት እንዲህ በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል።

*«መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም። በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» (ዮሐ.1:18)።*

ስለሆነም በልጁ ብቻ ነው አብን የምናውቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን (አብን) ለእኛ ገልጾልናል «እኔን ያየ እብን አይቷል» ያለው እርሱ ብቻ ነው (*ዮሐ.14:9*)። እግዚአብሔር አብ እስከ አዲሱ ሰማይና ምድር መፈጠር ሳይታይ ይኖራል (*1ጢሞ.6:15-16*)።

**2. ቡናማው መሥመር - /እግዚአብሔር ወልድ/**

**ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ለመኖሩ**

*«ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ» (1ጴጥ.1:20) ከሚለው ጥቅስ እንረዳለን።*

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቡናማው መስመር የእግዚአብሔርን ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል። ከዘላለም ዘመናት በፊት ክርስቶስ እምላክ ነበር። እግዚአብሔር እብ ከቶ ክርስቶስን አልፈጠረውም። ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው። *«እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ.10:30)* ብሏልና። ስለሆነም ጌታ ኢየሱስ ዘለዓለማዊው ልጅ ነው ልክ እንደ አብ ከዓለም ፍጥረት በፊት ለዘለዓለም ነበር። በሥነ-መለኮት ጥናት ይህ እውነት «የኢየሱስ እስቀድሞ መኖር» በሚል ይገለጻል። *«አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» (ዮሐ.17:5)*

## የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መገለጥ /ሰው መሆን/

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መግለጡን ያስተምረናል:: *«ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» (ገላ.4:4)*:: እኛን ለማዳን ከድንግል ማሪያም በመወለድ ወደዚህች ወደ ተረገመች ዓለም ገባ::

*«ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ:: አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐ.1:14)*::

በካርታው ላይ የኢየሱስ መሆንን በሚያመለክተው መስመር ላይ በሚሄደው ቡናማ ቀለም መስመር የተገለጠው ነው:: በዚህ ቀጥ ባለው መስመር መጨረሻ ላይ ያለው ትንሹ ቀስት የእግዚአብሔር ልጅ በመጣ ጊዜ በእርሱ በኩል ሰማይና ምድር እርስ በርሳቸው መገናኘታቸውን የሚያሳይ ነው አምላክ በልጁ በኢየሱስ በኩል ሰው መሆኑ በምንም ሊገመት የማይቻል ድንቅ ነው:: የማይሞተው እግዚአብሔር ወልድ ለመሞት ይችል ዘንድ እንደ እኛ ሰው መሆን አስፈለገው:: ጌታ በሞት ላይ ባለድል መሆን የሚችለው በሞቱ በኩል ብቻ ነበር *(ዕብ.2:14-15)*::

## የኢየሱስ ክርስቶስ የመዋጀት ሥራ

የእግዚአብሔር ልጅ ለሰላሳ ዓመታት በዚህች ምድር ላይ ታዋቂ ሳይሆን ኖረ:: ከዚህ ጊዜ በኋላ በሕዝብ ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ መሲሂ ሆኖ በመታየት የአባቱን ክብር በእግዚአብሔር ልጅነቱ ገለፀው *(ሉቃ.3:23)*::

*«ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው:: የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው፣ ቃልህንም ጠብቀዋል» (ዮሐ.17:6)*::

*«የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ ሆኖ*:: */ዮሐ.1:29* NIV/ የደህንነትን ሥራ በመስቀል ላይ ፈጸመ ስለ ኃጢአታችን ሞተ:: ስለዚህ ነው ቡናማው መሥመር በማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ በቀጥታ በመስቀሉ መካከል የሚያልፈው:: በመስቀሉ መካከል «ተፈጸመ» የሚለው አስደናቂ ቃል ተጽፏል:: *(ዮሐ.19:30)*

## የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

የእግዚአብሔር ልጅ የሞትን ኃይል የወሰደውና ለአንድ ጊዜና ለዘለዓለም በሞት ላይ ድልን የተቀዳጀው በትንሳኤው በኩል ነው:: ጌታ በኋላ በድል ትንሳዔው





በኩል የሚፈፅመውን ይኸንንም ሥራ ቀደም ብሎ በአልአዛር መቃብር በአስደናቂ ቃላት:-

*«ትንሣኤና ሀይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያውም የሆነው የሚያምንብኝ ለዘለዓለም አይሞትም. . .» (ዮሐ. 11:25-26)* በማለት ተናግሮት ነበር::

የክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ያለ ትንሣኤው ሙሉ አይሆንም ነበር:: ከዚያም የተነሳ የኃጢአታችንን ሥርየት ልንቀበል አንችልም ነበር:: ነገር ግን ለዘላለም በሞት ተገዢ እንሆን ነበር:: ስለዚህም ነው ትንሣኤው የመዳንን እውነት በአድናቆት የተፈጸመ ሥራ ያደረገው:: ይህንንም:-

*«እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፣ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስን ነበር:: በህይወታቸው ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ፣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» (ዕብ.2:14-15)*:: በማለት የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ ያቀርበዋል::

## የኢየሱስ ክርስቶስ እርገት

ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ከደብረ ዘይት ተራራ ወደ ሰማይ አረገ:: ደቀ መዛሙርቱ *«እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» (ሐሥ.1:9)*::

የኢየሱስ ክርስቶስ እርገት በሥዕላዊ መግለጫ ላይ ከፍ ብሎ በሚወጣው ቡናማ ቀለም የተገለጠ ነው:: በማቴ. 24:30 እንደተፃፈው ሁሉ «በኃይልና በታላቅ ክብር» ወደ ምድር እስከሚመለሰበት ጊዜ ድረስ «በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል» *(ሉቃ.22:69)*: የዕብራውያን መልዕክት የክርስቶስን በአብ ቀኝ መቀመጡን ይገልፃል::

*«ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» (ዕብ.1:3)*::
*«እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቁ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን ኃይማኖታችንን እንጠብቅ» (ዕብ.4:14)* በማለት አቅርቦታል::

## የኢየሱስ ክርስቶስ የሊቀ ካህናትነት አገልግሎት

በሰማይ ክርስቶስ ለእርሱ ለተገቡት ሁሉ ሊቀ ካህናት ነው::
*«ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፣ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን::» (ዕብ.8:1)*

*«ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፣ እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ዮሐ.2:1)::*

ዳግም የተወሰዱ አማኞች በሙሉ ዘላለማዊው ሊቀ ካህናት ስለ እነርሱ መማለዱን ሊያውቁ ይገባቸዋል:: ምክንያቱም *«ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና»* ተብሎ ተጽፏልና (*ዕብ.7:25*)::

**የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ**

የክርስቶስ *የመጀመሪያ መምጣቱ* /በመዋረድ/ ነበር:: *አመጣጡንም* ጳውሎስ «በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት የታዘዘ ሆነ» (*ፊል.2:8*) በማለት ይገልፀዋል:: በአንፃሩ ደግም ዳግም ምጽዓት «በኃይልና በታላቅ ክብር» ይሆናል (*ሉቃ.21:27*):: ነቢዩ ዘካሪያስ ይህን ታላቅ ሁኔታ «በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሣሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረዘይት ላይ ይቆማሉ» (*ዘካ.14:4*) ብሎታል:: የእግዚአብሔር ልጅ አንድ ጊዜ እንደገና በዚህች ምድር ላይ ይቆማል:: *በራዕ.20:6 መሠረት መሲሃዊ* የሰላም መንግስቱን ይመሠርትና በዚህች ምድር ላይ ለሺህ ዓመት ይገዛል:: የክርስቶስ ዳግም መምጣት በካርታው ላይ ወደታች በሚወርደው ቡናማ መስመር የተገለጸ ነው:: መስመሩ በመሲሁ የሠላም መንግሥት ያልፍና በቀጥታ ወደ «አዲስ ሰማይና ምድር» ያመራል (*ራዕ.21:1*)::

**3. አረንጓዴው መሥመር - እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ**

በማዳን ሥዕላዊ መግለጫ ላይ መንፈስ ቅዱስ በአረንጓዴ መስመር የተገለጸ ነው:: እርሱም እንደ አብና እንደ ወልድ ዘለዓለማዊ አምላክ ነው::

*«እኔም አብን እለምናለሁ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፣ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው:: ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፣ ውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ» (ዮሐ.14:16-17)::*

ጌታ ኢየሱስ ይህን ተስፋ ለደቀ መዛሙርቱ ሲሰጥ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ወደ ምድር አልመጣም ወይም አልወረደም ነበር:: ምክንያቱም ኢየሱስ ገና ስላልከበረ ነበር (*ዮሐ.7:39*):: መንፈስ ከአብ ዘንድ ከሰማይ ወደ ምድር አልመጣም ነበር፣ ምክንያቱም ክርስቶስ ወደ አባቱ መመለስ ነበረበትና::*«እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ»* (*ዮሐ.16:7*) ብሏልና:: ስለዚህ ክርስቶስ በመጀመሪያ ስለ ኃጢዓታችን መሞትና እኛን በደሙ መስዋዕትነት ከአባቱ ጋር ማስታረቅ ነበረበት:: ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህናት በመሆን ወደ ሰማይ አረገና በመዋጀት ሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ስለ እኛ ሊታይ ቀረበ (*ዕብ.9:12-26*):: ከዚህ በኋላ ነበር እንደ ተስፋ ቃሉ መንፈስ ቅዱስ መውረድ የነበረበት::





ስለዚህ ነው የሐዋሪያት መልዕክት በተሰቀሰውና በተነሳው በክርስቶስ ላይ ያተኮረው:: በሰው ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚያድረው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ሲታጠብ ብቻ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት፣ መቀበር፣ መነሳትና ማረግ ስመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ተቀዳሚና አስፈላጊ ነገር ነበር::

**የቤተ ክርስቲያን መመሥረት**

ከኢየሱስ ዕርገት ከአሥር ቀን በኋላ መንፈስ ቅዱስ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ወደ ምድር መጣ:: ይህንንም:-

*«ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ:: ተቀምጠው በነበሩበትም ቤት ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፣ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው:: በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር:: (ሐሥ.2:2-4)* ከሚለው ሀረፍተ ነገር እንረዳለን::

የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ወደታች በሚወርድ አረንጓዴ መስመር የተመለከተ ነው:: ይህ «በዓለ ሃምሳ» ተብሎ በሚጠራው ቀን የተከናወነ ነው (*ሐሥ.2:1*):: በዚህ ዕለት ሶስት ሺህ ሰዎች በጌታ ኢየሱስ አመኑና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (*ሐሥ.2:41*):: ዛሬም ቢሆን ይህን ታሪካዊ የማዳን ታሪክ ቀን «በዓለ ሃምሳ» በማለት እንጠራዋለን:: የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በዚች ምድር የተመሠረተችበት ቀን ነበር::

**የቤተ ክርስቲያን ዘመን**

በበጉ /በክርስቶስ/ ደም በታጠቡት ልብ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያድራል:: ይህ በጎልጎታ መስቀል ላይ በኢየሱስ የተፈጸመውን የማዳን ሥራ በእምነት የሚቀበሉትን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው:: በዚህም በአይሁድና በአህዛብ መካከል ልዩነት የለም:: ምክንያቱም *«በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና»* (*ኤፌ.2:18*):: ተብሎ ስለተፃፈ በተጨማሪም:-

«ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላጋሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» (ኤፌ.2:19-20) የሚል ስለምናነብብ።


የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በምድር ያሉትን አማኞች ያቀፈች ናት። ጌታ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ከሆነበት ከሁለት ሺህ ዓመታት ጀምሮ በእርሱ የዳኑትን እየተቀበለ በየዕለቱ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየጨመረ ነው (ሐሥ.2:47)።

በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ወደ ጎን የሚሄደው አረንጓዴው መሥመር በዚህ ምድር መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን የኖረበትን ዘመን ያመለክታል። እኛ የምንኖረው በዚህ የደህንነት ዘመን ውስጥ ነው። ጌታ የእርሱ የሆኑትን ወደ እርሱ
ለመሰብሰብ በሚመጣበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ወደ ፍጻሜ ይመጣል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ አለች። ምክንያቱም እንደ ተስፋ ቃሉ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ ስለ አለ ነው። (2ጢ.ሞ.1:14፤ ያዕ.4:5) የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በሰማይና በምድር ያለች የነበረችና በጣም ድንቅ የሆነች ናት። ለሰው አእምሮ ቤተ ክርስቲያን የማትጠፋ «መለኮታዊ ሚስጢር» ሆና ትኖራለች (ኤፌ.3:3)።

መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ያላትን መንፈሳዊ ህብረት እንማርና እናውቅ ዘንድ ስለ ቤተ ክርስቲያንና አባላቷ በግምት 700 ያህል መግለጫዎች ይሰጠናል። የሚቀጥለው ሥዕላዊ መግለጫ ባጭሩ የቤተ ክርስቲያንን ባህርይ የሚገልጹ 24 መግለጫዎችን ይዟል። ይህ አጭር መግለጫ ሊከፈትና ሊገለጽ የማይቻለውን የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የያዘችውን መንፈሳዊ ህብትና ብልጽግና የሚገልጥ ነው። በእግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅድ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ቦታ መያዟ ሊገመት የማይቻል ታላቅ ነገር ነው። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁለተኛ ጊዜ የማይመጣ በጣም ምርጥና ልዩ የሆነ የፀጋ ዘመን ነው።








## የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ሰማይ እስከሚወስዳት ድረስ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል።

*«ከዚያ በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን እንዲሁም ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር እንሆናለን » (1ተሰ.4:17)።*

መንፈስ ቅዱስና ቤተክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ አይቀሩም። በተወሰነው ጊዜ በጌታ ይወሰዳሉ። ይህ የተወሰነው ጊዜ ሊታወቅና ሊገመት አይቻልም።

*«ወንድሞች ሆይ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም። የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና» (1ተሰ.5:1፤2)።*

በማዳን ሥዕላዊ መግለጫ ቤተ ክርስቲያንን በሚያመለክተው መሥመር መጨረሻ ላይ በትልቅ አረንጓዴ ጥያቄ ምልክት ተመልክቷል። ይህ የጥያቄው ምልክት እዚያ የተደረገበት ምክንያትም ማንም ሰው የቤተ ክርስቲያንን የመነጠቂያ ሰዓትም ሆነ ጊዜን የማያውቅ መሆኑን ለማሳየት ነው። ጌታ ቤተ ክርስቲያኑን ሊወስድ በሚመጣበት ጊዜ «በቅጽበት ዓይን» (1ኛ ቆሮ. 15:52) የሚከናወን ጉዳይ ነው። በመጀመሪያው የግሪክ ትርጉም ይህን ገለጻ በማይታይ /IN AN ATOM/ የአቶም መከፊያ የሚወስድበትን ጊዜ ያህል ማለት ነው ። ይህ ገለጻ የማይከፊል አጭር ጊዜ መሆኑን ያሳያል። ይህም ማለት መነጠቅ በሰዓት ወይም በደቂቃ ወይም በደቂቃ አንድ አሥረኛ ጊዜ ውስጥ የሚሆን አይደለም፣ ነገር ግን በጊዜ ሊለካ በማይቻል በጣም ፈጣን በሆነ ጊዜ ውስጥ የሚሆን ነው። ስለሆነም ማንኛውም ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ሁልጊዜ የተዘጋጀ መሆን አለበት።

ከጥያቄው ምልክት በላይ ወደ ላይ የሚወጣው አረንጓዴ መሥመር የቤተ ክርስቲያንን መነጠቅ ያመለክታል። ትንሹ ቀስት በዚህ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ከክርስቶስ ጋር የመገናኛውን ነጥብ ያመለክታል (*1ተሰ.4:17*)። የተነጠቀችው ቤተ ክርስቲያን ጌታን በአየር ትቀበለዋለች። እርሷን ለመቀበልና እጅግ ሰፊ ወደ ሆነው ክብር ሊወስዳት ይመጣል። ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ይህን ጊዜ በትልቅ መሻት ሊመለከተውና ሊጠብቀው ይገባል።





## ሦስቱ የሰው ልጅ ታሪክ መሥመሮች

# የዓለም ህዝብ፣ የእሥራኤል ሕዝብና የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን

መጽሐፍ ቅዱስ ሁልጊዜ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ስላለው ሕብረት ይናገራል። ባለፈው ምዕራፍ ስለ መለኮት ሦስትነት /ሥላሴ/ ከተነጋገርን አሁን ደግሞ ትኩረታችን ወደ ሰው ዘር ይሆናል።

### የመዳን ዕቅድ ቁልፍ

በማዳን ታሪክ ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ መካከል ጉልህ በሆኑ በሰማያዊ፣ በቀይና በአረንጓዴ የተሰመሩ ሦስት መስመሮች ይገኛሉ። እነዚህ ሦስት መስመሮች በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ሦስት የሰው ዘሮችን ያመለክታሉ። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በመጀመሪያ መልዕክቱ

*«ለአይሁድም፣ ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ»* በማለት ጽፏል *(1ቆሮ.10:32)*።

ይህ ጥቅስ በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን የመዋጀት ዕቅድ ቁልፍ ነገር ስለያዘ እጅግ አስፈላጊ ጥቅስ ነው። ሦስቱ ሕዝቦች አንዱ ከሌላው የተለዩ ናቸው ይህንንም ከሚከተለው ማብራሪያ በግልጽ ማየት ይቻላል።

1. አይሁድ ዕብራውያን፣ እሥራኤላውያን (የእሥራኤል ነገድ)
2. ግሪክ /በአይሁድ አባባል ከእሥራኤል ውጭ የሆኑት በሙሉ፣ አህዛብ ተብለው ይጠራሉ።/
3. የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን /አይሁድና አህዛብ በክርስቶስ ያመኑ/ ይህ ማለት ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ማለት ነው።

| |
|---|
| አሕዛብ |
| እስራኤል 1 ቆሮንጦስ 10,32 |
| አብያተ ክርስቲያን |

ይህ አከፋፈል ለእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ መሠረት ነው። ሦስቱ የተለያዩት መስመሮች ከላይ የተጠቀሱትን የሦስቱን ህዝቦች ክፍል ያመለክታሉ። ሰማያዊው መስመር አህዛብን ወይም የዓለምን ህዝቦች ያመለክታል። ቀዩ መሥመር የእግዚአብሔርን የመዋጀት ታሪክ ከእሥራኤል ህዝብ ጋር ያለውን ይገልጻል። አረንጓዴው መስመር ደግሞ የክርስቶስ ኢየሱስን ቤተ ክርስቲያን ያመለክታል። ማንኛውም ሰው ከእነዚህ ከሦስቱ በአንዱ ውስጥ የተካተተ ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ከእነዚህ ውጭ ሌላ ህዝብ የለም። እነዚህም :-

## 1. ሰማያዊው መሥመር

# የዓለም ሕዝቦች

### አጭር እይታ

በማዳን ዕቅድ ታሪክ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ የዓለም ሕዝቦች ታሪክ በሰማያዊ ቀለም የተመለከተ ነው:: ይህ መስመር ለብዙ ሺህ ዓመታት በጥፋት ውስጥ ያለውን የሰውን ልጅ ታሪክ ያመለክታል:: ኃጢዓትና ሞትን የሚያመለክተው ጥቁሩ መስመር ነው:: ይህ መስመር የጠፉትን የአዳምን ትውልዶች ያመለክታል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል *በማቴ.7:13* ወደ ጥፋት በሚወስደው በሰፊው መንገድ ላይ እየተጓዙ ስላሉ ነው:: እዚህ የምንናገረው ስለማያምኑትና አምላክ የለሽ ስለሆኑት እግዚአብሔርን ስለማያውቁ ወይም ለማወቅ ስለማይፈልጉትና እንደዚሁም አስደናቂ የሆነውን የክርስቶስን የማዳን ሥራን ስለማያውቁት (ስለሚቃወሙት) አሕዛብ ነው:: ሐዋሪያው ጳውሎስ *«ከጌታ ፊት ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ»* (*በ2ተሰ.1:9*) እንዳለ እድላቸው የዘላለም ጥፋት ይሆናል:: ዛሬ በዓለማችን ከ6 ቢሊዮን በላይ የሆኑ ሕዝቦች ይኖራሉ:: ከእነዚህ አብዛኛዎቹ በሰፊው መንገድ ላይ እየሄዱ ያሉ ናቸው::

ሰማያዊው መስመር በዓለም ታሪክ ውስጥ አስቃቂ የሆኑትን ጥፋትና፣ ጉስቁልና፣ ጦርነትንና ሞትን ያሳያል:: ባለፉት ብዙ ሺህ ዓመታት ውስጥ አራት ታላላቅ የዓለም ገዢዎች ተነስተው ነበር ነገር ግን ሁሉም ወድቀዋል:: በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ የሆነ መንግስት የለም:: በክርስቶስ ዳግም መምጣት በሚጠፋው በክርስቶስ ተቃዋሚ ዘመን እነዚህ አራቱ ታላላቅ መንግስታት እንደገና ይነሳሉ:: ስለዚህ ነገር ወደ ፊት ሰፋ ባለ ሁኔታ እንመለከታለን::

ሰማያዊው መስመር «በነጩ ዙፋን ፍርድ ያከትማል» ይህ ፍርድ እያንዳንዱ የሚጠፉት (የሚፈረድባቸው) ስለ ስራቸው መልስ የሚሰጡበት ፍርድ ይሆናል:: «ሙታን ሁሉ ተነስተው በእግዚአብሔር ፊት በሚቀርቡበት» በነጩ ዙፋን ፊት የሚከናወን ነው:: (*ራዕ.20:11*) በዚያ «እያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን» የሚፈረድበት ይሆናል:: በተጨማሪም (*ራዕ.20:13*) «በህይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም ወደ እሳት ባህር ተጣለ» (*ራዕ.20:15*) ያልዳኑት የዓለም ህዝቦች አስቃቂ ዕድላቸው የዘለዓለም ጥፋት ነው::





### የጥንቱ ታሪክ

የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አሥራ አንዱ ምዕራፎች የሰውን ዘር ጅማሬን የዓለምን ህዝቦች ታሪክ ይሰጣል:: እነዚህ ምዕራፎች የጥንቱን ታሪክ ይዘዋል:: የሰው ዘርና የዓለም መሠረት እዚህ ተገልጾዋል:: የዚህ ዘመን አራቱ ዋና ዋና ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

1. **የዓለም መፈጠር (*ዘፍ. 1 እና 2*)**
2. **የሰው ውድቀትና ውጤቶቹ (*ዘፍ.3 እስከ 5*)**
3. **የጥፋት ውሃ (*ዘፍ.6 እስከ 8*)**
4. **የባቢሎን ግንብ (*ዘፍ.11*)**

እነዚህ ሁኔታዎች ስለምናጠናው ስለ እግዚአብሔር የመዋጀት ምክር በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: ስለሆነም ከዚህ በመቀጠል አጭር ገለጻ እናደርጋለን::

### የዓለም አፈጣጠር

1. *እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት ፈጠረ?*

   እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው በቃሉ ነው:: «በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ፅኑ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ» (*መዝ.(33):6-9፤ ዕብ.11:3*)::

2. *እግዚአብሔር ዓለምን ከምን ፈጠረ?*

   እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም /ከማይታዩት/ ፈጠረ (*ዕብ.11:3*)::

3. *እግዚአብሔር ዓለምን መቼ ፈጠረ?*

   በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ(*ዘፍ.1:1*)::

4. *እግዚአብሔር ዓለምን በማን በኩል ፈጠረ?*

   በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፈጠረ::

   (*ዕብ.1:2፤ ቆላ.1:16፤ ዘፍ.1:2፤ (መዝ.(33):6)*

5. *እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠሩን በምን እናውቃለን?*

   እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠሩን የምናውቀው በእምነት ነው (*ዕብ.11:3*)::

6. *በዘፍጥረት 1:1 የዓለም መፈጠር የተገለጸው እንዴት ነው?*

**ሀ. እግዚአብሔር ዓለምን በስድስት ቀናት ፈጠረ (*ዘፍ. 1:1-31*)**

በ1ኛው ቀን:- እግዚአብሔር ብርሃንን ፈጠረ::

በ2ኛው ቀን:- እግዚአብሔር ከሰማይ በላይና በታች ያሉትን ውሆች ለየና ሰማያትን ፈጠረ::

በ3ኛው ቀን:- እግዚአብሔር ምድርንና ውሀ ለየና ተክሎችን ፈጠረ::

በ4ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር በሰማይ ያሉትን ፀሐይን፡ ጨረቃና ክዋክብትን ፈጠረ።

በ5ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር ዓሶችንና በሰማይ የሚበሩትን ፈጠረ።

በ6ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር እንሰሶችን አራዊትንና ሰውን ፈጠረ።

በ7ኛው ቀን፡- እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ አረፈ (*ዘፍ.2፡1-4*)፡

ለ. እግዚአብሔር ዓለምን በሦስት ዋና ደረጃ በመከፋፈል ፈጠረ።

ሀ. የመጀመሪያው ደረጃ ፍጥረት፣

ዓለምን ወይም ሕይወት የሌላቸውን አካሎች ፈጠረ። (*ዘፍ.1፡1-19*)

1ኛ ቀን ብርሃን

2ኛ ቀን አየር

3ኛ ቀን ምድር ገሰጸ

4ኛ ቀን የሰማይ ህብረ ኮከብ

ለ. የሁለተኛው ደረጃ ፍጥረት

ሕይወት ያላቸው ነገሮችን ፈጠረ። (*ዘፍ.1፡20-25*)

5ኛ ቀን በባህር ያሉትን /ዓሶችን/ በአየር የሚበሩትን /ወፎችን/

6ኛ ቀን በምድር ላይ ያሉትን አራዊት፣እንስሳት፣ ትላትሎችን

ሐ. የሦስተኛ ደረጃ ፍጥረት

6ኛ ቀን መለኮታዊ ህይወት ሰውን (*ዘፍ 1፡26 እስከ 28*)

*«እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድረጎ ፈጠራቸው።»*

እነዚህ ሁሉ በራሳቸው ሙሉ ተደርገው ተፈጠሩ። አስደናቂ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ስለ እነዚህ መፈጠር «እግዚአብሔር ፈጠረ» በሚል ገልጿል።

(*ዘፍ. 1፡1*) «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ»

(*ዘፍ. 1፡21*) «እግዚአብሔር ዓሶችንና ወፎችን ፈጠረ»

(*ዘፍ. 1፡27*) «እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ»

ከዚህ ጋር በመያያዝ በእነዚህ ሦስት የመፍጠር ሂደት የኢቮሊዩሽን ፍልስፍና ሃሰት መሆኑ የተጋለጠ ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ፍጥረት አስደናቂ በሆነው «እግዚአብሔር ፈጠረ» በሚለው ቃል የተፈጠረ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ሕይወት የሌላቸውንና ህይወት ያላቸውን ከብርሃን፣ ከአየር፣ ከምድር ተክሎችና በሰማይ ያሉት (ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ክዋክብት) በመጀመሪያ የፍጥረት ክፍል





በሥልጣናዊ መንገድ ቢፈጥር ኖሮ አሶች፡ ወፎችና ሕይወት ያላቸው እንስሳት በሁለተኛው የመፍጠር ክፍል ሲሆን አይችልም ነበር።

እነዚህ ሕይወት ያላቸው አንሰሳት (ነገሮች) በሁለተኛው የፍጥረት ክፍል የሚገኙ ናቸው። «እግዚአብሔር ፈጠረ» በሚሰው አስደናቂ ቃል የተገኙ ናቸው። አሶች ወፎችና እንሰሶች ሕይወት ካላቸው ክፍል ውስጥ ናቸው። እነዚህ የደም ዝውውር፣ የማወቅ፣ ስቃይን የመረዳት ስሜት አላቸው። አብዛኞቹ በምድር ላይ የሚገኙት እንሰሳት አጥቢዎች ናቸው። እነርሱም መዋለድ፣ ልጆቻቸውን ማሳደግና መጠበቅ ይችላሉ። ከሚሰበር ተክልና ከሚቆረጥ ዛፍ ልዩነት አላቸው። ተክሎችና ዛፎች ስቃይን የመሰማት ነገር የላቸውም። እንደ ሰው ሲቆሰሉ ወይም ሲጎዱ ከሚሰማቸው ከእንሰሳት የተሰዩ ናቸው። እንደ ሰው ሲጎዱ ወይም ሲጨነቁ ይሰማቸዋል። ስለሆነም ከሁለተኛው የፍጥረት ክፍል እንሰሳትን ወደ ሦስተኛ የፍጥረት ክፍል ሰው ወደ መሆን ማደግ የማይቻል ነው። በድጋሚ ደግሞ ይህ ሦስተኛው የፍጥረት ክፍል የተገኘው «እግዚአብሔር ፈጠረ» ከሚለው አስደናቂ ቃል ነው። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረ በአፈጣጠሩ ከሌሎች ፍጥረታት ልዩ የሚያደርገው ግልጽ የሆነው ነገር እዚህ ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል አስር ጊዜ እንዴት እግዚአብሔር ተክሎችንና እንስሳትን «እንደ ወገኑ» እንደፈጠረ ይገልጻል። *(ዘፍ. 1፡11፣12፣21፣24፣25)* የእግዚአብሔር ቃል ሰው በዚህ መንገድ መፈጠሩን አይናገርም። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል (ዘፍ. 1፡27) *«በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው»* ይህ ፍጹም የተሰየና ልዩ የሆነ ነገር ነው።

እዚህ ላይ አንድ ሰው በላቦራቶሪ በሳይንስ ምርምር ጥናት ከሚደረገው የእውነተኛ ሳይንስ የኢቮሉሽን ፍልስፍና የማይስማማ መሆኑን በግልጽ ለማየት ይችላል። የኢቮሉሽን ፍልስፍና /መላምት/ ሁሉን ለሚችለው ለማይንና ምድርን ለፈጠረው የሚገባውን ክብር ለመስጠት የማይፈልግ ነው። አምላክ የለሽ የሆኑ ሰዎች (እግዚአብሔርን የማያምኑ) በእግዚአብሔር ከመፈጠራቸው ይልቅ ከጦጣ መገኘታቸውን ያምናሉ።

## የሰው የኃጢአት ውድቀትና ውጤቶቹ

የሰው ታሪክ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር በተፈጠረው በአዳም ይጀምራል። ከአዳም በፊት ሌላ ሰው በምድር ላይ አልነበረም። ሰው ሁሉ የመጣው ከአዳም ነው። ከማንኛውም ነገድ ወይም አገር እንምጣ ሁላችንም ከአዳም የመጣን ነን።

*ይህን እንዴት እናውቃለን?*

ሁላችንም ሟች በመሆናችን ከዚሁ እውነቱን ማየት እንችላለን፡፡ የትም ቦታ የማይሞት ሰው ቢኖር ይህ ሰው ከአዳም ያልመጣ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ «ስለዚህ ምክንያት ኃጢዓት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢዓትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ኃጢዓትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ» በማለት ያስተምረናል *(ሮሜ.5፡12)*፡፡ ከሰው ውድቀት በፊት ሞት በዓለም አልነበረም፡፡

አዳም በተፈጠረበት ጊዜ ያለ ኃጢአት ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም በሆነና ከልካይ በሌለው ህብረት ይኖር ነበር፡፡ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ኃጢዓት አልነበረም፡፡ አዳም ፍጹም ኃጢዓት በሌለበት ዓለም ውስጥ ይኖር ነበር፡፡ በራሱ ኃጢዓት አልነበረበትም፣ እርሱ በጠቅላላ ኃጢዓት የለሽ ነበር፡፡ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ሁለት ምዕራፎች በዘፍጥረት 1 እና 2 የተገለጸ ነው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ውድቀትና በሰው ላይ የሆኑትን አስፈሪ ውጤቶችን ይገልጻል፡፡ አዳም በኃጢዓት ከወደቀ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት አልነበረውም፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከእርሱ የተገኙ ሁሉ በእርሱ መውደቅ ምክንያት ተበከሉ (ተመረዙ)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ በኃጢዓት እንደተጸነሰና በኃጢዓት እንደተወለደ ይናገራል *(መዝ.(51)፡5)*፡፡ *«ሁሉም በድለዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል»* *(ሮሜ. 3፡23)*፡፡ *«የኀጢአት ዋጋ ሞት ነው»* (ሮሜ. 6፡23)፡፡ ሁላችን ከአዳም የተገኘን ስለሆነ ሁላችንም ሟቾች ነን፡፡ ምክንያቱም በአዳም ውስጥ ነበርንና *(1ቆሮ.15፡22)*፡፡ ይህ በአዳም ውስጥ ላሉት የሰው ዘር አስፈሪ እውነት ነው፡፡

*እግዚአብሔር ሰውን ለምን ለፈተና ፈጠረው?*

1. እግዚአብሔር ሰውን ፈቃድ የሌለው ባሪያ፣ አሻንጉሊት ወይም የቼዝ መጫወቻ እንዲሆን አልፈለገም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሰውን በፈቃደኝነቱ የሚታዘዝና ከአምላኩ ጋር ፍጹም የሆነ ሕብረት እንዲኖረው ፈቅዶ ነበር፡፡
2. እግዚአብሔር ህብረት የሚያደርገው ቅዱስ ከሆነው ፈቃዱ ጋር ህብረት ከሚያደርግ ሰው ጋር ብቻ ነው፡፡
3. ሰው በተፈጥሮ ላይ መግዛት ይችል ዘንድ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር ህግ መገዛት አስፈልጎት ነበር፡፡ (መታዘዝን ያልተማረ በኋላ ትዕዛዝ መስጠትን አይችልም)
4. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ በሆነው ፈቃድ፣ ሃሳብና ደስታ ስሜቶች ስላሉት ሊፈተን የሚችል ነው፡፡





*የሰው ውድቀት እንዴት ሊመጣ ቻለ?*

የሰው ውድቀት «አትብላ» ካለው ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሊመጣ የሚችል ነበር፡፡ ከዚያ ሰይጣን ለሰው የሚከተሉትን ፍላጎቶች ሰጠው፡፡

1. እግዚአብሔር የከለከለው እንዲኖራቸው፣
2. እግዚአብሔር ያልገለጸላቸውን እንዲያውቁ፣
3. እግዚአብሔር ያልፈቀደውን እንዲሆኑ፡፡

*ሰይጣን ሰውን እንዴት ያጠምዳል?*

1. በሥጋው ፈቃድ «ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ አየች» *(ዘፍ.3፡6)*
2. በነፍስ ፈቃድ «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ» *(ዘፍ.3፡5)*
3. በመንፈስ ፈቃድ «በውኑ እግዚአብሔር አዟልን ?» *(ዘፍ.3፡1)*

*ሰይጣን እንዴት የእግዚአብሔርን እውነት እንዳይታዘዙ አደረገ?*

1. በእግዚአብሔር ቃል እንዲጠራጠሩ «በውኑ እግዚአብሔር አዟልን?»
2. ለእግዚአብሔር ቃል እንዳይታዘዙ «አትሞቱም»
3. ከእግዚአብሔር ቃል የራሱን (የሰይጣንን) ቃል በመተካት «እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ»

*ሰው ለሰይጣን ወጥመድ የሰጠው መልስ ምን ነበር?*

1. ሰው ሊፈተን በሚችልበት አደገኛ ቦታ ራሱን ሰጠ፣
2. ሰው ራሱን ከፈታኙ ጋር ለመወያየት ሰጠ፣
3. ሰው የእግዚአብሔርን የእውነት ቃል ከመጠበቅ ችላ አለ፣
4. ለፈታኙ የማታለል ቃል ሁለት ጆሮውን ከፈተ፣
5. ሰው እምነት ያለው እግዚአብሔር በፈጠራቸው ነገሮች እንጂ በእግዚአብሔር አይደለም፣
6. የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያው አድረጎ መውሰዱ

*የሰው ውድቀት ውጤቶች*

1. ሰው በኃጢዓቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለየ፣
   «በዚህ ዓለም ያለ አምላክ ነበራችሁ» *ኤፌ.2፡12 ኢሣ.59፡2*
2. ሰው በኃጢአቱ ምክንያት የሰይጣን ተገዢ ሆነ፣

«ኃጢዓትን የሚያደርግ የኃጢዓት ባሪያ ነው።» (ዮሐ. 8:34፤ ቆላ.1:13፤ 2ጴጥ.2:19፤ ዮሐ. 8:44፤ የሐዋ.10:38፤ ዮሐ. 26:18)

3. በኃጢዓቱ ምክንያት ሰው ለሞት ተገዢ ሆነ።
«የኃጢዓት ዋጋ ሞት ነው።» (ሮሜ. 6:23፤ ዘፍ. 2:17)
   - *መንፈሳዊ ሞት፡- (ኤፌ.2:1፤ሉቃስ. 9:60፤ ሉቃ.15:23)*
   - *የስጋ ሞት፡- (ዕብ.9:27፤ 1ቆሮ.15:22፤ ሮሜ. 8:10)*
   - *የዘላለም ሞት፡- (ራዕ.20:6 እና ራዕ. 14፣21:8)*

4. ሰዎች ሁሉ ኃጢዓተኞች ስለሆኑ የሞት ተገዢዎች ናቸው። (*ሮሜ 3:23 ፤ሮሜ 5:12-19፤ ሮሜ 6:23፤ 1ቆሮ. 15:21፣22 ፤ መዝ.(51):7*

5. ኃጢዓት የሰውን ማህበራዊ ሥርዓት በአጠቃላይ አጥፍቶታል። ጥላቻ፣ ውሸት፣ ጦርነት፣ ሞት ጋብቻዎችን፣ ቤተሰቦችን፣ ሕብረተሰቡንና ሕዝቦችን በሙሉ እያሸነፈ ሔደ። ሰዎች በዚህች ምድር ላይ አንዱ ለሌላው መኖር ማለት ምን እንደሆነ ማወቅ አልቻለም። በፈንታው ግን እርስ በእርስ መቃረን ጀመሩ (*ሮሜ.1:21-32፤ ገላ.5:19-21፤ 1ጢሞ.1:9-10*)። እግዚአብሔር በኖህ ዘመን ማንኛውንም በጥፋት ውሃ የሚፈርድ ሆነ። ከኖህ ስምንቱ ቤተሰብ በስተቀር በሙሉ ኃጢዓት በክሎት ስለነበር እግዚአብሔር የሰውን ዘር በውሀ ለማጥፋት ፈረደ /ወሰነ/።

6. ኃጢዓት ከሰው ውጪ የሆኑትንም ፍጥረታት አጥፍቶአል። በአዳም ኃጢዓት በኩል የኃጢዓት እርግማን በጠቅላላው ተፈጥሮ ላይ በተክሎችና በእንስሳት ላይ መጥቷል (*ዘፍ.3:17-19፤ ሮሜ.8:19-23*)። እንስሳት እርስ በእርሳቸው የሚበላሉና የሚሞቱ ሆኑ። ተክሎች እንኳን የሚደርቁና የሚሞቱ ሆኑ ሞት ዓለምን ገዛ።

## የባቤል ግንብ

የሰው ዘር ለማይ ጠቀስ ከተሞችንና ግንቦችን ለመስራት በመነሳቱ የጥንቱ ታሪክ መደምደሚያው ላይ መጣ (*ዘፍ.11:4*)። አምላክ የለሽ የሆነው የሰው ዘር በራሱ ጉልበት ለማይን ለማወክ ያደረገው ሙከራ ነበር። ባቤል ማለት የአምላክ ደጅ /በር/ ማለት ነው /BAB-EL/ እግዚአብሔር ግን በፍርድ ጣልቃ ገባ። ተመልሰው ከተማቸውን እንዳይሰሩ ቋንቋቸውን በመደባለቅ በምድር ላይ




የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ማብራሪያ

በተናቸው (*ዘፍ.11:8*)። ከዚያን ጊዜ በኋላ ባቤል የሚለው ትርጓሜ መደባለቅ (መዘበራረቅ) የሚል ሆነ (*ዘፍ.11:9*)።

*ከዘፍ.12* ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ምዕራፉን ይጀምራል። በአብርሃም በኩል እግዚአብሔር ራሱን ለእሥራኤል ልጆች ሰጠ። ከዚህ በኋላ የዓለም ህዝቦች ከእሥራኤል ታሪክ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ብቻ ነው የሚገኙት።

መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍ.*12* ጀምሮ እስከ *ሐሥ. 12* ድረስ 39 የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትና የማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌሎች ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት ይናገራል። *ከሐሥ.13* ጀምሮ ወንጌል ወደ መላው የምድር ሕዝቦች መሄዱን ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ ከወገን፣ ከቋንቋና ከነገዶች የክርስቶስ ኢየሱስን ቤት ክርስቲያን ይሰበስባል።




## 2. ቀዩ የደህንነት *መሥመር*

## የእግዚአብሔር የማዳን *ታሪክ* ከእስራኤል ጋር

### አጭር እይታ

ቀዩ መስመር በእግዚአብሔር የደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ነገድ መዋጀቱን የሚያመለክት ነው:: ይህ መስመር ከ 2150 ክ.ክ.ል በፊት ይኖር የነበረውንና ከከለዳውያን ኡር በወጣው በአብርሃም ተአምራዊ ሥራ ይጀምራል:: አብርሃም የ100 ዓመት ሰው በነበረ ጊዜ በእግዚአብሔር ተዓምራዊ አሠራር «ይስሀቅ» ብሎ የጠራውን ልጁን ወለደ ይስሐቅ ደግሞ ያዕቆብን ወለደ:: እነዚህ ሦስቱ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ «የእምነት አባቶች» ተብለው ይጠራሉ:: እነርሱም ለእሥራኤል ነገድና ለደህንነት መገኘት ሥረ መሠረት ናቸው (*ሮሜ.11:16-20*): እግዚአብሔር ከእነዚህ ሦስቱ የእምነት አባቶች የሚወለዱት ለእግዚአብሔር የተመረጠ ዘር እንደሚሆኑና እነርሱም አንድ ጊዜ እንደገና ለምድር ህዝቦች በረከት እንደሚሆኑ ማለሳቸው (*ዘፍ.12:1-3፤ 22:15-18፤ 26:2፣28:12-15*)::

ያዕቆብ በኋላ ደግሞ እሥራኤል የተባለው (ዘፍ. 32:28) በጠቅላላው 12 ልጆች ነበሩት:: ሮቤል፣ ስምኦን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ዳን፣ ንፍታሌም፣ ጋድ፣ አሴር፣ ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ ዮሴፍና ቢንያም ናቸው:: እነዚህ የ12 የእሥራኤል ነገዶች አባቶች ነበሩ::









በመቶ ሠላሳ ዓመቱ ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር ወደ ግብጽ ወረደ:: በግብጻውያን ከመዋለድ እስኪታገዱ ድረስ ጭቆና ቢበዛባቸውም የእሥራኤል ህዝቦች እየበዙ ሄዱ (*ዘፀ.1:8*)::

በአጠቃላይ የእሥራኤል ህዝቦች በግብጽ ምድር ለ 430 ዓመታት ኖረዋል (*ዘፀ.12:40*):: ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ከግብጻውያን ባርነት ነፃ የሚያወጣቸውን ሙሴን ጠራው:: ለአርባ ዓመታት በምድረ በዳ ከተቅበዘበዙ በኋላ በመጨረሻ በኢያሱ መሪነት የተሰፋይቱን ምድር መውረስ ችለዋል::

ከዚህ በኋላ በሳዖል በዳዊትና በሶሎሞን በመጀመር እሥራኤላውያን የነገሥታትን ዘመን ጀመሩ:: የእሥራኤል ነገዶች ከግብጽ ከወጡ ከ 480 ዓመታት በኋላ ንጉሥ ሶሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠራና ለእግዚአብሔር ቀደሰው (1ኛ*ነገ.6:1*) :: ንጉሥ ሶሎሞን እግዚአብሔርን በጥሩ ሁኔታ እያመለከ ሳለ ባረጀ ጊዜ ከአህዛብ ወገን ያገባቸው ሚስቶቹ ልቡን ወደ ጣዖት አምልኮ አዘነበሉበት (*1ነገ.11:4*): ከንጉሥ ሶሎሞን ሞት በኋላ አሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች፣ ሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥትና የደቡቡ የይሁዳ መንግሥት በመባል በሁለት ተከፈሉ::

በ722 ክ.ል.በፊት ይሁዳና ቢኒያም ሲቀሩ የሰሜኑ አሥሩ የእሥራኤል ነገዶች በአሶራውያን እጅ ወደቁ:: ከ 606-586 እ.ኤ.አ. (ከክርስቶስ ልደት በፊት) ባለው ጊዜ የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የይሁዳንና የቢንያምን ነገዶች ወደ ባቢሎን ማረካቸው:: የሶሎሞን ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን ተደመሰሰ:: ቀጣዩን 600 ዓመታት የእሥራኤል ነገዶች በባቢሎናውያን፣ በሜዶንና በፋርስ፣ በግሪኮችና በመጨረሻም በሮማውያን አገዛዝ ሥር ሆኑ::



የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ መሲሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መጣ:: እግዚአብሔር ግን በብሉይ ኪዳን በነቢያቱ እንደተናገረው መሲሁ የመዋጀት ሥራውን በኢየሩሣሌም ፈጸመ:: እስራኤል ንጉሷንና መሲሁን ባታውቅም ክርስቶስ በኢየሩሳሌም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞት ለደህንነት የሚሆን ሥራ ሰራ:: በብሉይ ኪዳን ነቢያት እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል እንደተናገረው ተከናወነ እስራኤል ጌታዋንና ንጉሷን ኢየሱስን ሳታውቀው ነበር ከዚህም የተነሳ ሰቀሉት:: ምክንያቱም «ይሁዳ» የመሰናከል ዓለት ሆነባቸው(*1ቆሮ.1:23)* የመስቀሉን ማዳን ተቃወሙ:: በዚህም ምክንያት ለ1900 ዓመታት ያህል በዓለም ሕዝቦች መካከል ተበታተኑ ኢየሩሣሌምም በአሕዛብ ተረገጠች (*ሉቃ.21:24*)::

ይህም ቢሆን እሥራኤል አልጠፋችም:: በምንም ነገር እግዚአብሔር ህዝቡን አልጣለም(*ሮሜ.11:1*):: *«እግዚአብሔር በፀጋው ስጦታና በመጥራቱ አይጸጸትምና» (ሮሜ.11:29)::* ካለፈው አንድ መቶ ዓመታት ጀምሮ እግዚአብሔር ህዝቡን ከዓለም አገሮች ይሰበስብ ጀመር:: ከ118 ሀገሮች ወደ ቅድስት ምድር ተመለሱ:: ግንቦት 14 ቀን 1948 ዓ.ም. የዛሬዋ የእሥራኤል መንግስት ተመሠረተች:: ያልተሟሉና የተደባለቁም ቢሆኑም እንኳን 12ቱ ነገዶች ወደ ቅድስት ምድር ተመልሰዋል:: ከየትኛው ነገድ እንደ ሆኑ ማንም አያውቅም:: ከሌዊ ነገድ መምጣታቸውንና የዳዊት ቤተሰብ መሆናቸውን የሚያውቁት ካህናቱና ሌዋውያኑ ብቻ ናቸው:: አሁንም ቢሆን የአይሁዳውያን ወደ አባቶቻቸው ምድር መመለስ ያለማቋረጥ እየቀጠለ ነው::

እሥራኤል ሕያው ተዓምር ናት፡ እሥራኤል ለ 4000 ዓመታት በቀሩት በዓለም ነገዶች የተጠላች በጦርም የተወጋችና በከፊልም የተደመሰሰች ነገድ ብትሆንም በፍጹም አልጠፋችም:: በአሁኑ ጊዜ በተቃራኒው እንደ እሥራኤል ነገድ የዓለምን ሕዝብ ትኩረት የሳበ በምድር ላይ ሌላ ህዝብ አይገኝም::

ከእስራኤል ህዝብ ጋር ያለው የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ያበቃ አይደለም:: አንድ ቀን እሥራኤል መሲሗን ወደፊት ታውቀዋለች:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «በኃይልና በብዙ ክብር ሲመጣ የወጉት ያዩታል» (*ማቴ.24:30፤ ዘካ.12:10)* ይላል:: የተሰቀለውን በማየት ንስሐ ይገቡና ይድናሉ ፣የኃጢዓታቸውን ሥርየት ያገኙና መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ (*ዘካ.12:10-14*):: ቀዩ የመዋጀት መስመር የተዋጀው የእሥራኤል ሕዝብ በሺው ዓመት መንግስት ታሪክ ውስጥ ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆኑ ያሳያል:: በዚህ መንግስት የእግዚአብሔር ልጅ የነገሥታት ንጉስ በመሆን ዓለምን በሞላው ለሺህ ዓመት ይገዛል:: (*ራዕ.20:1-10፤ ኢሣ.11:1-10)* በዚህ በመሲሁ መንግሥት ዘመን መላው እሥራኤል ለሌላው የዓለም ህዝብ ሚሲዮናውያን /የወንጌል መልዕክተኞች/ ይሆናሉ:: (ዘካ. 8:13፣23፤ ኢሳ. 9:1-6) በሺሁ ዓመት መጨረሻ የእሥራኤል ቀይ የማዳን መስመር ወደ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ያመራል (ራዕ.21:1):: የአሥራ ሁለቱ





የእሥራኤል ነገዶች አባቶች ስሞች በተዋቡት በሰማያዊቱ ኢየሩሣሌም በሮች ላይ የተጻፉ ናቸው (ራዕ.21:12):: የተዋጀው የእሥራኤል ነገድ ለዘላለም በሰማይ ይሆናል::

## የእሥራኤል ነገድ ምንነት

## እሥራኤል – ብቸኛና ታላቅ መለኮታዊ ራዕይ የተሰጣት

*«እንግዲህ የአይሁድ ብልጫ ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው:: አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው» (ሮሜ.3:1-2) ::*

እግዚአብሔር ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር ያደረገው የመዳን ታሪክ በ39ኙ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት የተገለጠ ነው:: ጠቅላላውን ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ከእስራኤል ሕዝብ በሆኑት ዕብራውያን የተጻፉ ናቸው:: ለምሳሌ ሉቃስ አንዱ ፀሐፊ ነው:: ሉቃስ ቢደም ዕብራዊ አይደለም ሉቃስ ከአንጾኪያ የሆነ ግሪካዊ ዶክተር የጳውሎስ ተማሪና በእርሱ ሥልጣን ስር የጻፈ ነበር:: ሉቃስ ብቻ አንዱን ወንጌልና (የሉቃስ ወንጌል) የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍት ጻፈ:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ራሱን ለእሥራኤል ብቻ መግለጹን ይናገራል::

*«ቃሉን ለያዕቆብ፣ ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእሥራኤል ይናገራል ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፣ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም ሃሌሉያ» (መዝ.(147) ፣19፣20)::*

እግዚአብሔር ራሱን ለአህዛብ አልገለጠም፣ ነገር ግን ለተመረጡት ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ገለጠ:: መጽሐፍ ቅዱስ የመጣው ከእሥራኤል ነው:: ስለሆነም እሥራኤል ብቻ ናት ታላቅ መለኮታዊ ራዕይ ያላት::

## እሥራኤል፣ ብቸኛዋ የደህንነት ህዝብ በዓለም ውስጥ


ከዓለም ፍጥረት በፊት እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም ለመላክ ወሰነ (*1ጴጥ.1:19-20*):: ስለዚህም ምክንያት ነበር በብሉይ ኪዳን ዘመን ለራሱ የሆነ ህዝብ የመረጠው:: ይህ ሕዝብ ለእግዚአብሔር «የካህናት መንግሥትና ቅዱስ ሕዝብ» እንዲሆን ታቅዶ ነበር (ዘፀ.19:6):: ከሌላው ሕዝብ ጋር ሳይደባለቁ /በጋብቻ/ በደም ሀረጋቸው ንጹህ ሆነው እንዲኖሩ የተፈለጉ ነበሩ:: በዚያን ዘመን ሌሎቹ ሕዝቦች ጣዖታትንና ሰይጣንን ያመልኩ ነበር:: በምንም ነገር እስራኤል ሰይጣንን ያመልኩ ነበር:: (*1ቆሮ.10:20)::* በፍጹም በምንም ምክንያት ከእንደዚህ ካለ ርኩሰት ጋር በጥፋት ርኩሰት እንዲተባበሩ አልተፈቀደም ነበር:: ስለዚህም እግዚአብሔር ህግን፣ የአምልኮ ሥርዓትንና ተስፋን ሰጣቸው:: የእሥራኤል ህዝብ የእግዚአብሔር ልጅ /ሥጋ ሆኖ/ የሚገለጥበት ነገድ እንዲሆን የተለየ ነበር::

በዓለም ዓይን እሥራኤል ሁልጊዜ ታላቅ ምስጢር ሆና የምትኖር ናት:: ብዙ ሰዎች በእሥራኤል ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ በተለየ መንገድ ይወድዷታል:: እኛም ከእነዚህ ከሁለቱ በአንዱ ውስጥ እንገኛለን:: እኛ እሥራኤልን እንወዳለን ምክንያቱም አዳኛችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ከዚህ ነገድ መሆኑን ስለምናውቅ ነው:: የጎልጎታ መስቀል የተተከለው በእሥራኤል ነው:: አዳኙ የማዳን ሥራውን ከኢየሩሣሌም ከተማ ውጪ ፈጸመ:: ስለዚህም መስቀሉ የሚገኘው በቀዩ የመዋጀት መስመር መካከል ነው:: ቀዩ መስመር የፈሰሰውን የጌታችንን ደም ያሳስበናል:: ኢየሩሣሌም የዓለም መዳን መካከለኛ ሥፍራ ናት:: የዓለም መድሃኒት ክርስቶስ ስለሚመጣበት መንገድ ሲወሰን እግዚአብሔር እሥራኤልን ብቻ መረጠ:: ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «መዳን ከአይሁድ ነውና» ስለሚል ነው (*ዮሐ.4:22*): እሥራኤል ብቻ መዳን የሚገኝባትና የደህንነት ተሸካሚ ናት:: መሲሁ ብቻ የመዳን ዋነኛ ነጥብ ነው:: እሥራኤል የተመረጠችበት ዋነኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ ስለሚመጣባት ነበር:: ይህ ህዝብ በዚህ ምድር ላይ ሌላ የተለየ መለያ የለውም (ሮሜ. 9:4-5)::

## የሚመጣው መሲህ በእሥራኤል የማዳን ታሪክ ውስጥ

## ዓለምን የሚያድን ተስፋ መስጠት

እግዚአብሔር ለእርሱ ከተመረጡት ህዝብ ጋር ለአራት ሺህ ዓመታት ይናገር ነበር:: እሥራኤል የሚለው ቃል የሁለት ቃል ጥምር ነው ትርጓሜው «እግዚአብሔር ይዋጋል» ማለት ነው:: ትርጉሙም «እግዚአብሔር ጦርነትን እንደሚመራ» የሚገልፅ ነው:: እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ዘር ከኃጢአት፣ ከሞትና ከሰይጣን ለማዳን ይዋጋል:: ይህ ጦርነት /ውጊያ/ በኤደን ገነት አስደንጋጭ ከሆነው ከሰው ውድቀት የጀመረ ነው:: እግዚአብሔር «በቀደመው እባብ» በሰይጣን ላይ *«በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘረህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ:: እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ»* በሚል ቃል በማለት ጦርነትን አወጀ (*ዘፍ.3:15*)::








ይህ ኃይለኛ ቃል የጥንቱ ወንጌልና የጥንቱ ተስፋ ነው:: ስለ አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስና በጎልጎታ መስቀል ላይ ስለ ተፈጸመው የመዋጀት ሥራ ይናገራል::*«የእግዚአብሔር ልጅ የሰይጣንን ሥራ ሊያፈርስ»* መጥቷል (*1ዮሐ.3:8*): እግዚአብሔር የጠፋውን ሰው ለማዳን ሰው መሆን አስፈለገው (*ማቴ.18:11*) *በዘፍ.3:15* ስለሚመጣው መሲህ የተሰጠው የጥንቱ ተስፋ «ተቀዳሚ ተስፋ» በመባል ይታወቃል:: በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ገፅ 44 ላይ ተመልከት ይህን የሚመጣው ተስፋ የሚያመለክተው ቀይ መስመር ከአዳም ይጀምርና በሴትና በኖህ በኩል በማለፍ ወደ አብርሃም ያመራል:: ይህን ክፍል ከአዳም እስከ አብርሃም ያለውን ጊዜ «ሰውር የሆነው የእግዚአብሔር የመዋጀት ታሪክ» ልንለው እንችላለን:: ስውር የሆነበት ምክንያት ስለሚመጣው ደህንነት ተስፋ ብቻ ስለሚገልፅ ነው::

## ለአብርሃም የተሰጡት ሦስት ጣምራ ተስፋዎች

## አንድ ምድር፣ አንድ ነገድ፣ አንድ በረከት

በዘፍ.12 ያለው የአብርሃም መጠራት ከእሥራኤል ህዝብ ጋር ያለውን የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ ይጀምራል:: ታሪኩም የዚህ ነገድ አባት በሆነው በአብርሃም የእግዚአብሔርን የማዳን ታሪክ ይጀምራል:: የዚህ ነገድ አባት ለሆነው፣ ለአብርሃም ሦስት ጣምራ ታላላቅ ተስፋዎችን ሲሰጠው መረጠው::

*«እግዚአብሔር አብርሃምን አለው ከአገርህ ከዘመዶችህም፣ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ:: ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፣ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» (ዘፍ.12:1-3)::*

### 1. ምድረ - እሥራኤል

እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የገባለት ምድር የእሥራኤልን ምድር ነው:: እንደ ሕዝቅኤል ትንቢት *«በምድር መካከል በተቀመጠ ህዝብ ናትና»* (*ሕዝ38:12*) :: ትልቁ ሀገር ሲባኖስ እስራኤልን በሰሜን ያዋስናል ትልቁ ተራራማ የሲና ሰላጤ ደግሞ በደቡብ ያዋስናል የሜዲትራኒያን ባህር በምዕራብ በኩል ሲገኝ የዮርዳኖስ ወንዝ ከእሥራኤል በሰተምሥራቅ በኩል ይፈስሳል:: እሥራኤል 28,186 ስክዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያላት ትንሽ ሀገር ናት:: ቢሆንም ይህች አገር ለእኛ በጣም አስፈላጊ ናት:: የእግዚአብሔር ልጅ በምድር በነበረበት ጊዜ የኖረው እዚህ ነው:: እዚህ ነው ቃል ሥጋ የሆነው::

በዚህች በተረገመች ምድር የተመሳሰሰውና የዘለዓለሙን የመዋጀት ሥራ በጎልጎታ መስቀል ላይ የፈጸመው በእሥራኤል ምድር ነው። የእሥራኤል ምድር ለዚህ ዓለም ደህንነትና ለዘለዓለም ደህንነታችን የመከናወን መሠረትና ድልድይ ሆነች። ለዓለም ደህንነት መካከለኛ በመሆን የተፈጸመው የማዳን ሥራ ወደ ዓለም አገሮች የሚሰፋና በነገዶች መካከል የሚታወጅ ሆነ። እዚህ በቤተልሔም የዳዊት ዘር በሆነችው በማሪያም በኩል በኃጢዓተኛ ሥጋ ምሳሌ እንደ እኛ ሰው ሆኖ መጣ (*ሮሜ.8:3-4*)። ዘለዓለማዊው ራሱን ዝቅ በማድረግ የባሪያን መልክ ያዘ (*ፊል.2:5-11*)። ለመጀመሪያዎቹ ሰላሳ ዓመታት ያልታወቀ አናጺ ሆኖ በናዝሬት ኖረ። ከዚህ በኋላ እንደ መሲህና ንጉሥ ሆኖ በመታየት ቅፍርናሆምን የአገልግሎት መሠረት ለማድረግ መረጠ። ይህ ዝነኛ ቦታ የምቾት መንደር ተብሎ ይጠራል (የቃሉ ፍቺ ቅፍር መንደር ሲሆን ናሆም ደግሞ ምቾት ማለት ነው) የበረከት ተራራ ከቅፍርናሆም በላይ የሚገኝ ነው። እዚህ ንጉሡ ስምንቱን በረከቶችና የተራራውን ስብከት የሰማይን መንግስት በምድር ላይ አወጀ። በእሥራኤል ምድር ጌታ ኢየሱስ የተራቡትን በመመገብ፣ ድውያንን በመፈወስ፣ አጋንንትን በማውጣት፣ ሙታንን በማስነሳትና የገሊላን ባህር ማዕበል ፀጥ በማድረግ ታምራቱን ሁሉ አደረገ። እዚህ በእሥራኤል ምድር በመስቀል ላይ ሞተ፣ የከበረ ደሙ ፈሰሰ፣ እዚሁ ሞትን ድል አደረገና ከዚህ ወደ ሰማይ አረገ። በዚሁ በእሥራኤል ምድር ውስጥ ባለችው በኢየሩሣሌም እንደገና ይመጣል። እግሮቹ በደብረዘይት ተራራ ላይ ይቆማሉ። (*ሐሥ.1:9-11፣ ዘካ.14:4*)

## 2. የእግዚአብሔር ህዝብ - እስራኤል

እግዚአብሔር ለአብርሃም ታላቅ ሕዝብ እንደሚሰጠው ተስፋ ሰጠው። እግዚአብሔር ህዝቡን እንደ ባህር አሸዋና እንደ ሰማይ ከዋክብት ማብዛቱ ማለት ሳይሆን የእግዚአብሔር የማዳኑን ሥራ ስፋት የሚያመለክት ነው (ዘፍ. 22:17)። እግዚአብሔር ህዝቡ ጥቂት እንደሆነ ራሱ ያውቃልና (*ዘዳ.7:7-8*)፡ እግዚአብሔር የጠፋውን የሰው ዘር ከኃጢዓትና ከሞት ለማዳን ሲያደርግ የሚቻለውን እጅግ ታልቅ የሆነውን ነገር አደረገ። የኃጢዓት መሥዋዕት እንዲሆን ልጁን ላከው (*ሮሜ.8:3*)። የዓለሙ መድሃኒት በእስራኤል ህዝብ መካከል ሰው ሆነ። የእግዚአብሔር ልጅ በዕብራዊቷ ድንግል ሴት ሥጋ በኩል ወደዚህ ዓለም ገባ።





ከአይሁድ ነገድ የሆነ እውነተኛ ዕብራዊ ነበር። ሰዓሊዎች እንደሚስሉት (የሐሰት ሥዕል) ረጅም ነጣ ያለ ፀጉር ያለው ጀርመናዊ አይደለም። እርሱ ከእስራኤል ነገድ የመጣ ጥቁር ፀጉርና ጥቁር ዓይን ያለው ነበር። እርሱ በማሪያም በኩል ከዳዊት ቤተሰብና ቤት የመጣ ነው (*ሮሜ.1:3፤ 2ጢሞ.2:8*)፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእሥራኤል ነገድ የሆነ እውነተኛ እሥራኤላዊ ልጅ ነው በመስቀል ላይ ስለ ኃጢዓታችን ያፈሰሰው ደሙ የዕብራዊ ደም ነው። ጌታችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ ነገድ ስለመጣ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች ይህን የእሥራኤልን ነገድ እንወዳለን። ስለ ኢየሱስ ብቻ እሥራኤልን እንወድዳለን። በሌላ በኩል ደግሞ አምላክ-የለሽ የሆኑት ህዝቦች እግዚአብሔርንና ልጁን እንደሚጠሉ የእሥራኤልንም ህዝብ በጣም ይጠላሉ።.

## 3. በረከቱ – በኢየሱስ ክርስቶስ

በሦስተኛ አብርሃም በምድር ላይ በእርሱ በኩል /ፍጥረት ሁሉ/ የሚባረኩበትን ተስፋ ተቀበለ። ይህ በረከት ፍፁም ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር በእርሱ በኩል በሰማያዊ በረከቶች ሁሉ ባረከን (*ኤፌ.1:3*)። አዳም በኃጢዓት በመውደቁ ምክንያት ሰማያዊ በረከቶችን በከፊል አጣን። እርግማን፣ በረከቶችን ማጣትና ሞት በሰው ዘር ላይ ያደረሰው በኃጢዓት ምክንያት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ እርግማናችንና ማንኛውም ብልሽትና መጥፋትን በመስቀል ላይ ተሸከመ። ስለ ኃጢዓታችን ሞተ በከበረ ደሙ አነፃንና ዘለዓለማዊ ፀጋውንና ፍቅሩን ሰጠን። በሰማያዊ በረከቶች ሁሉ ባረከን። የክርስቶስ አማኞች በመሆናችን ከእርግማኖች ነጻ የወጣንና በአምላካዊ በረከቶች ሁሉ የተባረከን ነን። በክርስቶስ ሁሉ ነገር አለን። እርሱ ብቻ በህይወትና በሞት መጽናኛችን ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለን ብቸኛና ሁሉ በሁሉ የሆነ መመኪያችን ነው። እርሱ ካለን ከሰማይና ከምድር የምንጠይቀው ሌላ ም[illegible]ም ነገር የለንም ሁሉ አለንና።

### ኢየሩሣሌም:- «የታላቁ ንጉሥ ከተማ»

ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሣሌም በእሥራኤል ምድር እምብርት የምትገኝ ናት። ጎልጎታ የመዳን ታሪካዊ መለያ ስለሆነ ብቻ አይደለም። ኢየሩሣሌም ታላቅ ከተማ የሆነችው ፣ በእግዚአብሔር የማዳን እቅድ የተለየ ቦታ ስላላት ነው።

*«መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፣ ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል። የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል» (መዝ.(87):1-3) ።*

ኢየሩሣሌም የእሥራኤል ህዝብ ዋና ከተማ ብቻ አይደለችም:: ነገር ግን በምድር ላይ የእግዚአብሔር ዋና ከተማ ናት:: በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢየሩሣሌምን «የታላቁ ንጉሥ ከተማ» በማለት ገልጿታል (*ማቴ.5:35፤ መዝ. 48:2)* በተቃራኒ ደግሞ ባቤል በዚህ ምድር ላይ የሰይጣን ዋና ከተማ ናት:: በግሪክኛው ቋንቋ ይህች ከተማ ባቢሎን ትባላለች:: የባቤል ከተማ በዘፍ.11 እና በዳንኤልም ከምዕ.1-12 የተገለጠች ናት:: የእግዚአብሔር ጠላቶችና እምላክ የለሽነት የተሞላው የሰው ዘር የተሰበሰበባት ከተማ ናት:: በዚህም ምክንያት ባቤል ለብዙ ሺህ ዓመታት ኢየሩሳሌምን ስትወጋ ነበር:: ይህም በባቤልና በኢየሩሣሌም መካከል ያለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ነው:: የዓለም ህዝቦች በእሥራኤል ላይ የፖለቲካ ውጊያ የማድረግንም ውጤት አስከትሏል::

*ኢየሩሳሌም« የታለቁ ንጉሥ ከተማ » የሚለውን ስያሜ እንዴት ልታገኝ ቻለች*

መልሱን በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እናገኘዋለን:: አብርሃም ካህንና ንጉሥ የሆነውን መልከጼዴቅን በተገናኘው ጊዜ በመጀመሪያ እዚያ ተጠቅሳ ትገኛለች::

*«የሳሌም ንጉሰ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር:: ባረከውም፣ አብርሃም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው አለውም አብርሃምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው» (ዘፍ.14:18-20)::*

ኢየሩሳሌም እዚህ ባጭሩ «ሳሌም» በሚል ትታያለች:: ይህ አጭር አጠራር በመዝሙር እንደገናም *በዕብ.7:1-2* ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል::

*«እግዚእብሔር በይሁዳ ታወቀ:: ስሙም በእሥራኤል ታላቅ ነው:: ሥፍራው በሣሌም ማደሪያውም በጽዮን ነው» (መዝ.(76):1-2)::*

የመጨረሻው ቁጥር ሳሌም ኢየሩሳሌም ማለት እንደሆነ በቀጥታ ያመለክታል:: እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም የሚያድር ንጉስ ከሆነ *(መዝ.76:2)* *እግዚእብሔር ለዘለዓለም ይነግሳል (መዝ. (10):16)::* ኢየሩሳሌም እንደ ብሉይ ኪዳን ምስክርነት «የታላቁ ንጉሥ ከተማ» ናት*(መዝ.(48):2)*::

ከዚህ እልፍ በማለት አንድ ምዕራፍ ልንራመድ ይገባናል:: ከኢየሩሳሌም ከወጣው ካህናዊ ንጉሥ ወደ ሆነው ወደ መልከ ጸዴቅ ትኩረታችንን ስለሚስበን (ዘፍ.14:18) ቁልፍ የሆነ አስፈላጊ ጥቅስ ነው:: ስለ እርሱ በበለጠ ልንመረምር ይገባናል::





*መልከ ጸዴቅ ማን ነበር?*

መልከ ጸዴቅ የሚለው ስም «መልከ» እና «ፀደቀ» የተባሉት ሁለት የዕብራውያን ቃላት ጥምር ነው:: መልከ ማለት ንጉሥ ሲሆን ዘዴቅ (ጸዴቅ) ደግሞ ጽድቅ ማለት ነው:: ስለሆነም መልከ ጸዴቅ ማለት የጽድቅ ንጉሥ ማለት ነው:: እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የጽድቅ ንጉሥ በተመሳሳይ የሳሌም ንጉሥ ነው «ሳሌም» የሚለው ስም ሲተረጎም ሠላም ከሆነ መልከ ጸዴቅ ደግሞ የሰላም ንጉሥ ነው የሚለውን ያሰገኛል (*ዕብ.7:2)*:: እንደ ልዑል እግዚአብሔር ካህን አብርሃም ኮሎዶጎምርንና ነገሥታትን ወግቶ ሲመለስ አብርሃምን ሊገናኘውና ሊባርከው ወጣ:: አብርሃምን በተገናኘው ጊዜ እንጀራና የወይን ጠጅ አመጣ (*ዘፍ.14:18)*::

*መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም እንጀራውንና የወይን ጠጁን ለምን አመጣ?*

የዚህን ምስጢር ግልጽ ልናደርገው ይገባናል:: ያለበለዚያ ከኢየሩሣሌም ጋር ያለውን የእግዚአብሔርን ታሪክ ልንረዳ አንችልም:: በዕብራውያን መልዕክት ስለዚህ ሰው ስለ መልከ ጼዴቅ *«አባትና እናት የትውልድ ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል»* በማለት ተገልጿል (*ዕብ.7:3)*:: እንደዚህ ያለውን ገለጻ ሊያሟላ የሚችል ሌላ ሰው የለም ሁላችንም አባትና እናት የሕይወት ጅማሬና ፍጻሜ አለን:: ነገር ግን መልከ ጼዴቅ:-

*«በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል»* (ዕብ.7:3)::

ይህ አስደናቂ ነገር ነው:: መልከ ጼዴቅ በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሏል:: በምሳሌነቱ የእግዚአብሔርን ልጅ ከመሰለ ከእርሱ ጋር እኩል ነው የጽድቅ ንጉሥ፣ የሠላም ንጉሥ ፣ ለህይወቱ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ካህን ሆኖ ለዘላለም ይኖራል:: ስለዚህም ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው ከመልከ ጼዴቅ በኋላ እርሱን መስሎ የሚገኘው ምክንያቱም እርሱ ብቻ በእውነት

- «የጽድቅ ንጉሥ» *(1ቆሮ. 1:30)*
- «የሠላም ንጉሥ» *(ኤፌ. 2:14)*
- «ዘላለማዊ አምላክ» *(ራዕ. 1:18)*
- «ዘላለማዊ ሊቀ ካህናት» *(መዝ.(110):4)* ሆኗል::

እሁን መልከ ጼዴቅ እንጀራና የወይን ጠጅ ስለምን እንዳመጣ እንረዳለን:: ይህ ጌታ ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት በስቅለቱ ዋዜማ የመጨረሻውን ፋሲካ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ባከበረበት ጊዜ:-

*«ሲበሉ ኢየሱስ እንጀራን አንስቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርት ለጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ:: ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው:: እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ:: ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው») (ማቴ.26:26-28)::*

ብሎ በመስጠቱ መልከ ጼዴቃዊ ትንቢትን አሟላ:: ልክ እንደ መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ የጎልጎታው የመዋጀት ምሳሌ የሆነውን እንጀራና የወይን ጠጅ ለማምጣት ከኢየሩሳሌም መጣ ስጋዬ ስለእናንተ የተቆረሰው ደሜ ስለእናንተ የፈሰሰው በማለት የሰጠው ማለት ነው::

ዩኔ ሥጋ - ስለናንተ የተቆረሰው

ዩኔ ደም - ስለእናንተ የፈሰሰው

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ከመልበሱ ከ 2000 ዓመታት በፊት በክህነታዊ ንጉሥ ሽፋን ተገልጦ አብርሃምን ባረከው:: አብርሃም የእሥራኤል አባት እንደመሆኑ መጠን ይህን በረከት ለእስራኤል ህዝብ አስተላለፈ:: ስለዚህ ነው አስገራሚ የሆነው የደህንነት ታሪክ ከኢየሩሳሌም የጀመረው:: ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ እውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ «በዘላለማዊ ክህነት እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት» *(ዕብ.7:17)* ኃጢአታችንና ውርደታችንን በመውሰድ የእግዚአብሔር በግ በመሆን በጎልጎታ መስቀል ላይ መከራ ተቀበለ *(ዮሐ.1:29)*:: እንደ ነገሥታት ንጉሥና እንደ የጌቶች ጌታ *(ራዕ.19:16)* ለጠፋው የሰው ዘር ተዋጋና «ተፈጸመ» *(ዮሐ.19:30)* በሚለው ቃል የመዋጀትን ሥራ ፈጸመ::

የሚቀጥለው ንጽጽር የመልከ ጼዴቅን ፍቺ የበለጠ ያጠነክረዋል::

| | | |
|---|---|---|
| **መልከ ጼዴቅ** | — | **ኢየሱስ ክርስቶስ** |
| **አብርሃም** | — | **የእሥራኤል ህዝብ** |
| **ሳሌም** | — | **ኢየሩሣሌም** |
| **እንጀራ** | — | **ሥጋው** |
| **ወይን** | — | **ደሙ** |
| **ዘለዓለማዊ የጽድቅ የሠላም ንጉሥ** | — | **ዘለዓለማዊ የጽድቅና የሠላም ንጉስ** |





## የመሲሁ መምጣት

*«ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከህግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፣ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከህግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» (ገላ.4:4-5)::*

እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰው እንዲሆን በፈቀደ ጊዜ ይህችን ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ከፍ ማድረጉና መባረኩ ነበር:: በአዲስ ኪዳን «የሰው ልጅ» የሚለው ቃል ሰማንያ ስባት ጊዜ ተጠቅሷል:: ጌታ ኢየሱስም ራሱን ለመግለጽ ይህን አነጋገር ተጠቅሞታል:: ስለ ክርስቶስ ማንነት እንዲህ እናነባለን::

*ፍጹም አምላክ ነው::*

*ከአምላክ የተወለደ አምላክ፣ ካልተፈጠረው ብርሃን ብርሃን የሆነ፣ ፍጹም ሰው ሆነ፣ ስለ ሰው ልጆች በጎነት ሲል አምላክ ሰው ሆነ::*

ከዳዊት ዘር ተወላጅ የሆነችው ድንግል ማሪያም የእግዚአብሔር ልጅ የሚመጣበት መንገድ ሆና ተመረጠች:: በብሉይ ኪዳን እንደነበረችው እንደ ሙሴ እህት ስሟ «ማናያም ነበር» (*ዘኁ.26:59*) በግሪከኛ ቋንቋ ይህ ስም ማሪያም /MARI - YAM/ በመባል ይጠራል በኋላም እኛ ሜሪ እያልን የምንጠራው ስም ሆነ::

ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር የተባረከች ዕቃ ሆና ተመረጠች:: ሉቃስ እንደጻፈው የእግዚአብሔር ባርያ ብላ ራሷን ጠርታለች (*ሉቃ.1:38*):: በብሉይ ኪዳን ትንቢት እንደተነገረው ትንቢት የእግዚአብሔር ልጅ በእርሷም በኩል ወደ ተረገመችው ምድር ሰው ሆኖ በቤተልሔም ተወለደ::

*«አንቺ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ:- አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ:: ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእሥራኤል ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚል.5:2)::*

ዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ ወደዚህ ዓለም የመጣው የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ እንጂ ለሌላ አልመጣም::

*«መስዋዕትንና መባን አልወደድህም፣ ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፣ በሙሉ በሚቃጠል መስዋዕትና ስለ ኃጢዓት በሚሰዋ መሥዋዕት ደስ አላለህም:: በዚያን ጊዜ እነሆ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደ ተጻፈ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ አልሁ» (ዕብ.10:5-7)::*

የክርስቶስ ሰው መሆንን ከሌላው ልዩ የሚያደርገው ምድራዊ እናት ስትኖረው ምድራዊ አባት አለመኖሩ ነው። እግዚአብሔር አብ ራሱ አባቱ ነበር። በዚህ ምክንያት ነበር «የልዑል ልጅ» የተባለውና ጴጥሮስም «የሕያው እግዚአብሔር ልጅ» መሆኑን የተገነዘበው (*ሉቃ.1:1-32፤ ማቴ.16:16-17*)። ልደቱ ፍጹም የአምላካዊ ባህርይ ነበር። ነገር ግን ሰው በመሆኑ እውነተኛ ዕብራዊ ነበር እናቱ ከዳዊት ንጉሣዊ ቤተሰብ የሆነች ዕብራዊት ነበረች፣ የዕብራውያን ደም ነበራት፣ በዕብራውያን ህዝብ መካከል መለያ የሆነው ጥቁር ዓይኖችና ጥቁር ፀጉር ነበራት። አንዳንድ ሰዓሊዎች እንደሚስሉት የእግዚአብሔር ልጅ ሰማያዊ አይኖች ወይም የተደበላለቁ ፀጉርና የሰፋ ትከሻ አልነበረውም። ይህ የብዙ ሰዓሊዎች ግምት ይሆናል ነገር ግን ትክክል አይደለም። እንደዚህ ያሉ ሥዕሎች ፍጹም ግምታዊና ሐሰትም ናቸው።

*ይህን እንዴት እናውቃለን?*

በ1ኛ ቆሮንቶስ

*«ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት ተፈጥሮ እንኳን እያስተምራችሁምን?» በማለት ጳውሎስ ጽፏል። (1ቆሮ.11:14)*

ስለዚህም ለወንድ ልጅ አጭር ፀጉር ሲኖረው ለእርሱ ክብር ነው። ዛሬም ቢሆን በእሥራኤል ሃይማኖተኛ የሆኑ አይሁዶች ይህን ይገነዘባሉ። ወንዶች ረጅም ጢም ሲኖራቸው አጭር ፀጉር አላቸው። አዳኛችን በሥጋ ዕብራዊ፣ ከይሁዳ ነገድና የዳዊት ልጅ (ማቴ.1:1) ስለሆነ ጥቁር ዓይኖችና አጭር ጥቁር ፀጉር ነበረው።

*ያመሲሁ ተቀባይነትን ማጣት (መጣል)*

ኢየሱስም ሲያስተምር ሲጀምር እድሜው ሰላሳ ዓመት ያህል ነበር። (ሉቃ 3:23) ጌታ ኢየሱስ በእሥራኤል ምድር መሲህ ሆኖ የተገለጸው በምድራዊ ሕይወቱ መጨረሻ ላይ ነበር። የመጀመሪያዎቹን ሠላሳ ዓመታት ያሳለፈው የዛብሎን ግዛት ክፍል በነበረችው በናዝሬት ከተማ ነበር። ከዚህ በኋላ በምድር ላይ ለሶስት ዓመት ተኩል በሕዝብ መካከል ተመላለሰ። *«ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር» (ሉቃ.3:23)*። ወደ ጠፉት ወደ እሥራኤል ቤት በጎች በመሔድ ንስሐ ይገቡ ዘንድ (ማቴ. 15:24) *«መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ንስሀ ግቡ»* (ማቴ.4:17) በማለት ወደ ንስሐ ጠራቸው። በሽተኞችን ፈወሰ *(ማቴ.14:14)* ፣ *ሙታንን* አስነሳ (ማቴ.*11:5*)፣ *አጋንንትን* አስወጣ *(ማር.1:34)*፣ የተራቡትንም መገበ (ማቴ.*15:32-37*)። በእነዚህ ሁሉ የሰማይ አባቱን *ፈቃድ አደረገ (ዮሐ.10:37-38)* ነገር ግን እሥራኤላውያን አላወቁትም ነበር።





*እሥራኤል መሲኋን ያላወቀችው ለምን ነበር ?*

ለዚህ መልስ የምናገኘው ከነቢዩ ከኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ ነው። የህዝቡ ልብ ደንዳና እንደነበር ነቢዩ ጽፏል (*ኢሣ.6:9-10*)። እስራኤል ለብዙ መቶ ዓመታት በጣዖት አምልኮት ተውጣ ነበር። በሙሴ ዘመን እንኳን በወርቁ ጥጃ ዙሪያ ጨፍረዋል (*ዘፀ.32:4-6*)። በመሳፍንት ዘመን ጣዖታትን ተከትለው አምልከዋል (*መሳ.2:11-12*)። *ንጉሥ* ሰሎሞን ሚስቶቹን ለማስደሰት የእሥራኤልን ህዝብ ወደ ጣኦት አምልኮ መራቸው (*1ነገ.11:4-10*)። እሥራኤል በባቢሎናውያን ተማርከው እስከተወሰዱ ድረስ በዚሁ ሁኔታ ነበሩ። በእንደዚህ ባለ ርኩሰት መቆየት የሰውን ልብን ያደነድናል ንስሐ የማይገባ ያደርገዋል ጣዖትን የሚያመልክ ያደርገዋል። በእርግጥም የሚያመልከው ሰይጣንን ነው (*1ቆሮ.10:20*)።

በመጨረሻም መሲሁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ የእርሱ የሆኑት ህዝቦቹም አላወቁትም። ዮሐንስ «ወደ ወገኖቹም መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም» በማለት ጽፏል (*ዮሐ.1:11*)። *ንጉሥ* ለሆነው ለእርሱ በእንግዶች ማደሪያ ስፍራ አልተገኘለትም ነበር (ሉቃ.2:7)። *«የሰው ልጅ ራሱን የሚያስጠጋበት ቦታ የለውም»* በማለት ለደቀ መዛሙርቱ ተናግሮአቸዋል (ማቴ.8:20)። በዚህ ሁሉ ውስጥ *«የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከ»* (ሉቃ. 8:1)። በየሥፍራው እየሄደ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» «በእግዚአብሔር እመኑ፣ በእኔም ደግሞ እመኑ» እያለ በመደጋገም ለአይሁዶች ያስተምር ነበር (*ዮሐ.14:6-1*)። ቢሆንም በእርሱ ያመኑት «*ታናሽ መንጋዎች*» ነበሩ(*ሉቃ.12:32*)። የአብዛኛው ህዝብ ልብ እንደደነደነ ቀረ (ማቴ.13:15)። የሚያሳዝነው እስከ አሁን ድረስ ምንም ለውጥ አለመሆኑ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እቅዳቸው ሁሉ እርሱን ለማጥፋት ሆነ። *«ፈሪሳውያንም እንዴት አድርገው እንደሚያጠፉት ሸንጎ አደረጉ» (ማቴ.12:14)* የከፍተኛ ሸንጎ አባላትም ህይወቱን ለማጥፋት አደሙ (*ዮሐ.11:53*)። ጌታ ኢየሱስ በመደጋገም ወደ አብ የሚሄድበት መንገድ ይህ እንደነበረ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸው ነበር።

*«የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችም በጻፎችም ሊጠላ፣ ሊገደልም፣ በሦስተኛውም ቀን ሊነሳ ይገባዋል» በማለት ተናግሯቸዋል (ሉቃ.9:22፤ ሉቃ. 9:44-45፤ ሉቃ. 18:31-34)*። ነገር ግን አስቀድሞ የተናገራቸው ሁኔታ እስኪፈጸም ድረስ ደቀመዛሙርቱ አላስተዋሉም ነበር።

*«የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ ወደ ኢየሩሣሌም ለመሔድ ፊቱን አቀና» (ሉቃ.9:51)*።

በህዝብ ፊት ያሰው ምድራዊ ህይወቱ በኢየሩሣሌም የሚያበቃ ነበር። አባቱ የሰጠውንም ሥራ ለመፈጸም /ለመጨረስ/ ፈቃደኛ ነበር። (*ዮሐ.4:34*)

**ጌቴሴማኒ**

ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻ የምድራዊ ህይወቱን ምሽት በጌቴሴማኒ ከደቀመዛሙርቱ ጋር አሳለፈ። በዚያ ስለ ኃጢአታችን ከውስጥ በሆነ ስቃይ በታማኝነት ተሰቃየ። ላቡ በምድር ላይ እንደ ደም ነጠብጣብ ወረደ (*ሉቃ.22:44*)፡ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሆነው ያስቆሮቱ ይሁዳ ወደ ካህናት አለቆች ሔደና ካደው። ወዲያውኑ የካህንት አሰቆች ኢየሱስን ያዙትና አሰሩት። በዚህም ደቀ መዛሙርቱ ብቻውን ትተውት ሸሹ (*ማቴ.26:56*)። የካህናት አሰቆችና የሸንጎው አባሉች እርሱን ሰመግደል የሐሰት ምስክሮች ለመፈለግ ወደ ተሰበሰቡበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ቤተ መንግሥት አመጡት (*ማቴ.26:59*)። በምንም ነገር ጥፋተኛ ሆኖ ስላልተገኘ በመጨረሻ ከእርሱ ምክንያትን ለመፈለግ ሊቀ ካህናቱ ጌታን እንዲናገረው ገፋፋው «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደሆን እንድትነግረን በህያው እግዚአብሔር አሰምንሃለሁ አለው» ኢየሱስም

*«አንተ አልህ፣ ነገር ግን እላችኋለሁ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ፣ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ» አለው። «በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀድዶ ተሳድቦአል። ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ስለ ምን ያስፈልጋል? እነሆ ስድቡን አሁን ሰምታችኋል፣ ምን ይመስላችኋል?» አለ (ማቴ.26:63-65)* ።

ሊቀ ካህናቱ ልብሱን እንዲቀድድ አልተፈቀደለትም ነበር። እግዚአብሔር ይህን በግልጽ ከልክሎ ነበር (*ዘሌ.21:10*)፡ ስለሆነም ሊቀ ካህናቱ ያደረገው የተከለከለውን ነበር። ሊቀ ካህናቱ በእግዚአብሔር የተቀባና ቅዱስ የቅባት ዘይት የፈሰሰበት ነበር። (*ዘሌ.21:10*) ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ልብሱን በመቅደዱ በአጠቃላይ በብሉይ ኪዳን ያለው የአሮንን ክህነት ሥርዓት በምሳሌ ማፍረሱን ነበር። ብቸኛ፣ እውነተኛና ዘላለማዊ ሊቀ ካህናት በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አንጻር ቆሞ ነበር ይህን ያደረገው (*መዝ.(110):4፤ ዕብ.5:5-10*)።

**ገ በ ታ**

ከሊቀ ካህናት ከቀያፋ ፊት የእግዚአብሔርን ልጅ ወደ ግቢ /ፕራይቶሪዮን/ ወሰዱት (*ዮሐ. 18:28*) ይህን ስፍራ የገዢው ግቢ ይሰዋል። ፕራይቶሪዮን በዚያን ጊዜ የይሁዳ ገዢ እንዲሆን በሮሙ ንጉስ በጢበርዮስ የተሾመው የጲላጦስ መኖሪያ





ነበር። የሮም ንጉሥ የምድር ንጉሥ ነበር። ይህ የሮም ንጉሥ በየቀኑ የጁፒተርን ጣዖት በማምለክ ለይጣንን ያመልክ ነበር። እንደዚሁም ደግሞ እርሱ በሚገዛው ግዛት ሁሉ የበላይ ገዢ በመደረግ ይመለክ ነበር። በግሪኩ የኢኩሚኒ መልካም አምላክ የዚህ ገዢ የበታች እንደራሴ በመሆን ጴንጤናዊው ጌታ ኢየሱስን በሚከተለው መንገድ መመርመር ጀመረ።

*«የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?» አለው። ኢየሱስም መልሶ መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም አለው ጲላጦስም እንግዲህ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ እኔ ንጉስ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሠክር ተወልጃለሁ። ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምጼን ይሰማል አለው» (ዮሐ.18:33፣ 36፣ 37)።*

ያ የሥልጣን ወቅት ነበር። ምክንያቱም በሮማውያን ገዢ ፊት ከላይ የሆነው ሰማያዊ ንጉሥ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ሆኖ ሲታይ በሌላ በኩል ደግሞ ከታች የሆነው የሰይጣንን መንግሥት የሮምን መንግሥት የወከለው ጴንጤናዊው ጲላጦስ ይታያል። በውጪ ደግሞ የእሥራኤል ህዝብ ሊቀ ካህናት ውሳኔ እንዲደረግ እየጠየቁ ይጠባበቁ ነበር። ጌታ ኢየሱስን ባዩት ቁጥር «ስቀለው ስቀለው እያሉ ይጮሁ ነበር» (*ዮሐ. 19:6*)። ጲላጦስ ሦስት ጊዜ «በደል አላገኘሁበትም» ብሎ ስለ እርሱ ቢመሠክርም ሊሰሙት አልፈለጉም ነበር (*ሉቃ.23:4፣14፣22፤ ዮሐ.18:38፣ 19:4-6*)። ከዚህ በኋላ ጲላጦስን እጅግ አጽንተው «ስቀለው፣ ስቀለው፡ ከሚለው ጩኸታቸው ጋር እንዲተባበሩ ህዝቡን አነሳሱና አደፋፈሯቸው። ጌታ ኢየሱስን ወደ ውጪ አውጥቶላቸው «እነሆ ሰውየው» አላቸው (*ዮሐ.19:5*)። ጲላጦስ ግን ከፊቱ የቆመው ማን እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። እርሱ ከብዙ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች ፊት ሰፊት የቆመ ነበር። ክርስቶስ ግን ያለ ኃጢዓትና የተለየ ፍፁም ሰው ነበር። ይህ ሰው እውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። ጲላጦስ በፍርሃት ተሞልቶ ሊፈታው ፈልጎ ሳለ አይሁድ «ይህንንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም» ብለው ጮኹ (*ዮሐ.19:12*)። «የሮም ንጉሥ የቄሣር ወዳጅ» /አሚኩስ ሴሳሪስ-AMICUS CAESARIS/ የሚለውን ማዕረግ ስጥቂት ከፍተኛ ማዕረግ ላላቸው የሚሰጣቸው ስለነበር በዚህ «ማዕረግ» ጲላጦስን በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ከተቱት። ጲላጦስም የሮም ንጉሥ የክላውዲያ ፕሮኩላን የመጀመሪያ ልጅ የሆነችውን ቀላውዲያ ፕሮኩላንን አግብቶ ስለነበር ይህ ማዕረግ ተሰጥቶት ነበር። ይህች ሴት በማቴዎስ ወንጌል «ስለ እርሱ ዛሬ በህልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁ በዚያ ፃዲቅ ሰው ምንም አታድርግ» ያለችው ሴት እንደሆነች

ይታወቃል (*ማቴ.27:19*)፡፡ እርሱም ለማስጠንቀቂያው ዋጋ ሳይሰጥና ተወዳጅነቱን እንዳያጣ ያለው ሥልጣን ለሚቀጥለውም ርምጃ ተገዢ አደረገው፡፡

*«ኢየሱስን ወደ ውጪ አስወጣው፡፡ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለ ለቁስ በሚሉት ሥፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ፡፡ ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበር፣ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበር፡፡ አይሁድንም «እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው፡፡ እነርሱ ግን «አስወግደው፣ አስወግደው፣ ስቀለው» እያሉ ጮኹ፡፡ ጲላጦስም «ንጉሣችሁን ልሰቀለውን?» ብሎ ሲጠይቃቸው የካህናት አለቆችም «ከቄሳር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም» ብለው መለሱለት (ዮሐ.19:13-15)፡፡*

በሮማውያን መንግሥት ንጉሥን መስቀል የማይታሰብ ሲሆን ወንጀለኞች ግን ይሰቀሉ ነበር፡፡ የተማረኩ ነገሥታት እንኳን በሮማውያን ህግ እንገታቸው ይቆረጥ ነበር እንጂ አይሰቀሉም ነበር፡፡ የሮም ዜግነት ያለው ደግሞ በዚህ መንገድ አይገደልም ነበር፡፡ በተለይም ሴቶች በዚህ መንገድ አይገደሉም ነበር፡፡ ምክንያቱም ሮማውያን ባህል አክባሪ ዜጎች ስለነበሩ ነው፡፡ አይሁድ «ሰቀለው» እያሉ በከፍተኛ ጩኸት በመጮሃቸው ምርመራውም ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ ጲላጦበ በሐዘን «ንጉሣችሁን ልስቀለውን ?» ብሎ ጮኾ ሊቀ ካህናትም *«ከቄሳር በቀር ንጉሥ የለምን» ብለው መለሱለት (ዮሐ.19:15)*
ይህ የመደምደሚያ ውሳኔ እሥራኤል ያስችበትን አደገኛ ሁኔታ ይገልፁ ነበር፡፡ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ልጅ ለራሳቸው ውሳኔ እንዳያደርጉ ይገፋፋሉ፡፡ እርሱን መምረጥ ወይም መቃወም እንጂ ሌላ መካከለኛ አማራጭ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ጌታ *«ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል» በማለቱ ነው (ማቴ.12:30)፡፡*

ይህ አባባል ለእሥራኤል የላይኛውን ንጉሥ መቃወም የታችኛውን ምድራዊ ንጉሥ መምረጥ ማለት ነው፡፡ የታችኛው መንግሥት ራሱ ሰይጣን ነው፡፡

*እሥራኤል ንጉሥ የሌላት ለምንድን ነው?*

መልሱን የምናገኘው አስቸጋሪ ከሆነው ከዚህ ሕዝብ ታሪክ ነው፡፡ እሥራኤል ለእግዚአብሔር የተመረጠ ህዝብ ቢሆኑም ለብዙ መቶ ዓመታት ጣዖታትን ማምለክ የተለማመዱና «መልካም ባልሆነው በራሳቸው መንገድ የሚሄዱ አመጸኛ ህዝቦች ነበሩ» (*ኢሣ.65:2*)፡፡ እነዚህ ህዝቦች ራሳቸውን ለጣዖት አምልኮ በመበጠታቸው እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያስቆጡት ነበር (*ኢሣ.65:3*)፡፡ ጳውሎስ ስለ እሥራኤል ህዝብ በሮሜ መልዕክት *«ለእግዚአብሔር ቀናተኛ እንደ ሆኑ ስለ እነርሱ · መመስከር እችላለሁና ቅናታቸው ግን ከዕውቀት የተነሳ አይደለም፡፡*





*ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ጽድቅ ስላላወቁና የራሳቸውን ጽድቅ ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም» (ሮሜ.10:2-3)* በማለት ጽፏል፡፡ ኃጢዓት አሳውሯቸው ነበር ውጤቱም«ንጉሥ የለንም» የሚል ነበር፡፡ ይህ ከፍተኛው አደገኛ ነጥብ ነበር እሥራኤል ንጉሥ ነበራት፣ በእግዚአብሔር ልጅ በጌታ ኢየሱስ ይህ ንጉሥ በአይናቸው ፊት ቆሞ ነበር፡፡ እሥራኤል በጣዖት አምልኮ ስለተጠመደችና በሰይጣን ኃይል የተያዙና ህዝቡም ንስሐ የማይገቡና የታወሩ ስለነበሩ ንጉሣቸውንና መሲሃቸውን ለማወቅ አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህ የሊቀ ካህናቱ ውሳኔ መሐል ሰፋሪነት የሌለው ነበር፡፡ «ከቄሣር በቀር ንጉሥ የለንም» የሚለው ለእግዚአብሔር «አይደለም» ለሰይጣን «አዎን» ማለት ነበር፡፡ ስለዚህ ምክንያት ነበር አዳኙ «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁና የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበር» ያላቸው (*ዮሐ.8:44*)፡፡

ምርመራው ወደ ፍጻሜ ደረሰ፡፡ አይሁድም ጲላጦስ ላይ ብዙ ጫና አደረጉ፣ ጩኸታቸውም የሚያውክ ሆነ (*ሉቃ.23:23*)፡፡ በመጨረሻም ጲላጦስ ለህዝቡ ጫና ራሱን አስገዝቶ ኢየሱስን እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ (*ዮሐ.19:16*)

## ጎ ል ጎ ታ

*«ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፣ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ሥፍራ ወደሚሉት ወጣ፡፡ በዚያም ሰቀሉት፡፡ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ አድርገው ኢየሱስንም በመካከላቸው በማድረግ ሰቀሉት» (ዮሐ.19:17-18)፡፡*

እሥራኤል መሲኋን ካደች እንደ ማንኛውም ወንጀለኛ በሁለት ነፍሰ ገዳዮች መካከል ተሰቀለ፡፡ ሆኖም የእሥራኤል ንጉሥ መሆኑን የቀየረው ምንም ነገር አልነበረም እርሱ ለዘለዓለም ንጉሥ ሆኖ ይኖራል፡፡ ስለሆነም ጲላጦስ በዕብራይስጥ በሮማይስጥና በግሪክ ማንነቱን የሚያስታውቅ ጽሁፈት በመስቀሉ ላይ ሰቀለ፡፡ ቃሉም

«የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ» የሚል ሲሆን

*በብሔራዊ ቋንቋቸው በዕብራይስጥ*

«ቫሹዋ ሀ ኖዛሪ ሜልኬ ሀ ጂሁዲም»»

*በሮማውያን ብሔራዊ ቋንቋቸው*

«ጂሱስ ናዝሪኑስ ዴክስ ኢሽዳእሩም»

*በግሪክ ብሔራዊ ቋንቋ ደግሞ*
«ኢየሱስ ሆ ናዝራዮስ ሆ ባሲሊዮስ ቶን አይሁዳዮን» የሚል ነበር::

የአይሁድ ንጉስ ስለ ኃጢዓታችን ለመሞት ወደ ዓለም የሚመጣው የዓለም መድሃኒትና የእግዚአብሔር ልጅ ነው:: እርሱም *«ለሞት ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን ለሰማይ አባቱ የሚታዘዝ ሆነ» (ፊል.2:8)*: ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የእባቡን ራስ ቀጠቀጠ *(ዘፍ.3:15)*: በጎልጎታ በመስቀል ላይ ኃጢዓትንና ሞትን አሸነፈ:: ኃጢዓተኞች የሚድኑበትን ብቸኛ ሁኔታ ፈጠረ::

እግዚአብሔር የደህንነት *ታሪክ* ሁልጊዜ ዘለዓለማዊነትን የሚናገር ነው *(ዕብ.9:12)*: የእሥራኤል ህዝብ የፈስጉትና በተስፋ የጠበቁት ከሮማውያን ባርነት ነፃ የሚያወጣቸውን ምድራዊ መሲህና ደህንነት ነበር::

ወንድም ሆነ ሴት ከውስጥ የሰይጣን ባሪያ ሆነው ዘለዓለማዊ ሠላም ቢኖራቸው ምን መልካምነት አለው? እሥራኤልም ብትሆን ያለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዳን አይቻላትም:: እርግጥ ነው እግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅዱን በራሱ ህዝብ በኩል ተጠቅሟል:: በእነርሱ በኩል ልጁ ሰው ሆኖ እንዲመጣና የመዋጀት ስራውን በምድር እንዲፈጽም አድርጓል:: ነገር ግን ለእሥራኤል መንግስት ሰማይ ለመግባት የኋላ በር ወይም የተለየ በር የላቸውም «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» የሚለው ጥቅስ ማንኛውንም ሰውና የተመረጡትን የእሥራኤል ዘር እንኳን ሳይቀር የሚመለከት ነው *(ዮሐ.14:6)*::

መሲኋን በመቃወሟ ከእሥራኤል ጋር ያሰው የእግዚአብሔር የመዋጀት ስራ ለጥቂት ጊዜ ተቋረጠ:: «ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ» (ማር.1:15) ብሎ ጥሪ ለሰጠው ለመሲሁ ጥሪ የእግዚአብሔር ህዝብ የሰጡት ምላሽ ንጉሳቸውን መስቀል ነበር:: በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቀይ መስመር ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ ዝቅ እያለ መሄዱ ይታያል:: ነገር ግን ይህ ማለት የእግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ በዚህ አበቃ ማለት አይደለም:: እሥራኤል በክርስቶስ የሆነውን ደህንነት ብትቃወምም ደህንነት ከእሥራኤል ውጪ ላሉት ህዝቦች የሚሰበክ ሆነ:: ለ2 ሺህ ዓመታት ይህ በመላው ዓለም እስከ አሁን እየተካሄደ ነው በዚህ ሁኔታ ነው ወንጌል ወደ አውሮፓም የደረሰው:: ስለዚህ ጌታችንን ልናወድሰውና ልናመስግነው ይገባናል::

ከዘፍ.12 እስከ ሐሥ.12 ድረስ ስለ ልጁ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲል እግዚአብሔር በተለይ ከእሥራኤል ምድርና ህዝብ ጋር በተያያዘ የመዋጀትን ታሪክ እንደሠራ ይታያል:: ከሐሥ.13 ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ ጉዞዎች ወንጌል እስከ ምድር ዳር ድረስ ለአህዛብ መሰበኩን ያሳያል (ሐሥ.1:8):: የእሥራኤል ህዝቦች በምድራዊ ገዢ ተወስዱና ከእግዚአብሔር የመዋጀት ታሪክ ወደ ጎን ተተዉ::





## 3. አረንጓዴው የመዋጀት መሥመር


# የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

### አጭር እይታ

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሦስተኛው ክፍል (ህዝብ) የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ይህ ክፍል በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ሰፊ በሆነ አረንጓዴ መስመር የተመለከተው ነው::

በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ይኖሩ የነበሩት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሦስተኛ ትውልድ አድርገው ሰይመዋት ነበር:: እነዚህ ሦስቱ ክፍሎች አህዛብ በአብርሃም መመረጥ በኩል የመጡት የእሥራኤል ህዝብ አይሁድና በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሆኑት ክርስቲያኖች ናቸው:: እነዚህ ሦስቱ የህዝብ ክፍሎች ዛሬም በዓለም ውስጥ ይገኛሉ::

*«እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ»* የሚለውን አረንጓዴው መሥመር በምንመረምርበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መምጣቱን ተመልክተናል::



*በግሪክ ብሔራዊ ቋንቋ ደግሞ*
«ኢየሱስ ሆ ናዝራዮስ ሆ ባሲሊዮስ ቶን አይሁዳዮን» የሚል ነበር።

የአይሁድ ንጉስ ስለ ኃጢዓታችን ለመሞት ወደ ዓለም የሚመጣው የዓለም መድሃኒትና የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እርሱም *«ለሞት ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን ለሰማይ አባቱ የሚታዘዝ ሆነ» (ፊል.2፡8)*፡ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የእባቡን ራስ ቀጠቀጠ *(ዘፍ.3፡15)*፡ በጎልጎታ በመስቀል ላይ ኃጢዓትንና ሞትን አሸነፈ። ኃጢዓተኞች የሚድኑበትን ብቸኛ ሁኔታ ፈጠረ።

እግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ ሁልጊዜ ዘለዓለማዊነትን የሚናገር ነው *(ዕብ.9፡12)*፡ የእሥራኤል ህዝብ የፈስጉትና በተስፋ የጠበቁት ከሮማውያን ባርነት ነፃ የሚያወጣቸውን ምድራዊ መሲህና ደህንነት ነበር።

ወንድም ሆነ ሴት ከውስጥ የሰይጣን ባሪያ ሆነው ዘለዓለማዊ ሠላም ቢኖራቸው ምን መልካምነት አለው? እሥራኤልም ብትሆን ያለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዳን አይቻላትም። እርግጥ ነው እግዚአብሔር የመዋጀት ዕቅዱን በራሱ ህዝብ በኩል ተጠቅሟል። በእነርሱ በኩል ልጁ ሰው ሆኖ እንዲመጣና የመዋጀት ስራውን በምድር እንዲፈጽም አድርጓል። ነገር ግን ለእሥራኤል መንግስት ሰማይ ለመግባት የኋላ በር ወይም የተለየ በር የላቸውም «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» የሚለው ጥቅስ ማንኛውንም ሰውና የተመረጡትን የእሥራኤል ዘር እንኳን ሳይቀር የሚመለከት ነው *(ዮሐ.14፡6)*።

መሲኋን በመቃወሟ ከእሥራኤል ጋር ያለው የእግዚአብሔር የመዋጀት ስራ ለጥቂት ጊዜ ተቋረጠ። «ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ» (ማር.1:15) ብሎ ጥሪ ለሰጠው ለመሲሁ ጥሪ የእግዚአብሔር ህዝብ የሰጡት ምላሽ ንጉሳቸውን መስቀል ነበር። በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቀይ መስመር ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ ዝቅ እያለ መሄዱ ይታያል። ነገር ግን ይህ ማለት የእግዚአብሔር የደህንነት ታሪክ በዚህ አበቃ ማለት አይደለም። እሥራኤል በክርስቶስ የሆነውን ደህንነት ብትቃወምም ደህንነት ከእሥራኤል ውጪ ላሉት ህዝቦች የሚሰበክ ሆነ። ለ2 ሺህ ዓመታት ይህ በመላው ዓለም እስከ አሁን እየተካሄደ ነው በዚህ ሁኔታ ነው ወንጌል ወደ አውሮፓም የደረሰው። ስለዚህ ጌታችንን ልናወድሰውና ልናመስግነው ይገባናል።

ከዘፍ.12 እስከ ሐሥ.12 ድረስ ስለ ልጁ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲል እግዚአብሔር በተለይ ከእሥራኤል ምድርና ህዝብ ጋር በተያያዘ የመዋጀትን ታሪክ እንደሠራ ይታያል። ከሐሥ.13 ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያው ጳውሎስ ጉዞዎች ወንጌል እስከ ምድር ዳር ድረስ ለአህዛብ መስበኩን ያሳያል (ሐሥ.1:8)። የእሥራኤል ህዝቦች በምድራዊ ገዢ ተወሰዱና ከእግዚአብሔር የመዋጀት ታሪክ ወደ ጎን ተተዉ።





## 3. *አረንጓዴው የመዋጀት መሥመር*
## የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን

### አጭር እይታ

በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ሦስተኛው ክፍል (ህዝብ) የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህ ክፍል በደህንነት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ስፊ በሆነ አረንጓዴ መስመር የተመለከተው ነው።

በሁለተኛውና በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ይኖሩ የነበሩት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ቤተ ክርስቲያንን እንደ ሦስተኛ ትውልድ አድርገው ሰይመዋት ነበር። እነዚህ ሦስቱ ክፍሎች አህዛብ በአብርሃም መመረጥ በኩል የመጡት የእሥራኤል ህዝብ አይሁድና በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሆኑት ክርስቲያኖች ናቸው። እነዚህ ሦስቱ የህዝብ ክፍሎች ዛሬም በዓለም ውስጥ ይገኛሉ።

«*እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ*» የሚለውን አረንጓዴው መሥመር በምንመረምርበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስ መምጣቱን ተመልክተናል።



ይህ የሆነው በበዓለ ሃምሳ /ጴንጤቆስጤ/ ዕለት በኢየሩሳሌም ነበር:: (*የሐሥ.2:1-3*) ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ዕለት ነበር:: ከዚህ እለት ጀምሮ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በዓለም ዙሪያ በያለበት ወንጌልን ለመስበክ ወጡ:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር ቃል ስብከት በኩል እጅግ ብዙ ለዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ጀመሩ:: ከ2000 ዓመታት ጀምሮ ወንጌል አሸናፊ ሆነ:: ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ እውነተኛ መለወጥ ባገኘ ቁጥር የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን እያደገች ትሄዳለች:: እኛ አሁን ያለነው በአህዛብ ዘመን /በአህዛብ ቤተ ክርስቲያን ዘመን/ ውስጥ ነው::

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዳግም የተወለዱትን አማኞች ያቀፈች አካል ናት:: ለጠፋው ኃጢዓተኛ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ዳግም ልደት መቅደም አስፈላጊው ነገር ነው:: ለዚህ ነው ዩሐንስ ሐዋርያው *«ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም»* በማለት የፃፈው (*ዮሐ.3:33 ከዮሐ.3:5 )ጋር አስተያይ::*

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ዳግም የተወለዱት አማኞች የመጡት ከአህዛብ ወይም ከአይሁድ ነው:: በጌታ ክርስቶስ ኢየሱስ እምነታቸውን ያደረጉት ሰዎች ከአህዛብ ብቻ ሳይሆን ከእሥራኤልም ህዝብ ጭምር ናቸው:: በሉቃስ የተጻፈው የሐዋሪያት ሥራ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን 21 መልእክቶች ጋር ለኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ጽሑፎች ናቸው:: እነዚህ መፃሕፍት ከክርስቶስ ኢየሱስ የመዋጀት ስራ በተጨማሪ አማኙ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስላለው ግብረ ገባዊ ኑሮና አምልኮ ያመለክታሉ:: እነዚህ መፅሐፍት ደግሞ እያንዳንዱ አማኝ ወንድም ሆነ ሴት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በግል ስላላቸው ጉዞ ያስተምራሉ::

የቤተ ክርስቲያን ዘመን የተወሰነ ነው:: ወደ ፍጻሜው የሚደርሰው ጌታ ዳግም የተወለዱትን አማኞች ከምድር ወደ ሰማያዊ ክብር መጥቶ በሚነጥቅበትና በሚወስዳት ጊዜ ነው በራሱ ደም የገዛት ሃብቱ ናትና:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እውነተኛ አማኞች ከጌታ ጋር ለዘላለም ይኖራሉ (*1ተሰ.4:17*):: በአረንጓዴው የመዋጀት መሥመር መጨረሻ ላይ ያለው የጥያቄ ምልክት የመነጠቅን ጊዜ የሚያመለክት ነው:: መነጠቅ የሚሆንበትን ትክክለኛ ቀን መናገር የማይቻል ነው::





## የቤተክርስቲያን ዘመን

### 1. ዓለም አቀፍ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን

በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተ ክርስቲያን 100 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል:: በመጀመሪያው በግሪኩ ትርጉም «ኤክሊሺያ» «*ተጠርተው የወጡ*» የሚለው ቃል ቤተ ክርስቲያንን ለመግለጽ ሐዋርያት /የመፅሐፍ ቅዱስ ደራሲያን/ የተጠቀሙበት ቃል ነበር:: አዲስ ኪዳን ይህን ቃል ከጠፋውና በኃጢዓት ከተሞላው ዓለም ተጠርተው የወጡ በጌታ ኢየሱስ ያመኑትን ለማመልከት ተጠቅሞበታል:: «የእምነታችን ጀማሪና ፈፃሚ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ የመጡ ናቸው» (*ዕብ.12:2*)::

### የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ከአይሁድና ከአህዛብ

ቤተ ክርስቲያን ዳግም የተወለዱ አማኞች ስብስብ ናት:: በአይሁድና በአህዛብ መካከል ልዩነት የለም:: እስከ ዛሬ ድረስ ከእነዚህ ከሁለት ክፍሎች የሚድኑትን ህዝቦች ጌታ በየቀኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ እየጨመረ ነው:: (ሐሥ. 2:47) በገላትያ መፅሐፍ እንደተፃፈው

*«አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባርያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ» ከሚለው እናነባለን (ገላ.3:28)::*

የሰው የትውልድ ማንነት በደህንነቱ ምንም መለያ የማያደርግ ነው:: አይሁድ በአካልና በዝርያ አይሁድ ሆነው ነው የሚኖሩት:: ስለዚህም ነው ጳውሎስ አህዛብን ግሪኮች ያላቸው:: ይህም የተለመደው አሕዛብ የሚጠሩበት የመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ነው:: የሰው የአንድ አገር ዜጋ /ተወላጅ/ መሆኑና የቆዳው መልክ ለደህንነት አስፈላጊ አይደለም:: በዚህ በምድር ሕይወት ብቻ ወንድና ሴት እንለያለን :: ከሞት በኋላ ጾታችን አይታይም:: በእግዚአሔር ፊት ዋጋ ያለው አዲስ ፍጥረት መሆን እንጂ ሌላው አይጠቅምም:: (*ገላ. 6:15*) በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም በመወለድ አዲስ ፍጥረት እንሆናለን:: በዳግም ልደት ብቻ ነው የቤተ ክርስቲያን አባል የምንሆነው::

### የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አምላካዊ ሚስጢር

ቤተ ክርስቲያን ምስጢር የሆነች ናት:: ከብሉይ ኪዳን ስለ ቤተ ክርስቲያን በግልፅ ያየ ነቢይ የለም:: ይህ ምስጢር በተለየ መንገድ የተገለጸው ለሐዋሪያው ጳውሎስ ነበር (*ኤፌ.3:3-6*):: (ቤተ ክርስቲያንን አስደናቂ ምስጢርና ፍጥረት የሚያደርጋት «ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው» (*ቆላ.1:18*)::)

*«እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ። እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ» (1ቆሮ.12:27)* የሚለው ቃል መፃፉ ነው ቤተክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በሰማይም በምድርም አለች።

ስለዚህ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስና ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል የሆነች ናት። በ *ኤፌ.5:30* ዳግም የተወለደውን የቤተ ክርስቲያንን አባል «የአካሉ ብልት ነን» በማለት ይገልጸዋል።

ይህ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አማኞች ያላቸው የማይነጠል ሰማያዊ ህብረት እግዚአብሔር ሊሰጥ ካለው ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ስጦታ ነው። ሰዎች በክርስቶስ ዳግም ሲወለዱ ምን እንደሚሆኑና ምን እንደሚፈጠር አያውቁም። በሰማይና በምድር ወደ ተከበረው ወደ ክርስቶስ ከመጡ በኋላ እግዚአብሔር አብ ሰማያዊ ዓለም ወደ ሆነው ወደ ልጁ መንግሥት ያስገባቸዋል (ቆላ. 1:13)። በመንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል ያደርጋቸዋል። በፍጥረት ላይ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ (ቆላ. 1:18)።

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ለዘላለም የማትሸነፈው

ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ህብረት /ሕይወት ያለት ድርጅት/ እንደመሆኗ መጠን ሰማያዊ ተስፋዎችና ጥቂት ምድራዊ ተስፋዎችም አሏት። የገሃነም ደጆች ቤተ ክርስቲያንን ከቶ ሊቋቋሟት አይችሉም (*ማቴ.16:18*)። የጥንቱ የሮም መንግሥት ገሃነም በቅርቡ የወደቀው የኮሚኒስት ብሎክ ገሃነም፣ የአዶልፍ ሂትለር ገሃነም፣ የንጉሥ ኔሮ ገሃነም ቤተ ክርስቲያንን ሊያሸንፏት አልቻሉም። ቤተ ክርስቲያን «በአለቅነትና በሥልጣንም ላይ ራስ ከሆነው» ከክርስቶስ የተጣበቀች ናት (ቆላ.2:10)። ስለዚህ ነው አዳኙ «ሥጋን የሚገድሉት ነገር ግን ነፍስን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ» ያለው (*ማቴ.10:28*)። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ የማትሸነፍ ናት። በቀራንዮ የድል እግር ስር በክርስቶስ አሸናፊነት ላይ ለዘላለም የተመሠረተች ነች። ምክንያቱም « ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሰርት አይችልምና፣መሠረቱም እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (*1ቆሮ. 3:11*)።

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ከዚህ ዓለም ያልሆነችው

እስከ አሁን በተደረገው ገለፃ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ምንም ትስስር እንደሌላት በግልጽ ታይቷል። በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያመለክተው ሰፊው አረንጓዴው መሥመር የሰውን ዘር ከሚያመለክቱት ሁለት መሥመሮች በላይ የተደረገ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከምድር ህዝቦችና ከምድራዊ እሥራኤል በላይ በጣም ከፍ ያለች ናት። ያልዳኑት ህዝቦች ወደ ሚያስፈራው ጨለማ ዘመን እየደረሱ ላሉ የተመረጠችው እሥራኤል ደግሞ





እስከ አሁን ድረስ ምድራዊ ተስፋዎችን እንደያዘች ናት። ቤተ ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር ልጅ «ትልቅና ክቡር የሆኑ ተስፋዎች ተሰጥቷታል» (*2ጴጥ.1:4*)። ስለዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከዓለምና ከእሥራኤል ጋር የበዛ ምድራዊ ትስስር የላትም። በክርስቶስ ፍጹምና ሰማያዊ ናት። ስለሆነም አማኙ በሥጋ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት ምንም ልዩነት የለውም። ዋነኛው ነገር አማኙ «አዲስ ፍጥረት» መሆኑ ነው (*2ቆሮ.5:17*)። አስፈላጊው ቁም ነገር አማኙ በዳግም ልደት በኩል የክርስቶስ አባል መሆኑ ነው። ስለዚህ አማኞች የብሉይ ኪዳን ወደ ሆነው ወደ ሙሴ ህግ፣ በኃጢአት ወደ ተሞላው ዓለምና ስመ ክርስትና ኖሯቸው እምነታቸው ሙት ወደ ሆኑት መመለስ የለባቸውም። ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ስትተባበር ውጤቱ «ጋለሞታይቱ ባቢሎን» መሆን ነው። አንድ ቀን ጋለሞታይቱ ባቢሎን እንደምትገለጥ እናውቃለን (*ራዕ.* 17 እና 18)። ነገር ግን እኛ እውነተኛ አማኞች በመሆን ለቤተ ክርስቲያን የሆንን ነን። ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ህግ ስር መሆን ከቶ አያስፈልገንም። ያም ማለት እግዚአብሔር ለእሥራኤል ከሰጠው ሕግ ስር ልንሆንና በኢየሩሳሌም ይሰዋ ከነበረው የእንስሳ ደም መስዋዕት ተካፋዮች መሆን አይገባንም ማለት ነው። በዚህ አውድ የዕብራውያን መልዕክት የሚከተሉትን ያመለክታል።

| | |
|---|---|
| ክርስቶስ ከመላእክት የበለጠ | *ዕብ.1 እና 2* |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |
| [illegible] | [illegible] |

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ራዕይ /መገለጥ/ ከራዕዮች ሁሉ የበለጠና እጅግ የከበረ ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለእሥራኤል ህዝብ የሰጣቸው የወደፊቱን የመዋጀት ስራ ጥላ ብቻ ነበር። የዚህ የመዋጀት ጥልቅ ሀቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር (*ቆላ.2:16-17 ፤ ዕብ.10:1*)። የብሉይ ኪዳን ውጭዓዊ ገጽታ እውነተኛውን አዳኛችንን ክርስቶስን ያሳያል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ህግ ማንንም ለማዳን የማይቻለው ነበር። ሰው በህግ በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ፣ በብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች በኩል መዳን ቢችል ኖሮ የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ከንቱ ይሆን ነበር። በደሙ የዳኑና በዳግም ልደት ወደ ቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ

«እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ። እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ» *(1ቆሮ.12:27)* የሚለው ቃል መፃፉ ነው ቤተክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ በሰማይም በምድርም አለች።

ስለዚህ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስና ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል የሆነች ናት። በ *ኤፌ.5:30* ዳግም የተወለደውን የቤተ ክርስቲያንን አባል «የአካሉ ብልት ነን» በማለት ይገልጸዋል።

ይህ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አማኞች ያላቸው የማይነጠል ሰማያዊ ህብረት እግዚአብሔር ሊሰጥ ካለው ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነ ስጦታ ነው። ሰዎች በክርስቶስ ዳግም ሲወለዱ ምን እንደሚሆኑና ምን እንደሚፈጠር አያውቁም። በሰማይና በምድር ወደ ተከበረው ወደ ክርስቶስ ከመጡ በኋላ እግዚአብሔር አብ ሰማያዊ ዓለም ወደ ሆነው ወደ ልጁ መንግሥት ያስገባቸዋል (ቆላ. 1:13)። በመንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ሆነችው ቤተ ክርስቲያን አባል ያደርጋቸዋል። በፍጥረት ላይ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ (ቆላ. 1:18)።

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ለዘላለም የማትሸነፈው

ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ ህብረት /ሕይወት ያለት ድርጅት/ እንደመሆኗ መጠን ሰማያዊ ተስፋዎችና ጥቂት ምድራዊ ተስፋዎችም አሏት። የገሃነም ደጆች ቤተ ክርስቲያንን ከቶ ሊቋቋሟት አይችሉም *(ማቴ.16:18)*። የጥንቱ የሮም መንግሥት ገሃነም፣ በቅርቡ የወደቀው የኮሚኒስት ብሎክ ገሃነም፣ የአዶልፍ ሂትለር ገሃነም፣ የንጉሥ ኔሮ ገሃነም ቤተ ክርስቲያንን ሊያሸንፏት አልቻሉም። ቤተ ክርስቲያን «በአለቅነትና በሥልጣንም ላይ ራስ ከሆነው» ከክርስቶስ የተጣበቀች ናት (ቆላ.2:10)። ስለዚህ ነው አዳኙ «ሥጋን የሚገድሉት ነገር ግን ነፍስን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ» ያለው *(ማቴ.10:28)*። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ላይ የማትሸነፍ ናት። በቀራንዮ የድል እግር ስር በክርስቶስ አሸናፊነት ላይ ለዘላለም የተመሠረተች ነች። ምክንያቱም « ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሰርት አይችልምና፣መሠረቱም እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» *(1ቆሮ. 3:11)*።

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን - ከዚህ ዓለም ያልሆነችው

እስከ አሁን በተደረገው ገለፃ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ምንም ትስስር እንደሌላት በግልጽ ታይቷል። በመዋጀት ዕቅድ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚያመለክተው ሰፊው አረንጓዴው መሥመር የሰውን ዘር ከሚያመለክቱት ሁለት መሥመሮች በላይ የተደረገ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከምድር ህዝቦችና ከምድራዊ እሥራኤል በላይ በጣም ከፍ ያለች ናት። ያልዳኑት ህዝቦች ወደ ሚያስፈራው ጨለማ ዘመን እየደረሱ ሳሉ የተመረጠችው እሥራኤል ደግሞ





እስከ አሁን ድረስ ምድራዊ ተስፋዎችን እንደያዘች ናት። ቤተ ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር ልጅ «ትልቅና ክቡር የሆኑ ተስፋዎች ተሰጥቷታል» *(2ጴጥ.1:4)*። ስለዚህም ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ከዓለምና ከእሥራኤል ጋር የበዛ ምድራዊ ትስስር የላትም። በክርስቶስ ፍጹምና ሰማያዊ ናት። ስለሆነም አማኙ በሥጋ አይሁዳዊ ወይም አህዛብ ቢሆን በእግዚአብሔር ፊት ምንም ልዩነት የለውም። ዋነኛ ው ነገር አማኙ «አዲስ ፍጥረት» መሆኑ ነው *(2ቆሮ.5:17)*። አስፈላጊው ቁም ነገር አማኙ በዳግም ልደት በኩል የክርስቶስ አባል መሆኑ ነው። ስለዚህ አማኞች የብሉይ ኪዳን ወደ ሆነው ወደ ሙሴ ህግ፣ በኃጢአት ወደ ተሞላው ዓለምና ስመ ክርስትና ኖሯቸው እምነታቸው ሙት ወደ ሆኑት መመለስ የለባቸውም። ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ስትተባበር ውጤቱ «ጋለሞታይቱ ባቢሎን» መሆን ነው። አንድ ቀን ጋለሞታይቱ ባቢሎን እንደምትገለጥ እናውቃለን (ራዕ. 17 እና 18)። ነገር ግን እኛ እውነተኛ አማኞች በመሆን ለቤተ ክርስቲያን የሆንን ነን። ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ህግ ስር መሆን ከቶ አያስፈልገንም። ያም ማለት እግዚአብሔር ለእሥራኤል ከሰጠው ሕግ ስር ልንሆንና በኢየሩሳሌም ይሰዋ ከነበረው የእንስሳ ደም መስዋዕት ተካፋዮች መሆን አይገባንም ማለት ነው። በዚህ አውድ የዕብራውያን መልዕክት የሚከተሉትን ያመለክታል።

| | |
|---|---|
| ክርስቶስ ከመላዕክት የበለጠ | *ዕብ.1 እና 2* |
| ክርስቶስ ከሙሴ የበለጠ | *ዕብ.3* |
| ክርስቶስ ከኢያሱ የበለጠ | *ዕብ.4* |
| ክርስቶስ ከአሮን የበለጠ ነው | *ዕብ.5* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን የክህነት ሥርዓት የበለጠ ነው | *ዕብ.7* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ቃል ኪዳን የበለጠ ነው | *ዕብ.8* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መቅደስ የበለጠ ነው | *ዕብ.9* |
| ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች የበለጠ ነው | *ዕብ.10* |

እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ራዕይ /መገለጥ/ ከራዕዮች ሁሉ የበለጠና እጅግ የከበረ ነው። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለእሥራኤል ህዝብ የሰጣቸው የወደፊቱን የመዋጀት ስራ ጥላ ብቻ ነበር። የዚህ የመዋጀት ጥልቅ ሀቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር *(ቆላ.2:16-17 ! ዕብ.10:1)*። የብሉይ ኪዳን ውጭዓዊ ገጽታ እውነተኛውን አዳኛችንን ክርስቶስን ያሳያል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ህግ ማንንም ለማዳን የማይቻለው ነበር። ሰው በህግ በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ፣ በብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች በኩል መዳን ቢችል ኖሮ የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ከንቱ ይሆን ነበር። በደሙ የዳኑና በዳግም ልደት ወደ ቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ

የእግዚአብሔር ልጆች ወደ «ኋላ እንመለስም» የሚል አንድ መደምደሚያ መሥመር ሊኖራቸው ይገባል::

ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ መሠረት የሆነችና ዘላለማዊና ሰማያዊ መድረሻ ያላት ናት:: እርሷ «የበጉ ሙሽራ» (ራዕ. 21:9) በሰማይ ስጌታዋ ብቻ የሆነች ናት:: ይህም በምንም መንገድ ከእስምና ከእሥራኤል ጋር ትስስር ማድረግ ከቶ እንደማትችል ግልጽ ያደርገዋል:: ስለዚህም ነው ሰፊው አረንጓዴው መሥመር የሰውን ዘር ከሚያመለክቱት ሁለት መሥመሮች በላይ የሚሄደው::

## የኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ጋር ለዘለዓለም

ባለፉት 2000 ዓመታት ውስጥ አብዛኛውን ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች አልፈው አንቀላፍተዋል (ሞተዋል):: ዛሬም በሚሊዮን የሚቆጠሩ በዚህ ዓለም ዙሪያ ይኖራሉ:: ቢሆንም ከጴንጤቆስጤ /በዓለ-ሃምሳ/ ጊዜ ጀምሮ ካሉት ክርስቲያኖች ጋር ሲመዘኑ በጣም ጥቂቶች ናቸው:: እንደተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን ምስጢር ናት:: ስንት አባሎች እንዳሏት ማንም አያውቅም:: ጌታ ብቻ ነው ለእርሱ የሆኑትን የሚያውቅ (2ጢሞ.2:19) የእርሱ ናቸው ለዘላለምም የእርሱ ሆነው ይቀራሉ፣ ማንም ከእጁ ሊነጥቃቸው አይችልም (*ዮሐ.10:28*) *ብሎአልና*::


ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባልታሰበ ጊዜ በደሙ የተገዛችውን ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ሰማይ ይነጥቃታል:: ይህም የሚሆነው በአህዛብ ሙላት /ከዓለም በአንዱ ቦታ የመጨረሻው ሰው እምነቱን በክርስቶስ አድርጎ ራሱን ወደ ቤተ ክርስቲያን በጨመረ ጊዜ/ ነው (*ሮሜ.11:25፣26*):: ይህንን ጊዜ ማንም መገመት አይችልም የመጨረሻው ኃጢዓተኛ (/በመጨረሻ የሚድነው ማለት ነው) ሕይወቱን ወደ አዳኙ የሚመልስበትን ጊዜ ማንም ሰው አያውቅም:: ሆኖም ጌታ ቤተ ክርስቲያንን ሊነጥቅ ሊመጣ ባለው የመጨረሻ ሰዓት መኖራችንን እናውቃለን:: በሌላ አነጋገር «ስአኩለ ሌሊት ሰዓት» ከአምስት ደቂቃ ይልቅ አምስት ሴኮንድ በቀረበው ላይ ነን ቀኑንም ሆነ ሰዓቲቱን ከቶ አናውቅም (ማቴ. 24:36):: በደህንነት አረንጓዴ መሥመር ላይ ያለው የጥያቄ ምልክት ፍቺው ይህ ነው::

መነጠቅ መረዳት በማይቻል ፈጣን ጊዜ ውስጥ ይከናወናል:: «መወሰድ» ወይም «መነጠቅ» (1ኛ ተሰ. 4:17) የሚለው በአዲስ ኪዳን ወደ አሥራ አምስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል:: የዚህ ቃል ትርጉም «መነጠቅ» ወይም «በድንገት አንድን ነገር መንጠቅ» ማለት ነው:: ከዚህ ድርጊት በስተኋላ መስኮታዊ ኃይል መኖሩን እንድንገነዘብ ያደርገናል:: ቤተ ክርስቲያን «ጌታን በአየር ስመቀበልና ከእርሱ ጋር





ስመኖር ትነጠቃለች» (*1ኛ ተሰ.4:17*):: ጌታ ቤተ ክርስቲያንን ስመንጠቅ ወደ ምድር እየታየ አይመጣም:: ይልቅስ ቤተ ክርስቲያኑን በአየር ይገናኛታል::




ይህ በሚሆንበት ጊዜ በህይወት ያሉት «ያንቀላፉትን አይቀድሙም» (*1ተሰ.4:15*) «በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ፣ (1ተሰ.4:16) ከዚህ በኋላ ያልሞቱት በህይወት ያሉት አማኞች ይለወጣሉ (1ቆሮ.15:51)» በዚያን ጊዜ ብቻ ነው የዳኑት ጌታን በአየር የሚቀበሉትና ከእርሱ ጋር ስዘላለም አንድነት የሚኖራቸው:: የዳኑት ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ «እስከ አህዛብ ሙላት» ድረስ ያሉትን ያጠቃልላል:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ እግዚአብሔር ራሱ በወሰነው ጊዜ የሚሆን ነው::

ቤተ ክርስቲያን ወደ ክብሩ ከተነጠቀች በኋላ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ትቆማለች:: ይህንንም

*«መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሰራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል(2ቆሮ.5:10)*


ከሚለው ጥቅስ እንረዳለን::

ይህ «ፍርድ» የእግዚአብሔር ልጅ ደህንነት ወይም መፍረድን የሚጠይቅ አይደለም:: በዚህ የፍርድ ወንበር ጌታ ለታማኝ ደቀ መዝሙር ምን ሽልማት እንደሚሰጥ የሚወስንበት ነው:: የማንኛውም ክርስቲያን ሥራ በዚህ ፍርድ የተገለጠ ይሆናል:: ሥራው የሚጸና ወይም የሚቃጠል መሆኑ ይገለጻል (*1ቆሮ.3:14-15*):: የአማኙ የግል መዋጀት በምድር በህይወት በነበረ ጊዜ በሠራው ሥራ ላይ ያረፈ ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው የመዋጀት ሥራ ላይ ብቻ ያረፈ ነው:: ምክንያቱም *«ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»* (*1ቆሮ.3:11*) በማለት ስለተፃፈ ነው::

ከዚህ በኋላ እንደ ነጎድጓድ ያለ

*«የበጉ ሠርግ ስለደረሰ ሚስቱም ራሷን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን፣ ሐሴትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ» የሚል ድምጽ ይሰማል (ራዕ.19:7)::*

ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እንደ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሙሽሪት ሆነው ይገለጣሉ:: «የበጉ ሠርግ» በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ዘላለማዊውንና የማይሻረውን አንድነት ይደመድማል::




## 2. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

አዲስ ኪዳን ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ አባል የሆነበትን ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያንና በስም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተብለው በሚጠሩት መካከል ልዩነት ያደርጋል:: ይህ ልዩነት በአጥቢያ ያሉ አማኞች መሰብሰብን ይናገራል:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ መላ ምዕመኑ የሚሰበሰቡበት ሥፍራ ነው:: (*ሐሥ.2:42፤ 1ቆሮ.14:23*)

ሐዋሪያው ጳውሎስ ከመልዕክቶቹ ውስጥ ጥቂቶቹን በቀጥታ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ልኳል ለምሣሌ:- «በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን» (*1ቆሮ.1:2*) «እግዚአብሔር አብ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን» (1ኛ *ተሰ.1:1*) በማለት ጽፏል::

### አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - በዓለም ሁሉ

ከ2000 ዓመታት በፊት መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ዕለት 3000 ህዝቦች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑ ቀደም ብለን ተመልክተናል:: በኢየሩሳሌም የመጀመሪያዋ የአጥቢያ ማህበረ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ያኔ ነበር:: ደግሞም የጥንቷ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን በመባል ትታወቃለች::

በወንጌል መሠራጨት ምክንያት የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያናት በሌሎች ቦታዎች ተመሠረቱ ፤ በሐዎርያው ጳውሎስ ሚሲዮናዊ አገልግሎት ብዙ ሰዎች በተለይ ከአህዛብ በጌታ ኢየሱስ እንዲያምኑ ሆኑ:: ሰዎች በዳኑበት ሥፍራ ሁሉ አዲስ ቤተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ:: ዛሬም ቢሆን ይህ ሥራ እንዳለ ነው:: በዓለም አቀፍ ደረጃ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያናት አሉ:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት





ባልሰለጠኑት አገሮች ትናንሽ መንደሮችም ሆነ በሰለጠኑት አገሮች ትላልቅ ከተሞች ይገኛሉ:: ዳግም የተወለዱ አማኞች በትናንሽና በትላልቅ አጥቢያዎች «በጌታ እግር ሥር» በመሰባሰብ ይገኛሉ (*ሉቃ.10:39*)::

### የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የውጭ ምስክርነት

*«ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ» (ማቴ.18:20)::*

የአማኞች በአጥቢያ መሰባሰብ ግልጽ የሆነ ምስክርነት ነው:: አማኞች «ራስ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ» ለማደግ በአንድነት ይሰበሰባሉ (*ኤፌ.4:15*):: በዚህ መሰባሰብ በሚታየውና በማይታየው ዓለም ፊት ከተነሳው ጌታ ጋር አንድ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያሉ:: ማንኛውም ዳግም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ የክርስቶስ አካል አባል የመሆኑና የክርስቶስም ራስ የመሆኑ እውነት በአጥቢያ መሰባሰብ በኩል ግልጽ ሆኖ ይታያል:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የአማኝን የግል ዓላማ የሚያገለግሉ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ እውነተኛ ምስክርነት የሚሰጡ ናቸው:: በተጨማሪም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ይመሰክራሉ:: ይህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መለያ ነው:: ዋነኛው ዓላማ «ክርስቶስ» ነው::

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በኢየሩሳሌም በነበረችው የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ዳግም የተወለዱት አማኞች የመሰብሰባቸውን ዓላማ በትክክል የተረዱ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል::

*«በሐዋርያት ትምህርት፣ በህብረት እንጀራውንም በመቁረስና በፀሎት ይተጉ ነበር»* ተብሎ ስለ ተፃፈ *(ሐሥ.2:42)::*

1. በሐዋሪያት ትምህርት፣ 2. በህብረት 3. እንጀራውንም በመቁረስና /የጌታን ራት/ በመካፈል 4. በፀሎት በመትጋት በእነዚህ በአራቱ ሕያው ክርስቲያናዊ የህይወት ልምዶች ከጌታ ኢየሱስ ጋር ቀጥተኛ ሕብረት እንደነበራቸው ይገለጻል:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምስክርነትና የእያንዳንዱ አማኝ የግል በረከት በዚህ ህብረት ላይ የተመሠረተ ነው::

### አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን - የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ

*«...የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ»(1ቆሮ. 3:17)::*

በዚህ ጥቅስ ሐዋርያው ጳውሎስ ቆሮንጦሳውያንን በቤተ ክርስቲያንነታቸው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆናቸውን አስተምሯቸዋል:: በዚህ ጥቅስ መሠረት

እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በበለጠ በአጥቢያ የአማኞች ማህበር (ህብረት) መኖሩን ያሳያል::

የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሁልጊዜ ቅዱስ ቦታ ነው:: ይህን በጥልቅ ልንገነዘበው ይገባናል:: የሚያሳዝነው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ሕብረት በሰጠው ስርዓቶች ላይ ጥያቄ ማንሳቱ መጠየቁ ላይ ነው:: እነዚህ ልምምዶች በእግዚአብሔር ፊት የሚታዩ አይደሉም:: እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለማህበረ ምዕመኖቻቸው የራሳችውን ህግ እንዲያቋቁሙ አልተፈቀደላቸውም:: እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዓላማዎቻቸውን በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሠረት የሚያደርጉ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናቸው:: (*1ቆሮ.1:2፤ ገላ.1:2፤ ፊል.1:1፤ ቆላ.1:2)*

### 3. እያንዳንዱ አማኝ


*«ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖር የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም »* የሚለው ጥቅስ እንደሚያደርግ ያሳየናል *(1ቆሮ. 6:19)::*

መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ዳግም በተወለደው አማኝ ውስጥ ያድራል:: *«መንፈስ ቅዱስ የሰማይ ርስታችን መያዣ ነው ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምሥጋና ነው »* (*ኤፌ. 1:14*):: ስለዚህ ያለ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ መሆን አይቻልም:: ንስሐ የሚገባው ኃጢዓተኛ በፍጹም ልቡ በኃጢዓት ከተሞላ መንገዱ ሲመለስ፣ ኃጢዓቱን ሲናዘዝ፣ የእግዚአብሔርን ልጅ የግል ጌታውና አዳኙ አድርጎ ሲቀበል ዳግም ይወለዳል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ሂደት *«ዳግም መወለድ» «ዳግም ልደት»* ይለዋል (*ዮሐ.3:3*):: ይህ ዳግም ልደት በመንፈስ ቅዱስ የሚመጣ ነው:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተለወጠው ሰው ሕይወት በማደር ይኖራል (*ዮሐ.1:12*):: በክርስቶስ ሙሉ የሆነ አዲስ ሕይወት ይቀበላል:: ምክንያቱም ቃሉ *«ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፣ አሮጌው ነገር አልፎአል፣ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗልና (2ቆሮ.5:17)* ስለሚል:: ስለዚህ የሰው መለወጥ የመንፈስ ቅዱስ ስራ ነው::

ቀደም ካሉት ምዕራፎች በአንዱ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከስላሴ ሦስተኛ ወልድ ሁለተኛውና አብ ደግሞ የመጀመሪያው አካል መሆናቸውን ተመልክተናል:: መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ይመራናል::









ሁለተኛው አካል ክርስቶስ ደግሞ ወደ አብ ይመራናል:: ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የደህንነት ራዕይ /መገለጥ/ ነው:: ጌታ ኢየሱስ *«እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና»* በማለት የመንፈስ ቅዱስን ስራ ለደቀ መዛሙርቱ ገልጦላቸዋል (*ዮሐ.16:14*):: መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ልጅ በክብሩ ለሰው ነፍስ ያመለክታል:: ወደ እግዚአብሔር መምጣት የሚፈልግ ወደ ወልድ መምጣት አለበት:: ምክንያቱም ወልድ ብቻ ነው ሰውን በእውነት ወደ አብ መምራት የሚችለው ፤ስለዚህ ነው *«በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም»* በማለት ጌታ ኢየሱስ ያስተማረው /የሚያስተምረው/ (*ዮሐ.14:6*) ዳግም የተወለደ አማኝ የእግዚአብሔር ነው:: ስለሆነም እግዚአብሔርን አባቱ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታው አድርጎ ይቆጥራል ይህ የሚሆነው በመንፈስ ቅዱስ ነው:: ምክንያቱም *«በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር አንድ ስንኳ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል ስለማይችል» (1ቆሮ.12:3)*::

መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር በመስቀል አሠራር አንድነትን ያመጣል:: ስለዚህ ምክንያት ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ እኛ አማኞች ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ መሰቀላችንን፣ ከክርስቶስ ጋር መሞታችንና ከክርስቶስ ጋር መቀበራችንን የጻፈው:: *(ሮሜ.6:1-10)* የኤፌሶንም መልዕክት ከክርስቶስ ጋር መነሳታችንንና በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር መቀመጣችንን ያሳየናል *(ኤፌ.2:6)*:: ምክንያቱ ይህ ከክርስቶስ ጋር ያለው አንድነት በመንፈስ ቅዱስ ሥራ በኩል ብቻ የሚመጣ ነው:: «የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» *(ሮሜ.8:9)* የሚለውም ጥቅስ ይህንኑ ያፀናልናል::









የሰው ሕይወት መለወጥና ዳግም ልደት ፍጹም ውጤት በሚያመጣው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ያረፈ ነው:: ኃጢዓተኛው በመንፈስ ቅዱስ ሲማረክ የኃጢዓአቱን ይቅርታ በንስሐና በኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ያገኛል:: በዚያኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ወደ ክርስቶስ አካል ይጠመቃል *(1ቆሮ.12:12-13)*:: መንፈስ ቅዱስ አዲሱን አማኝ ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆነበትን የኢየሱስ ክርስቶስን የመዋጀት ሥራ ያረጋግጥለታል:: ኃጢአቱ መወገዱንና በአዳኙ መከራ፣ ሞት ሙሉ ይቅርታ ማግኘቱን ያሳያል:: በዳግም ልደት አማኙ የኢየሱስ ክርስቶስ ገንዘብ ይሆንና ዳግም ከተወለዱት ሌሎች አማኞች ጋር የእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል:: ከአዳኙና ከዋጀው ጌታ በማይለይ ሁኔታ የክርስቶስ አካል አባል ይሆናል *(1ቆሮ.12:27)*:: ስለሆነም ዳግም የተወለደው አማኝ ወደፊት የሚኖረው ራሱ ሳይሆን ለእርሱ ሲል ለሞተውና ለተነሳው ነው *(2ቆሮ.5:15)*:: ምክንያቱም የአማኙ ሰውነት (አካል) የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነ ነው:: ከዚህ የተነሳ አማኙ ከአምላኩ ጋር ባለው አካሄድ የተለየ ኃላፊነት ይጠበቅበታል:: አማኙ ሰውነቱን እንዴት መያዝና ከእርሱ ምን እንደሚጠበቅ አዲስ አይሆንበትም:: ሐዋርያው ጳውሎስ ቸልተኞቹን ቆሮንቶሳውያንን በዚህ ጉዳይ *«በዋጋ ተገዝታችኋልና፣ ስለዚህ በሥጋችሁ በመንፈሳችሁ እግዚአብሔርን አክብሩት»* በማለት ገስጿቸዋል *(1ቆሮ.6:20)*:: ዳግም የተወለደ አማኝ ያለው ምድራዊ ተስፋ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊም ተስፋ ነው *(ቆላ.1:27)*:: አዳኙንና ጌታውን ኢየሱስን የሚጠብቅ ዜግነቱ ሰማያዊ የሆነ ነው *(ፊል.3:20)*:: ይህም በዚህ ምድር እንግዳና መጻተኛ እንደመሆን ያለ ህይወት ነው:: *(1ጴጥ.2:11)* ዳግም የተወለደው አማኝ ስለ አምላኩ የማያቋርጥ ናፍቆት አለው፤ በጌታ ቶሎ መምጣትና ከዚህ ዓለም ተለይቶ ከክርስቶስ ጋር እንደሚሆን በማሰብ ይደሰታል *(ፊልጵ.1:23)*:: ዳግም የተወለዱት ለጠፉትና ላልዳኑት ሸክም አላቸው:: *«ሂዱና አህዛብን ሁሉ ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው» (ማቴ. 28:19)* የሚለው የጌታ ታላቁ ተልዕኮ በልቡ ውስጥ የሚነድድ ይሆናል:: ከጳውሎስ ጋር *«በወንጌል አላፍርም፣ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ነው»* በማለት ይመሰክራል *(ሮሜ.1:16)*:: ስለሆነም አማኙ በተገኘው መንገድ ሁሉ መልካሙን ዜና ለጠፉት ሰዎች ለማካፈል ይጥራል:: ኒኮላውስ ሉድቪግ ቪንዜን ሲንስ ርዶርፍ የተባሉ በጊዜያቸው ብዙ ህዝብ ወደ ጌታ የመሩ ሰው እንዲህ ብለው የነፍሳትን ማዳን ይገልጹታል::

«እስከ እለተ ሞቴ ድስ ምኞቴ ነፍሳትን ለበጉ ማትረፍ ነው::»

በ1ኛ.ቆሮ.10:32-33 ላይ ባደረግነው በሦስት የሰው ዘር ጥናት ላይ ተመስርተን በዚህ ነጥብ የተገኙትን የሚከተሉትን ውጤቶች ተመልለን እንቃኛለን::

1. **የጥንቱ ታሪክ፡-** ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ባቢሎን ግንብ ግንባታ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል:: እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ከነበሩት ህዝቦች ጋር በምድር ሁሉ ላይ እስከሚበትናቸው ጊዜ ድረስ ተናገረ:: (*ከዘፍ. ምዕራፍ 1 እስከ 11*)
2. **የእስራኤል ታሪክ፡-** ከአብርሃም መመረጥ ጀመረና መሲሁን በመቃወም አበቃ:: (ከዘፍ.12 - ሐሥ.12) እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የመዳንን ታሪክ በቀጥታ አደረገ:: ነገር ግን በመቃወማቸው የደህንነትን ነገር ወደ አሕዛብ አሳለፈ::
3. **የቤተክርስቲያን ዘመን፡-** በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጀመረና (ሐሥ.2) ዳግም በተወለዱት መነጠቅ ያከትማል:: እግዚአብሔር በወንጌል በኩል ራሱን ለሰው ዘር ሁሉ ሰጠ:: ቤተ ክርስቲያንም ታየች:: እርሷም አይሁድንና አህዛብን ያቀፈች ናት:: (ሐሥ.13 እስከ ራዕይ.3)

እንደገና አንድ ጊዜ ጥልቅ የሆነውን የደህንነትን ዘመን ታሪክ ለውጥ የተደረገበትን ምክንያት ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው:: እንደ *ማቴ. 16:13-19* አዲሱን የፀጋ ዘመን፣ *መዋጀትን፣* መንፈስ ቅዱስንና ለአይሁድ *(ሐሥ.2)* ለሰማሪያውያንና *(ሐሥ.8)* ለአህዛብ *(ሐሥ.10)* ቤተ ክርስቲያንን እንዲከፍት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ጴጥሮስ *«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ቁልፍ»* ሰጠው:: የሐዋርያት ሥራ ባጭሩ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ አዲሱ ኪዳን የፀጋ ዘመን እንዴት ሽግግር እንደተደረገ ይናገራል::ይህ ሽግግር እስከ አሁን ድረስ የቀጠለ ነው:: የሚቀጥለው









## ሁለቱ ክቦች ፍቺ
## እሥራኤል
## በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ላይ

በእግዚአብሔር የደህንነት ካርታ ላይ ግልጽ የሆኑ ሁለት ጥቁር ክቦች ታገኛላችሁ:: አንዱ ከቀራንዮ መስቀል አጠገብ የሆነ ነው:: ሌላው ደግሞ ከፍ እያለ ወደ ላይ የሚመጣው የእሥራኤልን ህዝብ የሚወክለውን ቀዩን መሥመር ወደታች በመውረድ በሚያቋርጠው የዓለም ህዝቦችን ከሚያመለክተው ሰማያዊ መሥመር ወደቀኝ ጥቂት እልፍ ብሎ ነው::

ሁለቱም ክቦች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: በጣም ልዩ የሆነን ሰዓት (ጊዜን) ያመለክታሉ:: «የእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት» ብለን እንሰይመዋለን:: ይህንንም በመመልከት ራሳችን በየትኛው የእግዚአብሔር የማዳን ዘመን ውስጥ እንዳለን እንመለከታለን:: በሌላ አነጋገር በዓለም የደህንነት ታሪክ እንዴት ወደኋላ (መጨረሻ) ላይ እንዳለ ያሳየናል:: ስለዚህ ይህንን ሰዓት እንዴት በጥንቃቄ ማንበብ እንዳለብን መረዳቱ አስፈላጊ ነገር ነው:: በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ፊት በደህንነት ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ቀናት የያዘ ነው:: በዚህ ሰዓት ያለው ቀስት ህዝቦችን (ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ የሆኑትን እሥራኤልን) የያዘ ነው::




| የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት ከ1900 ዓመታት በፊት | የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት በዚህ ክፍለ ዘመን |
|---|---|

በ1ኛ.ቆሮ.10:32-33 ላይ ባደረግነው በሦስት የሰው ዘር ጥናት ላይ ተመስርተን በዚህ ነጥብ የተገኙትን የሚከተሉትን ውጤቶች ተመልሰን እንቃኛለን::

1. **የጥንቱ ታሪክ:-** ከዓለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ባቢሎን ግንብ ግንባታ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል:: እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ከነበሩት ህዝቦች ጋር በምድር ሁሉ ላይ እስከሚበትናቸው ጊዜ ድረስ ተናገረ:: *(ከዘፍ. ምዕራፍ 1 እስከ 11)*
2. **የእስራኤል ታሪክ:-** ከአብርሃም መመረጥ ጀመረና መሲሁን በመቃወም አበቃ:: (ከዘፍ.12 – ሐሥ.12) እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የመዳንን ታሪክ በቀጥታ አደረገ:: ነገር ግን በመቃወማቸው የደህንነትን ነገር ወደ አሕዛብ አሳለፈ::
3. **የቤተክርስቲያን ዘመን:-** በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ጀመረና (ሐሥ.2) ዳግም በተወለዱት መነጠቅ ያከትማል:: እግዚአብሔር በወንጌል በኩል ራሱን ለሰው ዘር ሁሉ ሰጠ:: ቤተ ክርስቲያንም ታየች:: እርሷም አይሁድንና አህዛብን ያቀፈች ናት:: (ሐሥ.13 እስከ ራዕይ.3)

እንደገና አንድ ጊዜ ጥልቅ የሆነውን የደህንነትን ዘመን ታሪክ ለውጥ የተደረገበትን ምክንያት ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው:: እንደ *ማቴ. 16:13-19* አዲሱን የፀጋ ዘመን፣ መዋጀትን፣ መንፈስ ቅዱስንና ለአይሁድ *(ሐሥ.2)* ለሰማሪያውያንና *(ሐሥ.8)* ለአህዛብ *(ሐሥ.10)* ቤተ ክርስቲያንን እንዲከፍት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ጴጥሮስ *«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ቁልፍ»* ሰጠው:: የሐዋርያት ሥራ ባጭሩ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ አዲሱ ኪዳን የፀጋ ዘመን እንዴት ሽግግር እንደተደረገ ይናገራል::ይህ ሽግግር እስከ አሁን ድረስ የቀጠለ ነው:: የሚቀጥለው









## ሁለቱ ክቦች ፍቺ
## እሥራኤል
## በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ላይ

በእግዚአብሔር የደህንነት ካርታ ላይ ግልጽ የሆኑ ሁለት ጥቁር ክቦች ታገኛላችሁ:: አንዱ ከቀራንዮ መስቀል አጠገብ የሆነ ነው:: ሌላው ደግሞ ከፍ እያለ ወደ ላይ የሚመጣው የእሥራኤልን ህዝብ የሚወክለውን ቀዩን መሥመር ወደታች በመውረድ በሚያቋርጠው የዓለም ህዝቦችን ከሚያመለክተው ሰማያዊ መሥመር ወደቀኝ ጥቂት እልፍ ብሎ ነው::

ሁለቱም ክቦች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው:: በጣም ልዩ የሆነን ሰዓት (ጊዜን) ያመለክታሉ:: «የእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት» ብለን እንሰይመዋለን:: ይህንንም በመመልከት ራሳችን በየትኛው የእግዚአብሔር የማዳን ዘመን ውስጥ እንዳለን እንመለከታለን:: በሌላ አነጋገር በዓለም የደህንነት ታሪክ እንዴት ወደኋላ (መጨረሻ) ላይ እንዳለ ያሳየናል:: ስለዚህ ይህንን ሰዓት እንዴት በጥንቃቄ ማንበብ እንዳለብን መረዳቱ አስፈላጊ ነገር ነው:: በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት ፊት በደህንነት ታሪክ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ቀናት የያዘ ነው:: በዚህ ሰዓት ያለው ቀስት ህዝቦችን (ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብ የሆኑትን እሥራኤልን) የያዘ ነው::



| የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት ከ1900 ዓመታት በፊት | የእግዚአብሔር የአለም ሰዓት በዚህ ክፍለ ዘመን |
|---|---|

በየትኛው የደህንነት ታሪክ ዘመን ውስጥ እንኖራለን ለሚለው ጥያቄ መልሱን ለማግኘት ከፈለግን ሁልጊዜ ዓይናችንን እሥራኤል ላይ መጣል አለብን:: ስለዚህ አሁን ከእሥራኤል ጋር ከተያያዙት ጥቂት ታሪኮች እንመለከታለን:: እነርሱም ለመዳን ታሪክ ቀጥተኛና አስፈላጊ ናቸው:: እንደዚሁም ደግሞ ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ምን ያህሉ ትንቢቶች እንደተፈጸሙ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ እየተፈጸሙ ያሉትን ያሳዩናል:: ምን ያህል በፀጋ የመጨረሻ ቀናትና የዓለም ፍጻሜ ላይ እንዳለን ለመረዳት አስቸጋሪ አለመሆኑን እንገነዘባለን::

**1. የእሥራኤል ህዝብ መቡተን**

**በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ቀስት ወደ ታች መውረድ**

**እ.አ.አ በ33 ዓ.ም. ስቅለት**

*«ጲላጦስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው ሁሉም ሰቀለው አሉ:: ገዢውም ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድነው? ሲላቸው:: እነርሱ ግን ይሰቀል እያሉ ጩኸታቸውን አበዙ» (ማቴ.27:22-23)::*

*«እነርሱ ግን አስወግደው! አስወግደው! ስቀለው እያሉ ጮኹ:: ጲላጦስም ንጉሣችሁን ልሰቀለውን? አላቸው:: የካህናት አለቆችም «ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም» ብለው መለሱለት:: (ዮሐ.19:15)*

ከላይ እንደተጠቀሰው ጽሕፍት ፈሪሳውያን (መንፈሳዊ ባለስልጣናትና መሪዎች) በመሲሁ በጌታ ኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ ፈረዱበት:: ቀደም ሲል ጌታ በምሳሌው «ይህ በላያችን ሲነግስ አንወድም» ብሎ የተናገረው አሁን እውነት ሆነ:: (*ሉቃ.19:14*) በእግዚአብሔር ጎን ከመቆም ይልቅ ህዝቡን ወክለው የነበሩት ሊቀ ካህናት ከሮም ንጉሥ ጎን ቆሙ:: በይሁዳ የነበረው የሮም መንግስት ተወካይ ጴንጤናዊው ጲላጦስ ጌታን ለሞት የሚያበቃው በደል እንደሌለበት ደጋግሞ ቢመሰክርም ራሱን ለጌታ ተቃዋሚዎች በማንበርከክ በጌታ ላይ የሞት ፍርድ ፈረደበት (*ሉቃ.23:22*)::

ከጥቂት ሰዓታት በኋላ በጣም እስከፊ የሆነ ሁኔታ ተከናወነ:: እሥራኤል «በአመጸኞች እጅ» ንጉሣቸውን ሰቅለው ገደሉት:: (*ሐሥ.2:23*) ሰማያዊውን ንጉሡን በምድራዊ ገዢ ተኩት::

ካለፉት ምዕራፎች በአንዱ ምዕራፍ የሮም ገዢ ጨካኝ ጣዖት አምላኪ እንደነበር ተመልክተናል:: የሮም ከፍተኛ ጣዖት የነበረው የጁፒተር ልጅ ነው ተብሎ ይገመት ነበር:: ከጁፒተር በስተኋላ ያለው ሰይጣን መሆኑ የማያጠራጥር





ነው:: ስለሆነም እሥራኤል አስከፊ ምርጫ ነበር ያደረገችው:: የክብር ጌታዋን በመቃወም የዚህን ዓለም ገዢ መረጠች (*1ቆሮ.2:8*) ፣ ከመቅፅበት የዚህን ዓለም ገዢ መረጡ (*ዮሐ.12:31*)፡ በዚያን ጊዜያት የዚህ ዓለም ገዢ ዋነኛ አገልጋይና የበላይ መሪ የነበረውን የሮምን ንጉሥ እሥራኤል መረጠችው:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይህ መሪ ምን ያህል አስከፊና አጥፊ መሆኑ የተገለጸ ነበረ:: በኋላም የሮም መንግስት መጥቶ የእሥራኤልን ምድርና ህዝብ አጠፋ::

የጌታ ኢየሱስ የስቅለቱ ዓመት መቼ እንደነበር በግምት የተደረገ ነው (*በሉቃ.3:1*)፡ ዮሐንስ መጥምቁ እሥራኤልን ወደ ንስሐ እየጠራ በዮርዳኖስ ወንዝ የታየው በንጉሥ ጢባርዮስ በአሥራ አምስተኛው ዓመት ነበር:: ከ.ል.በኃላ ንጉሥ ጢባርዮስ የአውግስጦስ ወራሽ የሆነው በ14 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ሲሆን የገዛው ከ.ል.በኋላ ከ27 እስከ 14 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ድረስ ነበር:: መጥምቁ ዮሐንስ የታየበት የጢባርዮስ አስራ አምስተኛው ዓመት በግምት ከ 28-29 ዓ.ም. ያለው ጊዜ ሲሆን ይችላል:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጌታ ኢየሱስ መሲህ ሆኖ በመገለጥ በእሥራኤል ህዝብ መካከል ለሦስት ዓመት ተኩል /ለ3½ ዓመታት/ ሠራ:: ዘመኑን ለመገመት የሚቻለው ጌታ ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሦስት ጊዜ ከወጣበት እውነት በመነሳት ነው (*ዮሐ.2:13! ዮሐ.6:4! ዮሐ.12:1*)፡ ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ የተሰቀለው በ33 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ገደማ ሊሆን ይችላል:: ከኢየሩሳሌም መፍረስ (መደምሰስ) ከአርባ ዓመት በፊት ሮማውያን ከአይሁድ የሞት ፍርድ የመፍረድን መብት ወስደውባቸው ነበር:: ቤተ መቅደሱ የተደመሰሰው በ 70 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ነበር:: የሞት ፍርድ መፍረድ ካለመቻላቸው የተነሳ ነበር ሊቀ ካህናቱና የህዝቡ ሽማግሌዎች ጌታ ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ ያቀረቡት የሞት ፍርድ መፍረድ የሚችለው የሮማውያን መንግሥት ተወካይ ብቻ ነበር::

የጌታ ኢየሱስን ስቅላት ጊዜ ለመቁጠር ሃሳባችንን የሚስበው ከብዙ ዓመታት በፊት የተካሄደው ነገር ነበር:: በቤተልሔም ህፃናትን ያስገደለው ሄሮድስ በኢያሪኮ የሞተው በመጋቢት (April) 2 እ.ኤ.አ. (ከ.ክ.በኋላ) ነው:: የተቀበረው ከቤተልሔም ደቡባዊ ምሥራቅ አስራ ሦስት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ከሚገኘው የሄሮድሳውያን ምሽግ ውስጥ ነበር:: እንደ *ማቴ.2:16* መሠረት በሄሮድስ የተገደሉት ህፃናት ዕድሜአቸው ሁለት ዓመትና ከሁለት ዓመት በታች ነበር:: ይህ ጊዜ የዓለም አዳኝ የሆነው ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን 6 ከ.ል.በኋላ ያመጣናል:: የቤተልሔሙ ኮከብ መታየት ስለ ዘመኑ አቆጣጠር ሌላ የአቆጣጠር ምክንያት ሊሰጠን ይችላል:: የሚቀርቡልን ማስረጃዎች ነገሮች በጣም ግልጽ ላይሆኑ ይችላሉ:: ቢሆንም የጌታ ስቅላት የሆነው በ 33 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ነበር::

## በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት መቆጣጠሪያ ቀስት እንደገና ወደ ታች መውረድ 70 ዓ.ም ከ.ክ.ል.በኋላ የቤተ መቅደስ መደምሰስ

«ኢየሱስ ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ:: ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ:: እርሱ ግን መልሶ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው» (*ማቴ. 24:1-2*): ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በኢየሩሳሌም ስለ ነበረው ቤተ መቅደስ ተንብዮ ነበር:: የዚህ አስደናቂ ግንብ ድንጋይ በድንጋይ ላይ መፍረስ የማይቀር ነበር:: ይህ ትንቢት በግልጽ የሚፈጸምበት ጊዜ እየቀረበ እየመጣ ነበር::

### የእየሩሣሌም መደምሰስ

በ66 ዓ.ም. በሜዲትራኒያን ባህር አጠገብ ባለችው በቂሳሪያ የአይሁድ አመጽ በሮማውያን ላይ ተጀመረ:: በ73 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ለሰባት ዓመታት የቀጠለው አመጽ በሙት ባህር አጠገብ ባለው በረሃ በማሰዳ መውደቅ ወደ ፍጻሜ ደረሰ:: በ67 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ሮማውያን በገሊላ አይሁድን ድል አድርገዋቸው ነበር:: በእነዚህ ጊዜያት አራት ተፎካካሪ ገዢዎች ተነስተው ነበር:: በ68 በንጉሥ ኔሮ መገደል ምክንያት በአይሁድ ላይ የነበረው ጦርነት ጋብ ብሎ ነበር:: እነዚህም ገዢዎች ኦቶ፣ ጋልባ፣ ቪቲሊዮስና ቪስፓስያን ነበሩ:: በ69 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ቪስፓሲያን ዙፋኑን ያዘና የሮም ንጉሥ ሆነ:: በ70 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) ቪስፓስያን ቲቶስ የተባለውን ልጁን ኢየሩሳሌምን እንዲያሸንፍ የጦር ጀኔራል አድርጎ ላከው:: በኋላም ቲቶስ ራሱ በ79 ዓ.ም. የሮም ገዢ ሆነ:: ቲቶስ ከሠራዊቱ ጋር ኢየሩሳሌምን በከበባት ወቅት በውስጧ ከ600,000 ሰዎች በላይ ነበሩ:: የመጡት በመጋቢትና በሚያዝያ ወራት የፋሲካን በዓል ለማክበር ነበር:: በኢየሩሳሌም ይኖሩ ከነበሩትና ለመጡት እንግዶች በቂ ስፍራ ነበር::

ወደ ከተማው ከሚመጣው ከሮም ሰራዊት ተጽዕኖ የተነሳ የከተማዋ በሮች ተዘግተው ነበር:: ከተማዋ በደንብ ተመሽጋ የተሰራች ስለነበር በውስጧ የነበሩት ህዝቦች በኢየሩሳሌም ውስጥ ደህንነት እንደሚኖራቸው ተስምቷቸው ነበር:: እግዚአብሔር ቅድስቲቷን ከተማና ቤተ መቅደሱን ለጥፋት የማይሰጥ ነው ብለው አስበው ነበር:: ቢሆንም ያለፈ ነገር ነበር እሥራኤል የጥልቁን መንግስት መርጣ ነበር:: የመረጠችውም እነሆ መጣ::

ኢየሩሳሌም ለአምስት ወራት ያህል በሮማውያን ተከባ ነበር:: አስቃቂ ውጊያዎች ተደረገ፤ እሥራኤል ራሷን መከላከል ነበረባት:: በከተማዋ ውስጥ የነበሩት ህዝቦች ወጥመድ ውስጥ ወድቀው ነበር:: ከሌላው የዓለም ህዝብ ተለይተው መቀመጣቸው ከፉ ሆነባቸው:: ታላቅም ረሃብ ሆነ፣ ህዝቡም በድንገት የሚበላውን አጣ::





በዚህም ላይ አይሁድ እርስ በእርሳቸው ጠላታሞች ሆኑ:: የሌላውን ጎተራ መዝረፍ ስለተጀመረ ረሃቡን አባባሰው:: የከተማዋም ነዋሪዎች በዚህ ሁኔታ በጣም ተስፋ ቆረጡ:: ከረሃቡ ስቃይ የተነሳ እናቶች አዲስ የተወለዱትን የህፃኖቻቸውን ሥጋ በሉ (*ዘዳ.28:53*):: ፈላቪዮስ ጆሴፉስ የተባለው የአይሁድ ታሪክ ፀሐፊ «የአይሁድ ጦርነቶች» በተባለው መጽሐፉ ውስጥ አዲስ የተወለደውን ልጇን ስለ ቀቀለችው ሴት ስለ ማሪያ ጽፏል:: ያለ ምህረት ሕዝቡን በሽታ ጨረሰው:: በከተማዋ ዙሪያ ያሉት ሽለቆዎች በረሃብ በሚሰቃዩት ሰዎች ሬሳ የተሞሉ ሆኑ:: ሮማውያኑ ለጦርነቶችና ለመስቀሉች (ለስቅላት) መጠቀሚያ በኢየሩሳሌም ዙሪያ በሃያ ኪሎ ሜትር ሥፋት ላይ ያሉትን ዛፎች በሙሉ ቆረጡ:: በየቀኑ ሮማውያን ከ 500 በላይ አይሁዶችን ይሰቅሉ ነበር:: በከተማዋ ውስጥ ወደር በሌለው ሁኔታ ተስፋ መቁረጥ አደገ::

«ከቄሳር በቀር ንጉሥ የለንም» በማለት የእሥራኤል መሪዎች የመረጡት:: ንጉሥ ከአርባ ዓመት በኋላ በጠላትነት ወደ እነርሱ መጣ:: ወታደሮቹ በኢየሩሳሌም በሮች ፊት ለፊት ቆመ:: ከዚህ ጊዜ በኋላ በከተማይቱ ውስጥ ለነበሩት መዳን የሚቻል አልነበረም:: ኢየሩሣሌም ፈጽማ ተወረረች:: የተረፉት ያለ ርህራሄ ታረዱና ከተማይቱም ተደመሰሰች::

### የቤተ መቅደሱ መደምሰስ /ፍጻሜ/

በቅድስቲቱ ከተማ መደምሰስ ምክንያት የጌታችን ትንቢት ተፈጸመ:: ነሐሴ 10 ቀን 70 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) አንድ የሮማውያን ወታደር የሚነድ ችቦ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ጣለ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ መላ ቤተ መቅደሱ በእሳት ተያያዘ:: የእሳቱ ኃይል በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን ወርቅ አቀለጠው:: የቀለጠው ወርቅ ከግድግዳው ወደ ወለሉ ወረደ: ከዚያም ከድንጋዮቹ ስንጣቂዎች ውስጥ እየገባ ረጋ:: ወርቁን ለማግኘት የሮም ወታደሮች የከባድ ነገር መፈንቀያ ብረቶቻቸውን አንስተው ድንጋዮቹን ለባበሩአቸው:: መላ ከተማዋ ከነህንፃዋ በእሳት ጋየች:: ጦርነቱ እስከ መስከረም ድረስ ቀጠለ:: ዛሬም ቢሆን በአስደናቂዋ ከተማ በኢየሩሣሌም ብዙ ፍርስራሾች ይታያሉ:: አዳዲስ የከርሰ ምድር ቅሪቶች በየጊዜው ይገኛሉ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእሥራኤል ህዝብ ስለ ቤተ መቅደሱ መደምሰስ (በቲሻቤ የሀዘን ቀን) በ9ኛው ወር በየዓመቱ ያለቅሳሉ:: የቤተ መቅደሱን ተራራ ከሚከበው 488 ሜትር ርዝመት ካለው ግንብ በስተምዕራብ በኩል 80 ሜትሩ «የልቅሶ ግንብ» የልቅሶ አደባባይ የተባለው ስለዚህ ነው:: ቤተ መቅደሱ የተደመሰሰው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር:: ጌታ እንደተነበየው *«ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል» (ሉቃ.21:5-6):: «የአህዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሣሌም በአህዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24)::*

በ70 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) የቅድስቲቱ ከተማና የቤተ መቅደሱ መደምሰስ ለእሥራኤል ህዝብ የሚያሰቅቅ መናወጥ የሆነበትና እስከ አሁን ድረስ ያልተፈወሱበት ጉዳይ ነው:: ከ1900 ዓመታት በላይ አንድ አይሁዳዊ ለታመመ ቤተሰቡ የሚያስተላልፈው ቃል «እኛ ለጽዮንና ለኢየሩሳሌም እንዳዘንን ሃዘናችሁ ሃዘናችን ነው» የሚል ነው::

ኢየሩሳሌም በተከበበችበት በአምስት ወራት ውስጥ 600,000 አይሁዳውያን ሕይወታቸውን አጥተዋል:: «የአይሁድ ጦርነት» ተብሎ ከሚጠራው ከ66 ዓ.ም. እስከ 73 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ከሆኑት ይህ አንዱ ነበር:: በእነዚህ ዓመታት ሮማውያን 1.1 ሚሊዮን አይሁዶችን ገድለዋል:: በወቅቱ በነበረው «ምድራዊ ንጉሥ» በአስፈሪ ሥራው የአይሁድን ህዝብ አዋርዶ ጥሎአቸዋል:: እውነተኛውን ንጉስ በመቃወማቸውና ምድራዊ ንጉስ በመምረጣቸው በእሥራኤል ህዝብ ላይ ጥፋትና ሞት ወደቀ::

**በእግዚአብሔር የዓለም ሰዓት መቁጠሪያ ጠቋሚዋ**
**ቀስት እንደገና ወደ ታች መውረድ**
**135 ዓ.ም. ከ.ክ.ል.በኋላ የባረኮቼባ አመጽ**

*«በሰይፍ ስለትም ይወድቃሉ፣ ወደ አህዛብም ሁሉ ይማረካሉ፣ የአህዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሣሌም በአህዛብ የተረገጠች ትሆናለች» (ሉቃ.21:24)* ተብሎ እንደተፃፈው::

ከ132 እስከ 135 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) ባለው ጊዜ ውስጥ በአይሁድና በሮማውያን መካከል ውጊያዎች ተቀሰቀሱ:: አንድ ሐሰተኛ ነቢይ በእሥራኤል ተነሳ ስሙም ባርኮችባ ይባል ነበር:: የስሙ ትርጓሜ «የከዋክብት ልጅ» ማለት ነው:: ይህም ሰው «ከያዕቆብ የሚወጣው ኮከብ» አድርጎ ራሱን ይቆጥር ነበር (*ዘኁ.24:17*): ከሮማውያን ጋር በሚደረገው ጦርነት አይሁድን በድል የሚመራ «መሲህ» ብሎ ራቢ አኪባ የሰየመው ሰው ነበር:: ለሶስት ዓመታት ያልተቋረጠ አሰቃቂ ጦርነት ሆነ:: የሮማ ንጉሥ ሀድሪያን ከጀግኖቹ የሮም ወታደሮች ጋር አመጸኞቹን ደመሰሱአቸው:: ሮማውያን ቀላል ያልሆነ ክስረት ከሰሩ:: በአይሁዳውያን ላይ በነበራቸው ቁጣ በቀል ተበቀሉ ኢየሩሳሌምንም ደመሰሱ::

የባርኮቼባ አመጽ 500,000 አይሁዳውያን ሕይወታችን እንዲያጡ አደረገ:: ሮማውያን አይሁድን ለመደምሰስና ከምድር ገጽ ለማጥፋት ፈልገው ነበር:: ከቤተ ልሔም ደቡባዊ ምዕራብ በምትገኘው በቤዛር ከተማ 300 የአይሁድ ሕጻናት በድንጋይ ላይ ተፈጥፍጠው ተገደሉ (*መዝ.(137):8-9*): ሮማውያን የፈጸሙት ግፍ ሊገመት የማይቻል ነበር:: «ወዮ ለተሸናፊዎች» የሚለውን የሮማውያንን አባባል እናስባለን::





## የኢየሩሳሌም ፍጻሜ

ልክ እንደ 70ኛው ዓ.ም. ኢየሩሳሌም እንደገና የማታመልጥ ሆነች:: በተቃራኒው ጥፋቷ በበለጠ የሚገለጽ ሆነ:: ኢየሩሳሌም እንደ እርሻ ታረሰች:: ጌታ ስለ እየሩሳሌም መደምሰስ የተናገረው በተደጋጋሚ ተፈጸመ:: ኢየሩሳሌም እንደገና ኢየሩሳሌም ተብላ እስከማትጠራ ድረስ በአህዛብ የተረገጠች ሆነች:: ንጉሥ ሀድሪያን ከተማዋን በአራት ወረዳዎች ከፋፈላት:: ከተማዋን የሮም ወታደራዊ ቦታ አደረጋትና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከተማዋን «አሊያ ካፒቶሊና» ብሎ ለየማት:: ኢየሩሳሌም የሚለው የቅድስቲቱ ከተማ ስም ለጊዜው ተደመሰሰ:: ለአራት መከፈሏ እስከ አሁን ድረስ የሚታይ ነው::

በጥንቷ ኢየሩሳሌም በየስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የአይሁድ የክርስቲያን፣ የአርመኒያውያንና፣ የእስላም አካባቢዎች ይገኛሉ:: የመጨረሻው የአይሁድ ህዝብ መበተን የሆነው በ135 ዓ.ም. (ከ.ክ.ል. በኋላ) ኢየሩሳሌም በተደመሰሰች ጊዜ ነው:: የእስራኤል ልጆች «እንደ እስረኛ ወደ ዓለም የተወሰዱት» ጌታ ኢየሱስ አስቀድሞ በተናገረው ትንቢት መሠረት ነው (*ሉቃ. 21:24*): ከዓለም አልተወገዱም፣ ወደ ጎንም አልተጣሉም ነገር ግን መበተናቸው በዓለም ውስጥ ሆነ:: እስራኤል የሚለው ስም በጭራሽ ዳግመኛ የማይታሰብ እንዲሆን ተደረገ (*መዝ. 83:4*): ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሮማውያን የቅድስቲቱን ምድር ፍልስጥያ (ከዚህም ፓለስታይን የሚለው ስም ተገኘ) ብለው ጠሯት::

## እስራኤል ለብዙ ክፍለ ዘመናት በውጪ ነገስታት ሥር

ከብሉይ ኪዳን ዘመን ለአምላካቸውና ለንጉሣቸው ባለመገዛታቸው ለብዙ ምዕተ ዓመታት ለባዕድ ነገስታትና፣ ባለሥልጣናት መገዛታቸውን የሚከተለው መግለጫ ያሳያል ለብዙ አመታት ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እግዚአብሔርን ንጉሣቸው ባለማድረጋቸው በሌሎች ተገዙ:: ቀጥሎ የተዘረዘሩተ መንግሥታት በተለያዩ ጊዜያት እስራኤልን ገዝተዋል::

### 1. የባቢሎን ነገሥታት

| | | |
|---|---|---|
| 1. ናቡከደነፆር | 606/605- 562 | ከ.ል.በ |
| 2. ዩር ማርደክ | 561- 560 | » |
| 3. ኒርግሊሶር | 559- 556 | » |
| 4. ላባሲ ማሮዶክ /ለ3 ወራት/ | 556 | » |
| 5. ናቦኒ ደሱ | 555- 538? | » |
| 6. ብልጣሶር | 538- 536? | » |

- ክ.ል.በ = ከክርስቶስ ልደት በፊት ማለት ነው።
- ክ.ል.በኋ = ከክርስቶስ ልደት በኋላ ማለት ነው።
- በጥያቄ ምልክት (?) የጠቀሱት ዘመናት በአንዳንድ የታሪክ መጽሐፍት የተሰያዩ ስለሆኑ ነው።

## 2. የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት

| | | |
|---|---|---|
| 1. ኮሬሽ /ቂሮስ/ | 538/36- 530 | ክ.ል.በ |
| 2. ካምቢሰስ | 529- 522 | » |
| 3. ባርዲያ (ለ6ወራት/ናቡከደነፆር3ኛ /ለ3 ወራት/ | 522 | » |
| 4. 4ኛው ናቡከደነፆር /3ወራት/ | 521 | » |
| 5. ቀዳማዊ ዳርዮስ | 521 - 486 | » |
| 6. ቀዳማዊ ዘራክሰስ /አሸዊሮስ/ | 485 - 465 | » |
| 7. ቀዳማዊ አርጤክስስ | 465 - 424 | » |
| 8. ዳግማዊ ዳርዮስ | 423 - 405 | » |
| 9. ዳግማዊ አርጤክስስ | 404 - 359 | » |
| 10. ሳልሳዊ አርጤክስስ | 358 - 338 | » |
| 11. አርሳከስ | 337 - 336 | » |
| 12. ሳልሳዊ ዳርዮስ | 335 - 333 | » |

## 3. የግሪክ መንግስት ነገስታት - የዲዮዲቺ ኢምፓየር

| | | |
|---|---|---|
| 1. ትልቁ እስክንድር | 333-323 ዓ.ዓ. | |
| *ከ323 ዓ.ዓ. በፊት ጀምሮ በግብፃውያን አገዛዝ ሥር የተገዙበት* | | |
| 2. ቀዳማዊ ኘቶሎሚ ሶተር | 323 - 282 | ክ.ል.በ |
| 3. ዳግማዊ ኘቶሎሚ ፊላደልፈስ | 282 - 246 | » |
| 4. ሳልሳዊ ኘቶሎሚ ኢውርጌትስ | 246 - 222 | » |
| 5. አራተኛ ኘቶሎሚ ሎፓተር | 222 - 205 | » |
| 6. አምስተኛው ኘቶሎሚ ኢጲፋነስ | 204 - 180 | » |
| 7. አራተኛ ኘቶሎሚ ፊሎሜቶር | 180 - 145 | » |
| ከ180 - 175 በሦርያ አገዛዝ ሥር የተገዙበት | | |
| 8. አራተኛው ሴሉከስ ፊሎፓተር | 187 - 175 | ክ.ል.በ |
| 9. አራተኛው አንቲዎከስ ኢፒፋነስ | 175 - 163 | » |





መቃባውያን ከሶርያውያን ጋር ከ 175 ክ.ል.ቢ ጀምሮ መዋጋት ጀመሩ። ይህም ካህኑ መቃቢስ /ማታቲስ/ እና አምስት ልጆቹ ነበሩ። እነርሱም በጦርነቱ ሞቱ። ከዳዊት ሐረግ ባይሆኑም እንደ ንጉሥ በመሆን ገዙ።

| | |
|---|---|
| 1. ማታቲያስ /መቃቢስ/ አባት | በ166 ክል.በ ሞተ። |
| 2. ኤልአዛር /ልጁ/ | 161 ክ.ል.በ በጦርነት ላይ ሞተ። |
| 3. ይሁዳ መቃቢስ /ልጁ/ | 161 ክ.ል.በ በጦርነት ላይ ተገደለ። |
| 4. ዮሐንስ /ልጁ/ | በ160 ክ.ል.በ በሰው ተገደለ። |
| 5. ዮናታን /ልጁ/ | 143 ክ.ል.በ በሰው ተገደለ። |
| 6. ስምዖን /ልጁ/ | 134 ክ.ል.በ በመርዝ ተገደለ። |
| 7. ዮሐንስ ሐይርካኑስ | 134- 104 ክ.ል.በ |
| 8. ቀዳማዊ አርስቶቡሉስ | 104- 103 » |
| 9. እስክንድር ጃናኡስ | 103- 76 » |
| 10. ሶሎሜ አሌክሳድራ | 76 - 67 » |
| 11. ዳግማዊ አርስቶቡለስ | 67 - 63 » |
| 12. ሳልሳዊ ሀይርካኑስ | 63 - 40 » |
| 13. አንቲጎኖስ | 40 - 37 » |

## 4. የሮም ነገሥታትና ገዢዎች

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፖምፔ ኢየሩሣሌምን ወግቶ የያዛት 63 | ክ.ል.በ | |
| 2. ንጉስ ሄሮድስ | 40/37-4 | » |
| 3. ንጉስ ኤርኬላዎስ | 4/-6 | ዓ.ም. ክ.ል.በኋላ |

የሮም ገዢዎች /መሳፍንት/

| | | |
|---|---|---|
| 1. ኮፖኒዩስ | 6- 9 | ዓ.ም (ክ.ል.በኋላ) |
| 2. አምቢዩስ | 9- 12 | » |
| 3. አኒዩስ ሩፉስ | 12- 15 | » |
| 4. ቫሊሪዩስ ግራቱስ | 15- 26 | » |
| 5. ጴንጤናዊው ጲላጦስ *(ማቴ. 27:1-2)* | 26- 36 | » |
| 6. ማርሴሉስ | 36- 37 | » |
| 7. ሂራኒዩስ ካፒቶ | 37- 41 | » |
| /ንጉስ አግሪጳ (ሐሥ.12:1-2) | 41- 44 | » |
| 8. ኩስፒስ ፋዱስ | 44- 46 | » |
| 9. ጢባርዩስ ጁሊየስ | 46- 48 | » |
| 10. ሸንቲዲዩስ ኩማኑስ | 48- 52 | » |
| 11. አንቶኒየስ ፊልክስ *(ሐሥ.23:24)* | 52- 60 | » |

12. ጶርቅዮስ ፊስጦስ (*ሐሥ.24:27*) 60- 62 »
13. ቀላውዲዎስ አልቢነስ 62- 64 »
14. ጊስዩስ ፍሉሩስ 64- 66 »

በ66 ዓ.ም የአይሁድ ጦርነት ተነሳ በ70 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ተደመሰሰች:: የእስራኤል ህዝብ በዓለም ተበተኑ::

*የሮማውያን ነገሥታት*

1. አውግስጦስ (*ሉቃ.2:1*) 27 ዓ.ዓ. - 14 ዓ.ም(ከ.ል.በኋላ)
2. ጢባርዩስ (*ሉቃ.3:1*) 14- 37 »
3. ካሊጉላ 37- 41 »
4. ቀላውዲዎስ (*ሐሥ.18:2*) 41- 54 »
5. ኔሮ 54- 68 »
6. ጋልባ / ኦቶ ቢቴሊስ / 68- 69 »
7. ቪስፓሲያን 69- 79 »
8. ቲቶስ 79- 81 »
9. ዶሚታን 81- 96 »
10. ኔርቫ 96- 98 »
11. ትራጃን 98-117 »
12. ሀድሪያን 117-138 »

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው አይሁድ ለመጨረሻ ጊዜ ከ132-135 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) በሮም ላይ አመጹ:: በዚህም አመጽ ግማሽ ሚሊዮን አይሁድ ተገደሉ:: ኢየሩሳሌም በተጨማሪ ለአንድ ጊዜ ተደመሰሰች:: ንጉሱ ሀድሪያን «ኤሊያ ካፒቶሊና» የተባለች የአህዛብ ከተማ ስራ በመጨረሻም ኢየሩሳሌም በአህዛብ ተረገጠች:: እስራኤላውያን ወደ ዓለም ሁሉ በምርኮነት ተበታተኑ (*ሉቃ.21:24*):

30 ዓ.ም ፣ 70 ዓ.ም እና 135 ዓ.ም (ከ.ል.በኋላ) በደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸው ዓመታት ናቸው:: በአስተምህሮአችን ለረጅም ምዕተ ዓመታት የአይሁድን ህዝብ መዋረድ ያመለክቱናል:: ለ100 ዓመታት ምድራዊ ነገስታት የእስራኤልን ልጆች አዋርደዋል:: መሲሁን በመቃወምና ለመጨረሻ የአይሁድ ህዝብ በዓለም መበተን መካከል *100* ዓመታት ጠፍተዋል::

*ለ100 ዓመታት* የእሥራኤል ታሪክ እየደከመ መሄዱን ቀጠለ:: የአይሁድ ህዝብ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ማጣት ብቻ ሳይሆን ቤተ መቅደሱን ቅድስቲቱ ከተማቸውንና በጠቅላላ ሀገራቸውን አጥተዋል:: (በእግዚአብሔር የዓለም ታሪክ ሰዓት ጠቋሚዋ ዝቅተኛ ነጥብ ላይ ደርሳ ቆመች::)






## 2. እስራኤል ተበትና በነበረችበት ዘመን

*«ምድሪቱንም የተፈታች አደርጋለሁ የሚቀመጡባትም ጠላቶቻችሁም ከእርስዋ የተነሳ ይደነቃሉ:: እናንተም ከአህዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፣ ሰይፍንም አስመዝዝባችኋለሁ፣ ምድራችሁም የተፈታች ትሆናለች፣ ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆናሉ (ዘሌ.26:32-33)::*

*«በእነዚህ አህዛብ መካከል ዕረፍት አታገኝም፣ ለእግርህም ጫማ ማረፊያ አይሆንም፣ በዚያ እግዚአብሔር ተንቀጥቃጭ ልብ፣ ፈዛዛ ዓይን ደካማም ነፍስ ያመጣብሃል:: ነፍስህም ታመነታለች፣ ሌሊትና ቀንም ትፈራለህ፣ በህይወትህም አትታመንም» (ዘዳ.28:65-66)::*

ለ1800 ዓመታት የእሥራኤል ልጆች በዓለም ህዝብ መካከል ተበታተኑ:: ብዙ ጊዜ በአስፈሪ ሁኔታ ስር መኖሪያ እንደሌላቸው ሆነው እንዲኖሩ ተገደዱ:: ለብዙ ዓመታት ሰላምን አጡ:: በአንፃሩ ግን ሊገመት የማይቻል ስቃይ ደረሰባቸው ተሰደዱ፣ ተጣሉ ፣ተጨነቁ ተንቀውም ተገርፈዋል:: እግዚአብሔር የሰጣቸው ምድር በውጭ ገዢዎች እጅ ተደመሰሰች፣ ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ እንደተነበየው ምድራቸው የተጣለ ሆነ (*ማቴ.23:38*): ለ1800 ዓመታት በመበታተን ጊዜያቸው እስራኤላውያን በአሕዛብ የተረገጡ ሆኑ:: ከ70 ዓ.ም. በአድናቆት እስከተመለሱበት እስከ 19ኛው ምዕተ ዓመት (*ሉቃ.21:24*) የሚቅጥለው ሥዕላዊ መግለጫ እግዚአብሔር ቅድስቲቱን ምድር እንዲረግጡአት የፈቀደላቸውን ሕዝቦች ዝርዝርና *በሉቃ.21:24* የተተነበየውን አሳዛኝ እውነት አስረግጦ ያሳያል::



## የአህዛብ ኢየሩሳሌምን መርገጥና ለማጥፋት መፈለጋቸው

### 1. ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት

1492 ወይም 1502 -- 1448 የእሥራኤል ህዝብ ከግብፅ ወጡ:: ፈርዖንና ሠራዊቱ በቀይ ባህር ውስጥ ሰመጡ፣

1452 ከ1052 በመጀመር በመሳፍንትና በነገሥታት ዘመን ሞአባውያን፣ ምድያማውያንና ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ለማጥፋት ፈለጉ፣

1052 ሳዖል ንጉስ ሆነና እስከ 1012 ለ 40 ዓመታት ገዛ፣

1012 ዳዊት በይሁዳ ላይ ለ 76 ዓመት ተኩል ነገሰ፣

1004 ዳዊት ኢየሩሳሌምን አሸነፈና በመላ እሥራኤል ላይ ለ33 ዓመታት ነገሠ፣

972 ሶሎሞን ለ 40 ዓመታት በእሥራኤል ላይ ነገሰ ቤተ መቅደሱንም ሠራ፣

932 በነገስታት ዘመን ግብጻውያን ፣ ሶርያውያን ፣አሞናውያን፣ ሞአባውያንና አሦራውያን የእሥራኤልን ነገድ ለማጥፋት ሞከሩ፣

722 የሰሜኑ የእሥራኤል መንግስት ተደመሰሰ፣አስሩ የሰሜን ነገዶች በአሶራውያን ምርከኞች ሆነው ተወሰዱ፣

606 ለመጀመሪያ ጊዜ አይሁድ ወደ ባቢሎን ተማረኩ፣

597 አይሁድ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ባቢሎን ተማረኩ፣

586 ለሦስተኛ ጊዜ አይሁድ ወደ ባቢሎን ተማርከው የይሁዳ መንግስት ተደመሰሰ፣ ባቢሎናውያን ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን አፈረሱ::

536 የባቢሎን መንግስት ተደመሰሰ ፣ የሜዶንና የፋርስ ነገስታት የዓለም ገዢ ሆኑ፣የአይሁድ ህዝብ እንዲመለሱና ቤተ መቅደሱ እንዲሰራ ፈቀዱ፣

516 ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ታድሶ ተመረቀ፣

451 በ445 ነህምያ እንደገና የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሠራ፣

333 ግሪክ በትልቁ እስክንድር በመመራት በዓለም ኃያል ሆነች፣ በ332 እሥራኤል በግሪክ አገዛዝ ስር ወደቀች፣

312 እስራኤል በግብጽ ይገዙ በነበሩት በግሪክ (በፓቶሎሚክ) ነገሥታት ሥር ሆነች፣

198 እስራኤል በሦሪያ ሴሉሳውያን ሥር ሆነች፣

167 የሦርያው ንጉስ አንቲዖከስ ኤርፋነስ ኢየሩሣሌምን አሸንፎ የጥፋት ርኩሰትን በቤተ መቅደስ ተከለ፣





164 መመረቅ ኢየሩሣሌምን አሸነፈና ቤተ መቅደሱ ታደሰ:: /የቤተ መቅደሱ (ቻኑካ) በመባል ይታወቃል /(ዮሐ.10:22)::

142 የመቃባውያን ነገሥታት ለ100 ዓመታት ያህል እሥራኤልን መሩ፣

63 የሮሙ ጀኔራል ፓምፔ ኢየሩሣሌምን አሸነፈ፣

40 ኤዶማዊና አረባዊ የሆነው ሄሮድስ በእሥራኤል ላይ ንጉስ ሆነ፣

06 ወይም 07 ጌታ ኢየሱስ በቤተ ልሔም ተወለደ፣

04 ሚያዝያ 2 ቀን ሄሮድስ በኢያሪኮ ሞተ ልጁ አርኬላዎስ በእሥራኤል ላይ ንጉሥ ሆነ (ማቴ. 2:22)::

### 2. ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ

06 አርኬላዎስ ከመንግስቱ ተሻረ፣ ይሁዳ በሮም ጠቅላይ ግዛቶች ላይ ነገሰ

06-66 የሮም ገዢዎች ምድሩን ገዙ፣

26-36 ጴንጤናዊው ጲላጦስ በይሁዳ ላይ መሪ ሆነ፣

18-37 ዮሴፍ ቀያፋ በኢየሩሳሌም የሊቀ ካህንነቱን ቦታ ያዘ፣

33 የክርስቶስ ኢየሱስ ስቅለትና ትንሣኤ ፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ሆነ፣

66-73 አይሁድ በሮማውያን ላይ አመጹ፣ /የአይሁድ ጦርነት/ ሮማውያን 1.1 ሚሊዮን የሚሆኑ አይሁድን ገደሉ ፣

70 በሮሙ ጀኔራል ታይተስ በመመራት ሮማውያን ኢሩሳሌምን አሸነፉ፣ ነሐሴ 10 ቀን ቤተ መቅደሱን ደመሰሱ 600.000 አይሁዶችን ገደሉ፣

73 ከሦስት ዓመት ትግል በኋላ በሙት ባህር አጠገብ ያለችውን፣ ማሳዳን ሮማውያን አሸነፉ፣ሚያዝያ 15 ቀን 960 አይሁድ ራሳቸውን ገደሉ፣

132 ሦስቱ የባርኮቺባ የዓመጽ ዓመታት ጊዜ ሮማውያን 500.000 አይሁድን ገደሉ፣

135 ንጉሱ ሀድሪያን ኢየሩሳሌምን የአህዛብ ከተማ በማድረግ «አይላ ካፒቶላ» ብሎ ሰየማት፣

135 ሮማውያን ቅድስቲቷን ምድር እስከ 326 ዓ.ም.(ክ.ል.በኋላ)ድረስ ገዟት፣

326 በባዛንቲን አገዛዝ ስር እስከ 632 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም የክርስቲያን ከተማና

638 በካሊፍ ኡመር መሪነት አረቦች ቅድስቲቱን ከተማ አሸነፉ፣

687 የኡመር መስጊድ /ዱም ኦፍ ሮክ/ በአራት አመት ጊዜ ውስጥ በኢየሩሳሌም ከነበረው ቤተ መቅደስ ተራራ ላይ ተሰራ፣

711 የኤል-አስካ መስጊድ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተራራ ላይ ተሰራ፣
750 ከባግዳድ የተነሳው ሙስሊም አባሲድ ኢየሩሳሌምን አሸንፈና ቅድስቲቱን ምድር አስደተዳደረ።
996 እስከ 1071 ፋቲሚድስ በኢየሩሳሌም ላይ ገዙ፣
1071 እስከ 1099 ሴልጁኮች በቅድስቲቷ ምድር ላይ ገዙ።

## 3. የመስቀል ጦርነት ዘመን

1095 ሊቀ ጳጳስ ዳግማዊ አርባን ህዳር 27 ቀን በፈረንሳይ በስተደቡብ በምትገኘው በክሌርሞንት የመጀመሪያውን የመስቀል ጦርነት ጥሪ አደረጉ። የ 200 ዓመታት የአይሁድ ስደት ጅማሬ መነሻ ሆነ።
1099 ወደ ኢየሩሳሌም በተደረገው ጉዞ የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች ከ100. 000 በላይ አይሁድንና እስላሞችን ገደሉ። በሐምሌ 15 ቀን ኢየሩሳሰምን አሸንፈው በያዙበት ጊዜ 65.000 አይሁድና እስላሞችን ገድለዋል።
1099 ጎድፍሪይ የቦውይኑ የጌታን መቃብር ጠባቂ ሆነ ፣
1100 የመስቀል ጦረኞች በሃይፋ ያሉትን አይሁድ በሙሉ ገደሉአቸው።
1101 የቦሎኙ ቀዳማዊ ቦልድዊን የኢየሩሳሌም ንጉስ ሆነ ፣
1118 የሊቦርጉ ዳግማዊ ቦልዊድን በኢየሩሳሌም ገዛ ፣
1131 የአንጁ ፉልክ በኢየሩሳሌም ላይ ገዛ ፣
1143 ሳልሳዊ ቦልድዊን በኢየሩሳሌም ላይ ንጉስ ሆነ ፣
1147 ሁለተኛው የመስቀል ጦርነት ጀመረ ፣ ብዙ አይሁድ ተገደሉ።
1162 የሊቦርጉ አማላሪክ የአየሩሳሉም ንጉስ ሆነ ፣
1174 አራተኛው ቦልድዊን በኢየሩሳሌም የበላይ ገዢነቱን ወሰደ ፣
1187 በገሊላ ባለችው የሃቲን በሆነችው ሆርን በተባለችው ቦታ የኩረዱ ሱልጣን ሳላዲን የመስቀል ጦረኞችን በጅምላ ግድያ ደመሰሳቸው።
1187 ሰላዲን በኦክቶበር 2 ኢየሩሳሌምን በመያዝ የ88 ዓመት የፈረንሳይ መስቀል ጦረኞችን ግዛት አስቆመ።
1189 አውሮፓውያን በንጉስ ባርባሮሳ መሪነት በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት መልሰው ኢየሩሳሌምን ድል ለማድረግ መከሩ፣
1202 አራተኛ የመስቀል ጦርነት ልጆችን ያቀፈ ነበር ፣
1228 በዳግማዊ ንጉስ ፍሬድሪክ አምስተኛው የመስቀል ጦርነት ተመራ ፣
1241 እንደ ገና የመስቀል ጦረኞች ኢየሩሳሌምን አሸነፉ ፣





1244 ሙስሊሞች ለዳግመኛ ጊዜ ኢየሩሳሌምን አሸነፉ ፣
1248 ዘጠነኛው የፈረንሳይ ንጉስ ሉዊስ ስድስተኛውን የመስቀል ጦርነት መራ፣
1260 የማምሉክ ሱልጣን ባይባረስ ቅድስቲቷን ምድር አሸነፈ፣
1291 ማምሉኮች የመስቀል ጦረኞችን አስወጡ ፣
1291 እስከ 1517 ድረስ ማምሉኮች ቅድስቲቷን ምድር ገዙ።

## 4. የመካከለኛው ዘመን

1400 ማንጎለውያን በታማርላን መሪነት ቅድስቲቱን ምድር ደመሰሱ፣
1517 የቱርክ ቀዳማዊ ሱልጣን ሳሌም ኢየሩሳሌምን አሸነፈ፣
1517 እስከ 1417 ቱርኮች ቅድስቲቱን ምድር አስተዳደሩ፣
1537 እስከ 1541 የቱርክ ሱልጣን ትልቁ ሱሌይማን እስከ ዛሬ የሚታየውን የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥር ሠራ፣
1799 ናፓሊዮን ቅድስቲቱን ከተማ ለማሸነፍ ፈልጎ ሙከራው ውጤት የሌለው ሆነና ቱርኮችን በሚጊዶ አጠገብ ተዋጋቸው፣
1832 የግብጽ ኪዳቮ ፓለስታይንን አሸነፈ፣
1840 ቅድስቲቷን ምድር ካወጡት ከአውሮፓ የበላይ ሃይሎች ቱርኮች እርዳታ ጠየቁ፣
1846 ከ700 አመታት በኋላ ሙስሊሞች የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም እንዲሰራ ፈቀዱ።
1860 ሰር ሙሴ ሞንቴፎር ከተማይቱን እንዲሰሩ የአይሁድ ሕብረት ፈጠረ፣
1882 በፓለስታይን የመጀመሪያው የአይሁድ መስፈር ሆነ፣
1894 የድሬፉስ ፍርድ በአውሮፓ ያሉትን አይሁድ አናጋ፣
1896 ቴዎድሮ ሀርዝል « ዘ ጁዊስ ስቴት » የተባለውን መጽሐፍ አሳተመ፣
1897 ቴዎድሮ ሀርዝል ከነሐሴ 29 ቀን እስከ ነሐሴ 31 ቀን በባሲል የተደረገውን የጽዮናውያን ኮንግሬስ ጥሪ አደረገ፣ በስብሰባውም 199 አባሎች ተሰበሰቡ፣
1898 ጥቅምት 31 ቀን የሚመረቀው የአዳኙን ቤተ ክርስቲያን ለመመረቅ ግርማዊ ንጉስ ዊልሂለም ኢየሩሳሌምን ጎበኘ፣
1917 ፓለስታይን የአይሁድ ምድር መሆኑን ተስፋ የሰጠውን የባልፎሩን ዲክላሬሽን በህዳር 2 ቀን የእንግሊዙ ፓርላማ አሳተመ፣
1917 ታህሳስ 9 ቀን እንግሊዞች ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ፣ ይህም ለ 400 ዓመታት የቆየውን የቱርክን አገዛዝ እንዲያከትም አደረገው፣

1918 የእንግሊዝ ወታደሮች ጠቅላላውን የቅድስቲቱን ምድር አሸነፉ፣

1922 ዘ ሊግ ኦፍ ኔሽንስን /ዛሬ የተባበሩት መንግስታት የተባለው/ በፓሊስታይን ላይ ያለውን ሞግዚትነት ለእንግሊዞች በሐላፊነት ለጡ። በግንቦት 15 ቀን 1984 ተግባራዊ ሆነ፣

1947 ህዳር 29 ቀን የተባበሩት መንግስታት ፓለስታይንን ለመክፈል ወሰኑ፣

1948 ግንቦት 14 ቀን ዳዊት ቤን ጉርዮን በአቪብ ከተማ ባለው ሙዝዬም የእስራኤልን ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ አወጀ፣

1967 በስድስቱ ቀን ጦርነት እስራኤል ጠቅላላ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀለላቸውን ምድር አሸንፈው ያዙ። ኢየሩሳሌም ማንም የማይጋራቸው ዋና ከተማቸው ሆነች።

## 5. የፍርሃትና የጥፋት ሚዛን

1017 ፖኘ ቤንዲክት ስምንተኛው አይሁዶች በሮም ራሳቸው እንዲቆረጥ ፈቀዱ፣

1020 ፓፕ ቤንዲክት ስምንተኛው አይሁዶች በሮም እንዲቃጠሉ ፈቀደ፣

1066 አይሁድ በእስፓኝ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ፣

1095 ፓፕ አርበን ዳግማዊ በፈረንሳይ በስተ ደቡብ በምትገኘው ኬሌርሞንት ህዳር 27 ቀን የመጀመሪያውን የመስቀል ጦርነት ጥሪ አደረገ። ይህም ለ200 ዓመታት የአይሁድ ስደት ጅማሬ መነሻ ሆነ።

1096 በመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት በሲኒካን የጦር መሪ በጀርመን ከተሞች ዎርም፣ ጊልደን፣ከርጵን፣ዌስል፣ኒዩስ፣ሞርስ፣ ግደርቪንቡሮች፣ዙንታን፣ቦን፣ ኮሎኝ፣አልቴናር፣ ሜይንዝ፣ ስፔይር፣ ትሪይናርና፣በሌሎቹ ከተሞች ሊሲሲንግ ፣ መኳንንት መሪዎች ከ 12,000 በላይ አይሁዶች ተገደሉ።

1096 የመስቀል ጦረኞች በፕራግ ያሉትን የጅምላ ግድያ ፈጸሙባቸው፣

1171 በፈረንሳይ በብሉይዝ ያሉት አይሁዶች በመቃጠል ተገደሉ፣

1179 ፓፕ ኢኖሰንት ሳልሳዊ በላተራን ጉባኤ አይሁድ በራሳቸው ክልል /ጌቶስ/ እንዲቀመጡ አዘዙ፣

1189 በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ጊዜ በእንግሊዝ ከተማዎች አይሁዳውያን ታርደው ተገደሉ።

1194 በጀርመን ከተማ በኒዮስ የአይሁዳውያን ቤተሰብ የሆኑ እናትየው ከነህይወትዋ ስትቀበር አጎትየው በግርፋት እንዲሰቃይ ተደረገ ፣

1209 በፈረንሳይ በቢዚየር የሚኖሩት አይሁዳውያን በሙሉ ተገደሉ ፣





1215 በአራተኛው የላተርን ጉባኤ ላይ ፖፕ ኢኖሰንት ሳልሳዊ ማንኛውም አይሁዳዊ አንድ ዓይነት ልብስ/የዳዊት ኮከብ ያለበት ባጅ/ /ዩኒፎርም/ እንዲለብሱ አዘዙ

1221 በጀርመን በኢርፉት የአይሁድ መኖሪያ ተደመሰሰ ፣አይሁዳውያን በሙሉ ተገደሉ፣

1241 በጀርመን በፍራንክፈርት የነበረው የአይሁድ ቦታ ተወሰደ ፣ 200 አይሁዳውያን ተገደሉ ፣

1247 በፈረንሳይ በቫለሪስ የነበሩት አይሁድ በሙሉ ተገደለ ፣

1265 በጀርመን በራይን ወንዝ አጠገብ ባለችው በሲንዚንግ ከተማ ያሉት አሁዳውያን በሙሉ ድራሻቸው እንዲጠፉ ሆነ ፣

1270 በዊለንበርግ ፣ ያሉት አይሁዳውን በሙሉ ተገደሉ ፣

1278 በኢንግላንድ የነበሩት 300 የአይሁድ መሪዎች ተሰቀሉ፣

1283 በጀርመን ከተሞች በከሩዝናች ፣ በሜይንዝ ሜልሪች ስታድ አይሁዶች በጅምላ ተገደሉ ፣

1285 በሙኒች ምኩራብ የነበሩት አይሁዳውያን ተቃጠሉ ፣

1287 በጀርመን ከተማዎች በዌስል ፣ ቦፓርድ ፣ በኮርበን ፣ በናሂ ባለችው በኪርን ፣ ለሐንስቲን ፣ በራሂን ባለችው በቡራውባችና ሙንስትር ማይፌልድ ያሉት በሙሉ በጅምላ ተገደሉ፣

1288 104 አይሁዳውያን በጀርመን በቦን ከተማ ተገደሉ ፣

1289 በፈረንሳይ በትሮይስ 13 አይሁዳውያን ተቃጥለው ተገደሉ ፣

1290 በቀዳማዊ ንጉስ ኢድዋርድ ትዕዛዝ ከኢንግላንድ አይሁድ እንዲወጡ ተደረጉ

1298 በናይት ሪንደፍሊሶች በተደረገው ስደት በደቡባዊ ጀርመንና በአውስትሪያ 146 ማህበረ አይሁድ ተደመሰሱ። ከ20,000 በላይ አይሁዳውያን ተገደሉ። ግድያ የተፈጸመባቸው ዋናዎቹ የጀርመን ከተማዎች ኑርበርግ፣ባምበርግ፣ሮቷንጃን፣በርቼንግ፣ከሩዚም፣ሞሰባች፣አቼስንፈርትዎዝንበርግ፣ ዊንድዚም ፣ ዊንድዚም ፣ ሮተንበርግ፣ታውጅንና ሌሎችም ነበሩ።

1306 በዳግማዊ ፊልጶስ ከፈረንሳይ አይሁዶች እንዲወጡ ተደረጉ ፣

1321 5000 አይሁዳውያን በደቡባዊ ፈረንሳይ ተገደሉ ፣ በቺኖን የነበሩት አይሁዳውያን ማህበር ተቃጥለው ተገደሉ ፣

1328 በናቪር በፈረንሳይ 5000 አይሁድ በጅምላ ተገደሉ ፣

1332 በከንስታን ሀይቅ ባለችው አርበርሊንገር 400 አይሁዳውያን ተቃጠሉ ፣

1337 በዲጀንደርፍ (በባሪያ ባለችው) የሚኖሩት አይሁዳውያን በጅምላ ተገደሉ፣

1348 በመላ ኢሮፕ / በስፓኝ ፣ በፈረንሳይ . . . ወዘተ. / የቸነፈሩ ምክንያት በከንስታን ሀይቅ ባለችው በሊንዳ የሚኖሩት ፣ በኒከር ባለችው ሆርብ ፣ ኢስሊንግ ፣ ሩትሊንግ ፣ አውግስበርግ ፣ ኮልማርና ኑርበርግ የነበሩት የጀርመን አይሁዳውያን ማህበር ተደመሰሱ::

1349 በቸነፈሩ ምክንያት የአይሁዳውያን ስደት በጀርመን ከተሞች በብርስለው፣ በዊትዝላር፣ሜይንዝ፣ስኮሎኝ፣በራደልፍሩል፣በውዝበርግ፣በፍርድሪችሻፈር፣ በማይን ፍራንክፈርት፣ በድርስዲን፣ በፍልዳ፣በራቬንስበርግ፣ በከንስታን በስፔየር፣በኢለም፣በፍርበርግ፣በስታራስበርግና ስዊስ ከተሞች በዊንተርሁር፣ በዲሲንሆፈን፣ በቻፍሐውስን፣ በዙርጋ፣ በዙሪች፣ በባዲን፣በሪሁን ፊደን፣ በቅድስት፣ ጋለን፣ በባሴልና በአሚንታል /በሮን/ ተሰራጩ::

1349 2,000 አይሁዳውያን በስትራስበርግ በአደባባይ በህዝብ ፊት ተቃጠሉ::

1355 ፓፓ ቤንዲክት 12ኛው ፐሯግ ያለው የአይሁድ ምኩራብ እንዲፈርስ ፈቀዱ፣

1391 በስፓኝ ባለችው በሲቬላ 5000 የአይሁዳውያን ቤተሰቦች ተደመሰሱ:: 23 የአይሁድ ምኩራቦች ተደመሰሱ::

1391 በዳንዩብ ወንዝ አጠገብ ባለችው በኢንዝ የጀርመን ከተማ 200 አይሁዳውያን ተቃጠሉ::

1391 በመጀመሪያው ሃይለኛ በሆነው የስፔን አይሁዳውያን ስደት ጊዜ በማቃጠያው ስፍራ 20,000 የሚሆኑ አይሁዳውያን በእሳት ነደዋል::

1404 በአውስትሪያ ባለችው በስልዝበርግ የነበሩት አይሁድ በሙሉ ተቃጠሉ፣

1421 212 አይሁዳውያን /ወንድና ሴት/ በቪና አውስትሪያ ተቃጠሉ፣

1478 ግልጽ የሆነው የእስፓኝ ምርመራ ጅማሬ፣

1483 በብዙ የስፓኝ ከተማዎች በካቶሊኮች በተደረገው ምርመራ 30,000 አይሁዳውያን በግልጽ በአደባባይ ተቃጠሉ::

1492 የአርጉኑ ዳግማዊ ፌርዲናንድና የካስቲሏ ኢሳቤላ አሁዳውያን በሙሉ ከእስፓኝ እንዲወጡ አደረጉ ፣

1494 የጳጳሱን አዋጅ በመከተል በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን ጠንቋዮች ናቸው ተብለው በመገመታቸው በብዙ የአውሮፓ ከተሞች በጭካኔ ተገደሉ::





1496 በንጉሥ ማግከስ ሚላን ቀዳማዊ መላ አይሁድከኦስትሪያ እንዲወጡ ተደረጉ::

1497 አይሁዳውያን በሙሉ ከፖርቱጋል እንዲወጡ ተደረጉ፣

1501 በስፓኝ ባለችው ቶሊዶ ብዙ አይሁዳውያን ተቃጠሉ፣

1504 በሩሲያ ሞስኮ የታወቁት አይሁዳውያን በሙሉ ተቃጠሉ፣

1506 በፖርቱጋል ሊስበን 2000 አይሁዳውያን ተደብድበው ተገደሉ፣

1510 በጀርመን በርሊን 38 አይሁዳውያን ተገረፉና ተቃጠሉ፣

1574 በሜክሲኮ 897 አይሁዳውያን በአደባባይ ተቀጠሉ፣

1614 በጀርመን በፍራንክፈርት የአይሁዳውያን ቦታ ተደመሰሰ፣

1648 በቦግዳን ቼ ሚሊኒኪ፣ በሩሲያውያን፣ በኮሳኮች በዩክራውያን 12,000 አይሁዶች በጅምላ ተገደሉ፣

1648 በፓላንድ ውስጥ ባሉት ኮሳኮች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉና ተወገዱ፣

1650 በሩሲያ ባሉት ኮሳኮች ሌሎች 200,000 አይሁዳውያን ተገደሉና ተደመሰሱ·

1670 በቀዳማዊ ሊዎፓልድ 4.000 አይሁዳውያን በኦስትሪያ ካለችው ቪና እንዲወጡ ተደረጉ ፣

1670 እስራኤላውያን ሁሉ ከሜር(ፈራንሣይ) ተባበሩ

1679 በፈረንሳይ ባለችው ሚትዝ ያሉት አይሁዳውያን እንዲወጡ ተደረጉ፣

1680 በማድሬድ /አውቶዳፍ/ በአደባባይ በእንጨት ላይ ተሰቅለው ተቃጠሉ፣

1704-1769 በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በፖርቱጋል ተገደሉ ፣

1728 ከሊምበርግ/ ሊቮቭ / ፋሊሺያ እንዲወጡ ሆነ ፣

1734 በፓላንድ ባሉት ጌድማኪያን ኮሳኮች 20,000 አይሁዳውያን ተገደሉ ፣

1818 በጀርመን ዎርዝበርግ ከተማ ብዙ አይሁዶች ተገደሉ፣ የቀሩት 400 እንዲወጡ ተደርጎ ሂፕ ሂፕ የሚለው የጩኸት ግሳት ፈነዳ:: ትርጓሜው ኢየሩሳሌም ታጣች (ኢየሩሳሌም ጠፋች ማለት ነው)::

1821 ወደ ብዙ የሩሲያ ከተሞችና ወደ ዩክሬይን የተዛመተው የተጠናከረው የመጀመሪያው አሰቃቂ ግድያ የተጀመረው በኦዲሳ ነው:: ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት መነሳት በፊት ብዙ አይሁዶች ሞተዋል::

1826 በእስፓኙ ምርመራ የመጨረሻው ግድያ፣

1840 በደማስቆ ያሉት የአይሁድ መሪዎች በሀሰት ተከሰሱና ብዙ ስቃይ እንዲቀበሉ ሆኑ፣ በውጤቱ ጥቂቶች ሞቱ፣

1858 በተጠናከረው ግድያ ውጤት በሺና በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን በሩሲያ ሞቱ ፣

1859 የተጠናከረው ግድያ እስከ 1871 ድረስ በአዲሳ በመደጋገም ቀጠለ፣

1864 በሞሮኮ ቁጣ የተሞላበት ታላቅ የአይሁዳውያን ግድያ ሆነ ፣

1867 በሩማኒያ ታላቅ የአይሁድ ስደት፣ ተደረገ።

1881 792 አይሁዳውያን በዩክራይን ባለች ኪሾ ሰሞት ተደረጉ፣

1881 አሰቃቂ የሆነ ግድያ በኤሊስቤት ግንድ ኡክራኢን እና 1882 በባልታ ኡክራኢን

1883 ጭካኔ የተሞላበት የተጠናከረ ግድያ በደቡባዊ ሩሲያ (በደቡብ ሮስቶቭ) ተካሄደ፣

1891 በሩሲያ ሞስኮ ያሉት አይሁዳውያን ከሃገር እንዲወጡ መደረግ ፣

1892 በፓላንድ ሉድዝ 20 የአይሁድ ሰዎች ተገደሉ፣

1903 በሞልዳቪያ ባሉት ኪሺኒቭና ጎሜል ጭካኔ የተሞላበት ግድያ ሆነ፣

1905 በብላክ ሃንድረስ በተፈጠረው ምክንያት በ 700 የሩሲያና የዩክሬንያ ከተሞች የተጠናከረ ግድያ ሆነ፣

1917 በመደጋገም በሆነው የተጠናከረ ግድያ በሩሲያና በዩክሬይን ከ1200 ከተሞች በላይ 30,000 የአይሁድ ወንዶች ፣ ሴቶችና ህፃናት ተገደሉ። ይህም እስከ 1921ዓ.ም ድረስ ቀጠለ።

1917 በገላትያ ውስጥ ባለችው ካሉዝ አስከፊ ጭካኔ የተሞላበት ግድያ በአይሁድና በፖላንዳውያን ሴቶች ላይ ተደረገ ልጃገረዶችን በመግረፍ አሰቃዩ።

1919 በሩሲያ ባለችው ፕሮ ኩሮቫ በተጠናከረው ግድያ 1500 አይሁዶች ለግድያ አልፈው ተሰጡ።

1919 እስከ 1921 በዩክሬናውያን ብሔራዊ ሠራዊት ከ 100 በላይ የተጠናከረ ግድያ በማካሄዳቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያ ተገደሉ፣

1922 የጀርመን የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ዋልተር ራዚናው በጀርመን በበርሲን ከተማ አይሁዳዊ ስለነበር በብሔረተኞች ተገደለ፣

1929 ፓለስታይን ውስጥ ባለችው በኬብሮን የሚኖሩት አይሁዶች በሙሉ በአረቦች ተገደሉ ወይም ሀገር ለቀው እንዲወጡ ተደረጉ፣

1933 እስከ 1945 በመላ የአውሮፓ ከተሞች 6.5 ሚሊዮን አይሁዶች በናዚ ተገደሉ፣ ከእነዚህም 1.5 ሚሊዮን ከ14 ዓመት በታች የነበሩ ህፃናት ነበሩ።





1936 እስከ 1939 ወደ 500 የሚሆኑ የአይሁድ ወንዶች ፣ ሴቶች ፣ ህፃናት በአረቦች በተነሳ የኑሮና የሥራ ማጣት ሁከት ምክንያት ሞቱ፣

1941 በኢየሩሳሌም ያለው የአረቡ ሙፍቲ ሐጂ አሚን አልሁሴኒ በጀርመን የበርሊንን ከተማ ጎበኘና ሂትለርን በፓለስታይን ያለውን የአይሁዶችን ሥራ በሙሉ እንዲያፈርስ ጥሪ አደረገለት ፣

1945 እስከ 1948 በተደረገው በአረብ ጦርነትና የስደተኞች መርከቦች መስመጥ ምክንያት ብዙዎች ሞቱ ፣

1945 እስከ 1953 በቼኮዝላቫኪያ የሚኖሩ አይሁዶችና ከካምፑ የተሸነፉት ጀርመኖች አንድ ላይ እንዲሰቃዩ ተደርገው ሰሞት አልፈው ተሰጡ፣ ምክንያቱም ሁሉም የጀርመን ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩና።

1948 በአምስት የአረቦች ጦር ግንባር በተደረገው የነፃነት ጦርነት 6,000 ሞቱ 9,000 ቆሰሉ/ የአረብና እስስራኤል ጦርነት / ፣

1956 በስዊዝ ጦርነት ላይ 170 ሞቱ ፣ 700 ቆሰሉ ፣

1967 በስድስቱ ቀን ጦርነት / በአረቦችና በእስራኤል / 800 ሞቱ 2,600 ቆሰሉ ፣

1972 በሙኒክ በተደረገው የኦሎምፒክ ጨዋታ ላይ በአረብ ሽብርተኞች 11 እስፖርተኞች ተገደሉ፣

1973 በሊባኖስ ከነበሩት ወታደሮች 574 ሞቱ፣ 2,780 ቆሰሉ፣

1982 574 የሞቱና 2780 በሌባነን ጦርነት የቆሰሉ

1986 በኢስታንቡል ምኩራብ አምልኮት ላይ እያሉ በቱርኮች አሸባሪዎች 21 ተገደሉ፣

1991 2 በሮኬት ድብደባና 72 ከገልፍ ጦርነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሞቱ ፣

1998 ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ 18,250 ወንዶችና ሴቶች በጦርነቶች ሞቱ እነዚህ ወታደሮች በ25,250 ቤተሰቦቻቸውና 62,120 በተጎዱ ወታደሮች ሀዘን ተደረገላቸው፣

1998 ከ1948 ጀምሮ ከ 2,250 የእስራኤል ወንዶች ፣ ሴቶችና ህፃናት በአረብ አራፋት ሽብርተኖች ተገደሉ። በዓለም አቀፍ የአረብ አራፋት ሽብርተኞች 75 የእስራኤል ዲፕሎማቶች ተገደሉ።

«ደማቸውን ሳልበቀል አላልፍም» እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።(ኢዩ. 4:21)

የእስራኤል ሕዝብ ስደት እንደ ራሷ እንደ እስራኤል ታሪክ የቆየ ነው:: ለአራት ሺህ ዓመታት ያህል የዓለም ሕዝቦች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በእስራኤል ሕዝብ ላይ በታላቅ ቁጣ እየተቃወሙአቸው ነበር:: ከአብርሃም መመረጥ ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ እንደ ቀጠለ ነው:: ምንም እንኳን በ70 ዓ.ም. በሮማውያን በእስራኤል ላይ የተፈጠረው ስደት፣ እስራኤል መሲሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበሏ (ማቴ.23.27-39):: ከእግዚአብሔር የሆነ ቅጣት ቢሆንም እግዚአብሔር ልጆቹ የሆኑትን የእስራኤልን ሕዝብ ጥሏቸዋል ማለት አይደለም:: በዘመናት ሁሉ በአይሁድ ሕዝብ ላይ የወረደው ጭካኔ የተሞላበት ስደትና ጥፋት፣ እንደዚሁም በሂትለር የወረደባቸው መከራ ተጨምሮ፣ እግዚአብሔር ከልጆቹ ጋር አዲስ የደህንነት ታሪክን ከማድረግ አላገደውም:: እስራኤል የእግዚአብሔርን ቅጣት ስረጅም አመታት ብትቀበልም (ኤር.46:28፤ ሮሜ.11:28-29)::

*«አንተ ባሪያዬ ያዕቆብ ሆይ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ ይላል እግዚአብሔር አንተንም ያሳደድሁባቸውን አክዛብን ሁሉ ፈፅሜ አጠፋለሁናን አንተን ግን ፈፅሜ አላጠፋህም በህመም እቀጣሃለሁ ያለ ቅጣትም አልተውህም (ኤር.46:28)::*

ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ዳግም የእስራኤልን ሕዝብ መቀበሉን ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን የእስራኤልን ሕዝብ የተቃወሙትን ሁሉ የሚያጠፋ መሆኑንም ያሳያል:: የእስራኤልን ሕዝብ የሚነካ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነው (ዘካ.2:8፤ ዘዳ.32:10):: ይህ እስራኤልን ስሚነካ ግለሰብም ሆነ ቡድን፣ መላውን የዓለም ሕዝብ የሚያመለክት ነው:: የእግዚአብሔር ፍርድ ተመልሶ እስራኤልን የሚቃወሙትን የሚመታ ነው:: በመጨረሻም የዓለም ሕዝቦች በእስራኤል ላይ የሚያደርጉት ጦርነት በራሱ በእግዚአብሔር ላይ እንደሚደረግ ያህል ነው:: እግዚአብሔር የእነርሱ ነው፣ ኪዳኑም ስተመረጡት ሕዝቦቹ የጸና ነው:: መሲሁን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመቀበሏና ባለመታዘዟ እንኳን ለእነርሱ ያለው ኪዳን የጸና ነው:: እስራኤል ወደ እርሷ የተላከውን መሲሁን ኢየሱስን እውቃ ባትቀበልም እግዚአብሔር ልጆቹን አልጣለም (ሉቃ.13:34፤ሉቃ.19:42):: እስራኤል የተጠላችበትና ጦርነቶች የተካሄደበት እውነተኛው ምክንያት ለእግዚአብሔር የተመረጠች ሕዝብ በመሆኗ ነው:: እስማኤል ይስሐቅን አሳድዶታል፣ ምክንያቱም የተስፋውን ቃል ወራሽ ይስሐቅ ስለነበር ነው:: ኤሳው ያዕቆብን አሳድዶት ነበር:: ምክንያቱም ወደ መሲሁ የሚያመለክተውን ተስፋ የተሸከመው ያዕቆብ ስለ ነበር ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ፈርዖን በግብፅ የሚወለዱትን የእስራኤል ወንዶች ልጆች ወደ ወንዝ እንዲጣሉ አደረገ:: ሃማ ደግሞ መላ የአይሁድን ሕዝብ ከሜዶንና ከፋርስ ግዛት ድራሻቸውን ስማጥፋት ፈለገ::





የዓለም ሕዝብ በዚህ በተመረጠው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ያሰው አመለካከት እስከ ዛሬ ድረስ ያልተለወጠ ነው:: ታሪክ እንደሚያሳየን በእስራኤል ላይ በተቃውሞ የተነሱት ጠላቶቿ ሁሉ ጠፍተዋል:: ገናና የነበረው የሮም መንግስት ወድቋል:: በባቢሎናውያን፣ በሮማውያንና በመስቀል ጦረኞች የተካሄዱት አስቃቂ መከራዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነችውን እስራኤልን ለማጥፋት አልቻሉም:: መንግስታቸው አልፏል፣ እስራኤል ግን እስከ አሁን አለች::

### 3. የእስራኤል ሕዝብ መመለስ

19ኛው ምዕተ ዓመት በዓለም ተበታትነው ለነበሩት የአይሁድ ሕዝብ ትልቅና ድንገተኛ የሆነ ለውጥ አሳየ:: የፈረንሳይ ገገር ናፖሊዮን በፈረንሳይ ስሚኖሩት የአይሁድ ሕዝቦች የዜግነትን መብት ፈቀደላቸው:: አስደናቂው ነገር ደግሞ ሌሎች አገሮችም ይህንኑ ተከተሉ:: በፕሩሲያ፣ በኢንግላንድ፣ በአውስትሪያና በኢጣልያ የሚኖሩት አይሁድ የዜግነት መብት ተፈቀደላቸው:: ከዚህ በፊት ያላወቁት ብዙ እድሎች የሥራ መስክ ተከፈተላቸው:: በጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ አይሁዶች ነጋዴዎች፣ ዶክተሮች፣ የጦር መኮንኖች፣ የፓርላማ ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች መሆን ጀመሩ:: በተከታዩ ምዕተ ዓመት በአውሮፓ ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች የነጻነትን ኑሮ መኖር ጀመሩ::

ይህ ነጻነት በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በደህንነት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታን እንዲያገኙ አድርጓል:: ምክንያቱም አይሁዶች በመንግስታዊ ስፍራ ብዙ ከፍተኛ (ሥልጣናዊ) ስፍራዎችን ስለያዙ ነው:: ይህም አንድ ታሪካዊ ስውጥን አስከተለ:: ይህም በታሪክ መጽሐፍት «የድሬይፍዩስ ፍርድ» ተብሎ የታወቀውን ታሪካዊ ስውጥ አስገኘ::

#### የድሬይፉስ ፍርድ

ይህ ፍርድ በታህሳስ 22 ቀን 1894 ዓ.ም. (ከ.ል.በኋላ) በፈረንሳይ ጦር ውስጥ በመኮንንነት ይሠራ በነበረው አይሁዳዊ መኮንን ላይ የተካሄደ ነበር:: ይህ ሰው አልፈርድ ድሬይፉዩስ ይባላል በዜግነቱ አይሁዳዊ ነበር:: በፈረንሳይ ሠራዊት ውስጥ በመኮንንነት በኋላም በጀኔራልነት ያገለገለ ነበር:: በአጠቃላይ ክሱ በሙሉ ትክክል አልነበረም:: ፍርዱ በደቡብ አሜሪካ በፈረንሳይ ጉያ ባለችው በካይን ጠረፍ በምትገኘው በዲቪል አይላንድ (ደሴት) በእድሜ ይፍታህ እስራት እንዲያሳልፍ ነበር:: ምክንያቱም ከፍተኛ የክህደት ወንጀል የፈጸመ አድርጎ የተገመተ ስለነበር ነው::የተከሰሰው ሰውጭ ኃይል ማለት ስጀርመን ስልሏል በመባል ነበር::

ይህ ብያኔ በዚያን ጊዜ መላ አውሮፓን አስደንቆ ነበር:: ከዚህም ሁኔታ በ1791 ዓ.ም. (ክ.ል.በኋላ) የወጣው አይሁድን ከሌላው ሕዝብ ጋር እኩል የሚያደርገው ህግ በወረቀት ላይ ብቻ የሠፈረ ሆኖ ቀረ:: በድሬይፉዩስ ላይ በተበየነው ብያኔ ምክንያት መላ አውሮፓ እንደገና በአይሁዶች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዲኖራቸው አደረገ:: ጥር 5 ቀን 1895 በፈረንሳይ ጦር አካዳሚ በተደረገው አሳዛኝ ሥነ ስርዓት ላይ ከድሬይፉዩስ ልብስ ላይ የመቶ አለቅነቱ ማዕረግ ተገፈፈ፣ ሰይፉ ለሁለት ተሰበረ:: በዚህም አሳፋሪ ድርጊት ከጦሩ ተወገደ:: እርሱ ከጦሩ በተወገደ ዕለት ከፈረንሳይ መኮንኖችና ተመልካቾች *«ሞት ለአይሁድ፣ ሞት ለከዳተኞች»* የሚል ጩኸት አስተጋባ ::

በኦውስትሪያ ይኖር የነበረው ቴዎደር ሄርስል የተባለው አይሁዳዊ ጋዜጠኛ ስለዚህ ጩኸት መስከሯል:: በቀንና በሌሊት እንቅልፍ እስከሚያጣ ድረስ በዚህ ነገር በጣም ተጨነቀ:: «ሞት ለአይሁድ! ሞት ለከዳተኞች!» የሚለው ጩኸት ሕሊናውን ደግሞ ደጋግሞ የሚያስጨንቀው ሆነ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር ዕረፍት የነሳው ሆነ:: ቴዎድር ኸርዝል ግንቦት 2 ቀን 1860 ዓ.ም. በቡዳፔስት የተወለደ አይሁዳዊ ነበር:: በ1878 በቪያና የሕግ ትምህርት ማጥናት ጀመረ:: በ1884 የዶክትሬቱን ዲግሪ ከተቀበለ በኋላ ደራሲና ጋዜጠኛ ሆነ:: ትዳር የመሠረተና የሶስት ልጆች አባት ነበር:: ከ1891-1895 በፐርሲ ላለው ለቪያናው ኒው ፍሪ ፕሬስ ተወካይ ሆነ:: በድሬይፉስ ላይ በተፈረደው ፍርድ የዓይን ምስክርና ስለ እርሱ መልእክት (ሪፖርት) የሰጠ ነበር:: ይህ ፍርድ ሕይወቱን ቀየረው:: በኋላ «ይህ በድሬይፉስ ላይ የተፈረደው ፍርድ ወደ ጽዮናዊነት ቀየረኝ» ብሏል:: ኸርዝል ምንም እንኳን አይሁዶች የእኩልነት መብት ቢኖራቸውም ባሉበት ቦታ የማይፈለጉና የተጠሉ እንደሆኑ ተገነዘበ:: ይህ ሰው አንድ ዓላማ ነበረው ይኸውም ወደ አባቶቻቸው ምድር ወደ እስራኤል መመለስ የሚል ነበር:: ወደ ቪያና በተመለሰ ጊዜ በአይሁድ እጅግ ተወዳጅ የሆነውን «የአይሁድ ግዛት» የሚለውን መጽሐፍ በጥር ወር በ1896 አሳተመ:: ብዙዎች አስተያየታቸውን መቀየር ጀመሩ:: ከኸርዝል ሌላ ሌሎች ግለሰቦች ጸሐፊዎች፣ ዶክተሮች የአይሁድ ሕዝብ ወደ ቅድስት ምድራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ማድረግ ጀመሩ::





**በእግዚአብሔር የሰዓት መቁጠሪያ ላይ ያለችው ሰዓት ጠቋሚዋ**

**በድንገት ወደ ፊት ተራመደች**

**1897 የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ**

*«እነሆ የእስራኤልን ልጆች ከሄዱባቸው ከአሕዛብ መካከል አወስዳለሁ፣ ከስፍራም ሁሉ እሰበስባቸዋለሁ ወደ ገዛ ምድራቸውም አመጣቸዋለሁ» (ሕዝ.37:21)::*

ቴዎደር ሄርስል የእርሱን ሀሳብ የሚደግፉ ብዙ ጓደኞችንና ደጋፊዎችን አፈራ:: ከነሐሴ 29-31 ቀን በ1897 ለሚደረገው የመጀመሪያው የጽዮናውያን ስብሰባ ጥሪ አደረገ:: በዚህ ስብሰባ ላይ 199 የሚሆኑ ተመልከቾችና ሁኔታው ያጓጓቸው ሰዎች ተገኙ:: ይህን ስብሰባ በትኩረት የተመለከቱት ብዙዎች ነበሩ:: ቴዎደር ሄርስል የተከበረ ዝነኛ ሰው ሆነ:: አጣዳፊ መልስ በሚያስፈልግ ሁኔታ በድሬይፉስ ላይ የተወሰደውን ፍርድና ፈረንሳዮች የመላ አይሁዶችን ጥፋት መመኘታቸውን ገለጹ:: የአይሁድ ሕዝብ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የተቻላቸውን ነገር የማያደርጉ ከሆነ ይህ የመጨረሻ የዕድላቸው ጊዜ እንደሆነ ተነበየ:: ቢሆንም ይህ ነገር ቀላል አልነበረም:: የአይሁድ ሕዝብ በቀላሉ ወደ ቅድስት አገራቸው ለመመለስ የሚችሉ አልነበሩም:: ምክንያቱም ከ1517 ጀምሮ ምድሪቷን ይገዙዓት የነበሩት ቱርኮች ያኔም እየገዟት ስለነበር ነው:: ቱርክ በዓለም ኃያል መንግሥት ነበረች:: የግዛቱ ስፋት ከዩጎዝላቪያ፣ በግሪክ በኩል በማለፍ እስከ ፐርሺያን ባሕረ ሰላጤ ድረስ ይደርስ ነበር:: ሰሜን አፍሪካ፣ ግብፅና ሌሎች የአረብ አገሮች እንኳን የዚህ ታላቅ ግዛት ተገዢዎች ነበሩ:: ቢሆንም አይሁድ በማንኛውም ሁኔታ መጡ:: አይሁዶች ጥሪውን በግልፅ ሰሙት:: በድብቅ ወደ ፓለስታይን በመግባት ባዶ የሆኑትን መሬቶች ከ500 የአረብ ቤተሰቦች ትንሽ በትንሽ መግዛት ጀመሩ:: በዚያን ጊዜ ሀገሪቱ በሕዝብ የተሞላች አልነበረችም:: ለመጀመሪያ ጊዜ ከ1000 እስከ 2000 አይሁዶች ነበሩ በየአመቱ ይገቡ የነበሩት:: ነገር ግን ወዲያዉኑ በአስደናቂ ሁኔታ ቁጥራቸው እየጨመረ መሔድ ጀመረ::

ቴዎደር ሄርስል ያለ እረፍት አይሁዶች ወደ ጽዮን እንዲመለሱ በመምራት የተቻለውን ጥረት ሁሉ አደረገ:: የአይሁድ ወደ ተስፋ ምድራቸው መመለስ «ብትፈልጉ ይህ ተረት አይደለም» በማለት ቴዎደር ሄርስል ጻፈ:: በሕይወቱ ሳለው ከፍተኛ ግብ ድጋፍ ለማግኘት በመላው ዓለም ዞረ:: ዓላማውም ነፃ የሆነ የአይሁድን መንግሥት ማቋቋም ነበር:: ሄርስል በፒትስበርግ ያለውን የሩሲያውን ቴሳር ተወካይ ጎበኝቷል::